# የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
ታዬ ሕዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ::
ለሰላም፣ ለፍትህ ለሕዝቦች ነፃነት፣
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት::
መሠረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን፣
ሕዝቦች ነን ለሥራ በሥራ የኖርን::
ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ሕዝብ እናት፣
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ፣
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ::

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዢ



- ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ቤትሽ ንብረት ነው::
- መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይንም እንዳይጠፋ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ::
- ቀጥሎ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚረዱ 10 ነጥቦች ቀርበውልሃል/ቀርበውልሻል::

1. መጽሐፉን እንደ ኘላስቲክ፣ ጋዜጣ ወይንም መሰል ወረቀቶች በመጠቀም ሸፍን/ሸፍኝ::
2. ምንጊዜም መጽሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጭ::
3. መጽሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው::
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገጾች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ::
5. ለመጽሐፉ የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ::
6. ከመጽሐፉ ውስጥ ገጾችን ወይንም ስዕሎች በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/አታውጪ::
7. የተቀደዱ ገጾች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይንም በኘላስተር ጠግን/ጠግኝ::
8. መጽሐፉን ከትምህርት ቤት ቦርሳህ/ቦርሳሽ ውስጥ በምታስገባበት/በምታስገቢበት እና በምታስወጣበት/በምታስወጪበት ጊዜ ጥንቃቄ ውሰድ/ውሰጂ::
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ/አድርጊ::
10. አዲስ መፅሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት በመጀመሪያ መጽሐፉን በጀርባው አስቀምጥ/አስቀምጭ:: ቀጥሎ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ግለጥ/ግለጭ:: መጽሐፉ የሚታጠፍበት ገፅ ላይ በዝግታ ጫን በማድረግ አስተካክል/አስተካክይ:: ይህም ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዲቆይ ይረዳል::

# የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ
## 5ኛ ክፍል


**ፀሐፊዎች፡-**

1. አቶ ሸዋቀና ቸርነት
2. አቶ ቦጋለ ስብሃቱ
3. አቶ አሰግደው ተስፋዬ
4. አቶ ተስፋዬ ከፋለ
5. አቶ ጌታቸው በለጠ
6. ወ/ሮ ፀሐይ መሳኩ
7. ወ/ሮ ውዳሳት ገዳሙ
8. ወ/ሮ የዝና ወርቁ
9. ወ/ሮ አጋረደች ጀማነህ
10. አቶ ብቃለ ስዩም
11. አቶ የሻው ተሰማ

**አዘጋጆችና አርታኢአን፡-**

አቶ ግርማ አለማየሁ
አቶ ዳንኤል አበበ
አቶ ቱጁባ በቃና



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

© ትምህርት ሚኒስቴር
የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ISBN 978-99944-2-050-6

# ማውጫ

ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ..................................................... 1

ምዕራፍ ሁለት፡- የሕግ የበላይነት ..................................................... 13

ምዕራፍ ሦስት፡- እኩልነት ..................................................... 26

ምዕራፍ አራት፡- ፍትሐዊነት ..................................................... 40

ምዕራፍ አምስት፡- የሀገር ፍቅር ..................................................... 55

ምዕራፍ ስድስት፡- የኃላፊነት ስሜት ..................................................... 69

ምዕራፍ ሰባት፡- ጠንካራ የሥራ ባህል ..................................................... 81

ምዕራፍ ስምንት፡- ራስን መቻል ..................................................... 93

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የቁጠባ ባህል ..................................................... 105

ምዕራፍ አሥር፡- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ..................................................... 117

ምዕራፍ አሥራ አንድ፡- ዕውቀትን መሻት ..................................................... 127

# ምሥጋና

*ይህ መጽሐፍ ጥራቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲወጣ በርካታ ሰዎች ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። Ms. Myra Murphy ለመጽሐፉ አዘጋጆች ተማሪ አሳታፊና ምቹ የሆነ የመጽሐፍ አዘገጃጀት ሥልጠና በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ አድረገዋል። Ms. Myra Murphy በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ወጪያቸውን የሸፈነው የአውሮፓ ዩኒየን በመሆኑ ከፍተኛ ምሥጋና ይገባዋል።*

*በመጽሐፉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የተለያዩ ምስሎች በመለገስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፣ በወቅቱ የነበረው የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢትዮጵያ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ላደረጉት ድጋፍ ምሥጋና ሊቸራቸው ይገባል።*

*በአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ውስጥ የሚገኘው የመማሪያ ማስተማሪያ አዘገጃጀት ዩኒት መጽሐፉን ለማሣተም የሚያስችል የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀትና ለዓለም ባንክ በመስጠት ላደረገው አስተዋጽኦ ሊመሰገን ይገባዋል።*

*በተለይም የቪኤሶ ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አባል የሆኑት Mrs. Helen Papworth መጽሐፉን ከወትሮ ለየት ባለመልኩ ፎርማት በማድረግ ልዩ አድናቆት የሚሰጠው ተግባር በማከናወናቸው ሊመሰገኑ የሚገባ ሲሆን፣ የቪኤሶ ኢትዮጵያም የበጎ ፈቃደኞች ወደሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በመምጣት ሙያቸውን እንዲያካፍሉን በማድረጉ ከፍተኛ ምሥጋና ስናቀርብ በከፍተኛ ደስታ ነው።*

# ምዕራፍ አንድ

# ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የዴሞክራሲና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምንነትን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡
- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸውን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡
- የልዩነትን ምንነትና ልዩነትን እንዴት አቻችሎ መኖር እንደሚቻል ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡
- የፌደራልና የክልል መንግሥታትን ምንነት ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡
- የውጭ ግንኙነት ምንነት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡

## 1.1 ዴሞክራሲ ምንድንነው?



*ሥዕል 1.1 የክፍል አለቃ ምርጫ*



*ሥዕል 1.2 የትምህርት ቤቱ ሥነሥርዓት መመሪያ*

- *በሥዕል 1.1.* ላይ ምን ይታያችኋል? በክፍሉ ውስጥ ምን እየተደረገ እንደሆነ ገምቱ፡፡
- *በሥዕል 1.2* ላይ እንደምትመለከቱት በአ ዳራሹ ውስጥ ምን እየተደረገ እንደሆነ ገምቱ፡፡
- ዴሞክራሲ የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ ሳትሰሙት አትቀሩም፤ ዴሞክራሲ የሚለ ውን ቃል ስትሰሙ በአእምሮአችሁ የሚ መጣው ሀሣብ ምንድን ነው?

### የክፍል አለቃ ምርጫ

አቶ መርጋ በፍኖተ ጥበብ ትምህርት ቤት የ5ኛ ክፍል ኃላፊ መምህር ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ ለክረምት ዕረፍት ተዘግቶ ከተከፈተ አንድ ሳም ንት ሞልቶታል፡፡ መምህር መርጋ ባለፈው ዓመት የዚህ ክፍል አለቃ ግርማቸው እንዲሆን የተመረጠው ቀደም ሲል በነበሩት መምህር እን ደነበር ማወቃቸውን ተናገሩ፡፡ በመሆኑም ያለ ፈው ዓመት አለቃ የነበረው ግርማቸው በዚህ ዓመትም እንዲቀጥል ወይም ሌላ አዲስ አለቃ መምረጥ ይፈልጉ እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠየቋ ቸው፡፡ ተማሪዎቹም በአብዛኛው ፍላጎታቸው አዲስ አለቃ መምረጥ መሆኑን ገለፁ፡፡ ሆኖም የተወሰኑ ተማሪዎች ግርማቸው እንዲቀጥል በመ ፈለጋቸው ለክፍል አለቃነት በድጋሚ እንዲወዳ ደር በጋራ ስምምነት ላይ ደረሱ፡፡

በዚሁ መሠረትም የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ተማሪ ግርማቸውን፣ ተማሪ ከድርን እና ተማሪ ዓለሚ ቱን ለምርጫ እንዲወዳደሩ አቀረቡ፡፡ ተማሪ ከድርን የክፍል አለቃ እንዲሆን የመረጡት 15 ተማሪዎች ሲሆኑ ለተማሪ ግርማቸው ድምፅ የሰጡ ደግሞ 12 ተማሪዎች ነበሩ፡፡ የቀሩት 40 ተማሪዎች ድምፃቸውን የሰጡት ለተማሪ ዓለሚቱ ነው፡፡ ተማሪ ዓለሚቱ በአብላጫ ድምፅ ስለተመረጠች የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች አለቃ ሆነች፡፡

የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ለዚህ ዓመት መሪ የሚሆናቸውን አለቃ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በመምረጣቸው ደስተኛ ሆኑ፡፡

የፍኖተ ጥበብ ትምህርት ቤት የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ትወክለናለች፣ በደንብ ትሠራልናለች፣ ብለው ያመኑባት እና የመረጧት ተማሪ ዓለሚቱም በከፍተኛ ድምፅ ስለመረጧት ለጓደኞቿ ምሥጋና አቀረበች፡፡ ተማሪዎቹም ዴሞክራሲ ማለት ይሄ ነው፣ የሥልጣን ባለቤት ሆንን ብለው ፈነደቁ፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ተማሪዎቹ ራሳቸው በመረጡት አለቃ መመራታቸው መልካም መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ የተመረጠችው አለቃ ሥራዋን በደንብ ካልሠራችና ኃላፊነቷን በአግባቡ ካልተወጣች ሌላ የተሻለ ሊመርጡ እንደሚችሉ ከጋራ መግባባት ላይ ደረሱ፡፡ የበፊቱ አለቃም ሥልጣኑን በሠላማዊ መንገድ ለአዲሷ አለቃ አስረከበ፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት ሂደትን በሥዕል 1.2 ላይ እንዳያችሁት ተማሪዎቹ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በዴሞክራሲያዊ አካሄድ በሚመሩበት የሥነሥርዓት መመሪያ ላይ ውይይት በማድረግ እና የማሻሻያ አስተያየት በመስጠት በንቃት እንደተሳተፉ ሁሉ ሕዝቡም በራሱ ጉዳይ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ ይሳተፋል፡፡

በአጠቃላይ በዴሞክራሲ ሥርዓት መሪ ሲመረጥ የሚመለከታቸው ሰዎች በምርጫው ላይ በእኩልነት ይሳተፋሉ፡፡ በአብላጫ ድምፅ የተመረጠው አለቃ ወይም መሪ ይሆናል፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ሕዝቡ እሱን በሚመለከት በሚደረግ በማንኛውም ውሳኔ ላይ በንቃት ይሳተፋል፡፡

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ከላይ ባነበባችሁት ፅሁፍ እና በሥዕሉ ውስጥ ባስተዋላችሁት ተግባር የተገነዘባችሁትን መሠረት በማድረግ ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፁ፡፡
2. ከላይ በጥያቄ 1 ላይ የሰጣችሁት የዴሞክራሲ ትርጉም ከንባቡ በፊት ከሰጣችሁት ትርጉም ጋር ምን ያህል ይመሳሰላል፡፡
3. መምህር መርጋ የክፍሉ አለቃ ግርማ ቸው ሆኖ እንዲቀጥል ቢያደርጉ ምን ችግር አለው? ተወያዩበት፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ከክፍል አለቃ ምርጫ እና በትምህርት ቤት የሥነ ሥርዓት መመሪያ ላይ ከመወያየት ሌላ ዴሞክራሲ የሚገለፅባቸው አሠራሮች አሉ? ካሉ ምሳሌዎችን ጥቀሱ፡፡ ከሌሉ ደግሞ በምን በምን መልኩ ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች ሊኖሩ እንደሚገባቸው ዘርዝሩ?
2. በክፍላችሁ እና በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሠራር እንዲኖር ማድረጉ የሚኖረው ጥቅም ግለፁ?

ዴሞክራሲ የሚለው ቃል "ዴሞስ" እና "ክራቶስ" ከሚሉ ሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘ ነው፡፡ ዴሞስ ማለት በአንድ ሀገር የሚኖር ሕዝብ ማለት ሲሆን ክራቶስ ማለት ደግሞ ሥልጣን ወይም አመራር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ሥልጣን ወይም አመራር የሕዝብ የሆነበት አስተዳደር ማለት ነው፡፡ በሥዕል 1.1 ላይ እንዳያችሁት ተማሪዎች አለቃቸውን በመረጡበት አካሄድ ሕዝቡም የሚመሩትንና የሚያስተዳድሩትን በፍላጎቱ መምረጥና በመረጠው መሪ የሚተዳደርበት ሥርዓት ዴሞክራሲ ይባላል፡፡

## 1.2 የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ምንነት

### 1.2.1 የሰብዓዊ መብቶች ምንነት

- ሰብዓዊ መብት ማለት ምን ማለት እን ደሆነ ትርጉሙን በራሳችሁ አባባል በወ ረቀት ላይ በፅሑፍ አስፍሩ::
- የጻፋችሁትን ትርጉም አጠገባችሁ ካሉት ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት::

**ሰብዓዊ መብት** ማለት ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ያላቸው መብት ነው:: ለምሳሌ የሕይወት እና የአካል ደህንነት መብቶች ማንኛውም ሰው ሰው በመሆኑ ያሉት ሰብዓዊ መብቶች ናቸው:: ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር በሕይወት የመኖር መብቱ አይደፈርም:: የአካል ደህንነት መብት ሲባል ማን ኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ማለት ነው::

### 1.2.2 የዴሞክራሲያዊ መብቶች ምንነት



*ሥዕል 1.3 የክበብ ምሥረታ*

- ሥዕሉ ውስጥ የሚንፀባረቀው ዴሞክራ ሲያዊ መብት ምን እንደሆነ ተናገሩ::
- ከሥዕሉ በመነሳት ዴሞክራሲያዊ መብት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፁ::

**ዴሞክራሲያዊ መብት** ማለት በዴሞክራሲ ሥር ዓት ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦችም ሆኑ ሕዝቦች የሥርዓቱ አባል በመሆናቸው የሚኖራቸው በሕግ የሚደነገጉ መብቶች ናቸው:: በዴሞክራሲ ሥር ዓት ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው ዴሞክራሲያዊ መብቶች በርካታ ናቸው:: ለምሳሌ በማኅበር የመደራጀት መብት አንዱ የዴሞክራሲ መብት ማረጋገጫ ነው:: ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ለሆነ ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው::

ከዚህ አንፃር ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የተለያዩ ክበባትን የመመሥረትና በተ ለያዩ ክበባት ውስጥ የመሳተፍ መብት አላ ቸው:: ተማሪዎቹ በነዚህ መብቶቻቸው ለመ ጠቀም ክበባቱን በሚመሠርቱበት ጊዜ የትም ህርት ቤቱን ደንብና መመሪያ ማክበር ይጠበቅ ባቸዋል::

በክበባቱ ውስጥ በሚሳተፉበትም ጊዜ የትምህርት ቤቱን ማሕበረሰብና የሌሎችን ተማሪዎች ክብርና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው::

መብት የሚለው ቃል በውስጡ ግዴታንም ያመ ለክታል:: መብት ብቻውን ሙሉ አይደለም:: መብት ባለበት ሁሉ ግዴታም አለ::

መብት ሲባል ሰዎች ያለባቸውን ግዴታና ኃላፊ ነት አቅፎ መያዙን ማወቅ አግባብ ይሆናል:: ስለዚህ ማንኛውም ሰው መብቱን ለመጠቀም ሲፈ ልግ የሌሎችን ሰዎች መብት በማይጥስ ሁኔታ መጠቀምና መብታቸውን የማክበር ግዴታ እን ዳለበት መዘንጋት አይኖርበትም::

**መልመጃ 3**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. የሰብዓዊ መብቶችን ምንነት በምሳሌ ግለፁ::
2. የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ምንነት በምሳሌ ግለፁ::

## 1.3 ልዩነት

### 1.3.1 በክፍልና በትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች



*ሥዕል 1.4 ተማሪዎች በእረፍት ሰዓት*

- *ሥዕል 1.4ን በደንብ ተመልከቱ:: ከጐናችሁ ካለው ተማሪ ጋር በመሆን በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በተማሪዎች መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን ዘርዝሩ::*
- *አንዳችሁ ከሌላችሁ ጋር የምትመሳሰሉባቸውንና የምትለያዩባቸውን አምስት አምስት ልዩነቶች ዘርዝሩ::*

ልዩነት ማለት በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዕድሜ፣ በፆታ፣ በመልክ፣ በቁመት፣ በችሎታ እና በመሳሰሉት አንዱ ከሌላው ጋር አለመመሳሰል ማለት ነው:: አንዳችን ከሌላችን ጋር የምንመሳሰልባቸው በርካታ ነገሮች ሲኖሩ የምንለያይባቸውም ብዙ ነገሮች አሉ:: ዋናው ቁምነገር ከምንለያይባቸው ነገሮች ይልቅ የምንመሳሰልባቸው ነገሮች የበለጡ መሆናቸውን ማወቅ ነው:: ሌላው ትልቁ ነገር ልዩነት መኖሩ የማይቀርና አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ነው:: ልዩነት መኖሩ ኑሮአችንን እና ሕይወታችንን የበለጠ አስደሳችና ውብ የሚያደርግ መሆኑንም መገንዘብ ይኖርብናል::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. **ልዩነት ማለት ምን ማለት ነው?**
2. **ልዩነታችን ውበታችን ነው ሲባል ምን ማለት ነው?**

### 1.3.2 ልዩነትን አቻችሎ በሠላም መኖር

- ከጓደኞችሁ፣ ወይም ከወንድምና ከእህታችሁ ጋር በጨዋታ ላይ ወይም በንግግር ወቅት መስማማት አቅቷችሁ የተጣላችሁበትን ጊዜ አስታውሱ::
- አጠገባችሁ ላለ/ላለች ጓደኛችሁ ገጠመኛችሁን ንገሩ:: የተጣላችሁበት ምክንያት ምን እንደነበር እና በፀቡ ወቅት ምን እንደተፈጠረ በአጭሩ ንገሯቸው::

## እርግበ እና ፋጦ

እርግበ እና ፋጦ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ናቸው:: የእርግበ ቤተሰቦች ገበሬዎች ሲሆኑ የፋጦ ደግሞ ነጋዴዎች ናቸው:: እርግበ እና ፋጦ ዘወትር በዕረፍት ሰዓታቸው የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት ይወያያሉ:: አንዳንዴም ይከራከራሉ:: ሆኖም አንድም ቀን በሃሳብ ልዩነት የተነሣ ተጣልተው አያውቁም::

ከተቻለ ይተማመናሉ ካልሆነ ግን አንዳቸው የሌላውን ልዩነት በማክበርና በመቀበል ተቻችለው ክርክራቸውን በሠላም ይደመድማሉ::

አንድ ዕለት ግን እርግበ እና ፋጦ ከወትሮው ትንሽ ለየት ያለ ነገር ገጥሟቸዋል:: ከገበሬ እና ከነጋዴ የትኛው የበለጠ ለሀገር ይጠቅማል? የሚል ክርክር አነሱ:: እርግበ ገበሬ ይበልጣል ስትል ፋጦ ደግሞ ነጋዴ ነው የሚበልጠው አለች:: ሁለቱም በክርክራቸው ወቅት ከወትሮው የተለየ ሁኔታ ያሳዩ ነበር:: ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጯጯሁ ጀመር:: ተራ ሳይጠብቁ የመጣላቸውን ይናገሩ ስለነበርም መደማመጥ አልቻሉም::

ከብዙ ንትርክ በኋላ ግን ሁለቱም ሁኔታቸው ለእራሳቸው ገርሟቸው ምን ነካን? ምን ሆነናል? ብለው ራሳቸውን ጠየቁ:: ከዚያም ለመካረራቸውና ላለመደማመጣቸው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተገነዘቡ:: መግባባት ያልቻሉበት ምክንያት እርግበ ቤተሰቦቿ ገበሬ በመሆናቸው ገበሬ እንዲበልጥ በመፈለጓ፤ ፋጦም ደግሞ ቤተሰቦቿ ነጋዴዎች ስለሆኑ ለነጋዴ በማዳላቷ እንደሆነ ተረዱ:: የፈፀሙት ተግባር ተገቢ እንዳልሆነ አምነው በድርጊታቸው ተፀፀቱ:: በመጨረሻ ልዩነታቸውን አስወግደው ገበሬም ሆነ ነጋዴ ለሀገር እድገት ጠቃሚ መሆናቸውን ተማመኑ:: ገበሬው ነጋዴ ከሌለ ነጋዴውም ገበሬ ከሌለ በሥራቸው ውጤታማ እንደማይሆኑ ተረዱ:: የዕረፍት ሰዓት ማለቁን የሚያበስረው ደወል ተደወለ:: እርግበና ፋጦ ከተቀመጡበት ተነስተው ተቃቀፉና ወደ ክፍላቸው ሄዱ::

**መልመጃ 5**

?

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የማከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. እርግበ እና ፋጦ በክርክራቸው ወቅት በመደማመጥ ፋንታ የተጯጯሁት ስምንድን ነው?
2. ልዩነትን አቻችሎ ከሌሎች ጋር በሠላም ለመኖር የሚያስፈልገን ነገር ምንድን ነው?
3. ከእርግበ እና ከፋጦ ታሪክ ምን ትምህርት አገኛችሁ?

ልዩነትን አቻችሎ ከሌሎች ጋር በሠላም ለመኖር የሚያስፈልገን ትልቁ ነገር ትዕግሥት እና መደማመጥ ነው::

ሰዎች በተፈጥሮ የሚለያዩባቸው በርካታ ነገሮች እንዳሏቸው ተረድተናል:: ሰዎች ሁሉ የየራሳቸው አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እምነት አላቸው:: የአመለካከትና የአስተሳሰብ ልዩነት በመኖሩ ደግሞ ማንም የኔ ሃሳብ ምን ጊዜም ትክክል ነው የሌላው ስህተት ነው ማለት አይችልም:: እኔ ያልኩት ብቻ ትክክል ነው የሚል ነገር ከመጣ በሠላም አብሮ ለመኖር አይቻልም:: ግጭት ብጥብጥና ሁከት ይፈጠራል:: ስለዚህ ግጭትና ብጥብጥ እንዳይከሰት ልዩነትን አቻችሎ በሠላም አብሮ ለመኖር ታጋሽነት እና መደማመጥ በጣም ጠቃሚ ነው:: ታጋሽነት ልዩነትን ለመቀበልና ተቻችሎ በሠላም ለመኖር ይረዳል:: ታጋሽነት በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በችሎታ እና በመሳሰሉት ልዩነት ቢኖረንም የሌሎችን ስሜት በመረዳትና በማክበር እየተረዳዱ አብሮ ለመኖር ይጠቅማል::

ልዩነትን ማክበር ወይም በፀጋ መቀበልና ልዩ ነቶችን አቻችሎ በሠላም መኖር ማለት እምነቱ፣ አመለካከቱ መልኩ፣ ዘሩ፣ ወዘተ ከኛ የተለየ ቢሆንም የማንኛውንም ሰው መብት ማክበርና ክብሩን መጠበቅ ማለት ነው:: የሰው ልጅን ልዩ ነት እንደጠቃሚ ሀብት በመቁጠር ማድነቅ፣ ሁሉም ዓይነት የሰው ልጅ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ወዘተ በጐና ጠቃሚ አስተዋፅኦ እንዳለው አምኖ መቀበል ነው:: ይህን ማድረግ መቻል ደግሞ የሰው ልጆች ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ በሠላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ያደርጋል::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?


1. ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በቤተሰብ አባላት መካከል ልዩነትን በፀጋ በመቀበልና ልዩነቶችን አቻችሎ በሠላም በመኖር ፈንታ መቻቻል ጠፍቶ ፀብና ግጭት የተከሰተበትን አጋጣሚ መንስዔ ለፀብና ለግጭቱ የተሰጡ መፍትሔዎች ያካተተ ከአንድ ገፅ ያልበለጠ ጽሑፍ አቅረቡ::
2. በመጨረሻ ከዚህ አጋጣሚ ክስተት ምን ትምህርት እንዳገኛችሁ በአጭሩ ግለፁ::

## 1.4 የመንግሥት ሥርዓት በኢትዮጵያ

### 1.4.1 የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ምንነትና አስፈላጊነቱ



*ሥዕል 1.5 ለመምረጥ የተሰለፉ ሰዎች*




*ሥዕል 1.6 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት አወቃቀር*

- ሥዕል 1.5 የሚያሳየው ሰዎች ምን ሲያደርጉ ነው?
- ሥዕል 1.6 ምን ያሳያል?
- መንግሥት የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ሃሣብ ምን እንደሆነ ግለፁ::

ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሕዝብ ሃሳቡን በነፃ የሚገልፅበትና የሚሳተፍበት የመንግሥት አመ ራር ዓይነት ነው:: በዴሞክራሲያዊ መንግሥት አመራር ውስጥ ሕዝቡ በዋናነት የሚሳተፈው በመምረጥና በመመረጥ ነው:: ከዚህም በላይ ሕዝቡ በተለያዩ ጉዳዮች ውስጥ ለምሳሌ በአካባቢ ልማት በንቃት ይሳተፋል::

ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሕዝብ የሚሳተፍበት ሥርዓት በመሆኑ በርካታ ጥቅሞች አሉት:: ከጥ ቅሞቹ መካከል በዋናነት የሚከተሉት ይጠ ቀሳሉ:-

- የሕዝቦችንና የሌሎችን መብቶችና ጥቅ ሞችን በተገቢው መንገድ ያስጠብቃል፣
- መልካም የሆነ አስተዳደር ያሰፍናል፣
- ሕዝቦች በሠላምና በተረጋጋ መንፈስ ሠርተው እንዲኖሩ ያስችላል:: በዚህም የሀገር ዕድገት ይፋጠናል::

## መልመጃ 7

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

?

1. ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ምን ዓይነት መንግሥት ነው?
2. የዴሞክራሲያዊ መንግሥትን ጥቅም ዘርዝሩ?

## 1.4.2 የፌደራል መንግሥት ምንነት

- ፌዴራል የሚለውን ቃል ትርጉሙን ታው ቃላችሁ? እስቲ ፌዴራል የሚለውን ቃል ስትሰሙ በአዕምሮአችሁ የሚመጣው ሃሳብ ምን እንደሆነ በወረቀት ላይ አስፍሩ፡፡
- በወረቀት ላይ ያሰፈራችሁትን የፌደራል ትርጉም አጠገባችሁ ከተቀመጡ ተማሪዎቸ ጋር አስተያዩ፡፡ ምን ያህል ተመሳሳይ ወይም የተለያየ ነው?

**ፌደራል** ማለት ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተ ዳድሩ የክልል መንግሥታት በሕብረት መሥ ርተው የሚኖሩበት የመንግሥት ሥርዓት ነው፡፡ በፌዴራል ቅርፀ መንግሥት ውስጥ አንድ ማዕ ከላዊ መንግሥት ያዋቀሩ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ በርካታ መንግሥታት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞ ክራሲያዊ ሪፐብሊክ 9 አባል የክልል መንግ ሥታት አሉት፡፡

በፌደራላዊ የመንግሥት ሥርዓት አወቃቀር ሥልጣን በማዕከልና በክልሎች ተከፋፍሎ በሕግ የተለየ ነው፡፡ የማዕከላዊ መንግሥት ፌደራል መንግሥት የሚል ሥያሜ ሲኖረው በሕግ ከተ ሠጠው ሥልጣን ውጭ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ የክልል መንግሥታትም በሕግ ከተ ሠጣቸው ሥልጣን ውጭ በፌዴራል መንግሥቱ ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም፡፡


## መልመጃ 8

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. ፌደራል የሚለው ቃል ትርጉም እናንተ ከሰጣችሁት ምላሽ ጋር ምን ያህል እንደሚቀራረብ አነጻጽሩ፡፡
2. ፌደራል ምን ዓይነት የመንግሥት ሥርዓት ነው?

## 1.4.3 የክልል መንግስታት ምንነት




| ክልል | ዋና ከተማ |
|---|---|
| 1. ትግራይ | መቀሌ |
| 2. አፋር | ሰመራ |
| 3. አማራ | ባህር ዳር |
| 4. ኦሮሚያ | ፊንፊኔ |
| 5. ሶማሌ | ጅጅጋ |
| 6. ቤኒሻንጉል ጉምዝ | አሶሣ |
| 7. ደቡብ ሕዝቦች | ሐዋሳ |
| 8. ጋምቤላ | ሐረር |
| 9. ሐረሪ | ጋምባላ |
| 10. አዲስ አበባ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 11. ድሬደዋ | ድሬደዋ |

*ሥዕል 1.7 የኢትዮጵያ ካርታ*

- ኢትዮጵያ ስንት የክልል መንግሥታት አሏት? የክልሎቹን ሥም ዘርዝሩ፡፡
- የክልል መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው?

ከፌደራሉ መንግሥት ቀጥሎ ከፍተኛው አደ ረጃጀት ክልል ነው፡፡ ክልሎች በሕዝብ አሰፋ ፈር፣ በቋንቋ፣ በማንነት እና በፈቃደኝነት ላይ በመመስረት ይዋቀራሉ፡፡ በዚህ መሠረት ኢት ዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ዘጠኝ የክልል መንግሥ ታት አሏት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
2. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
3. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
4. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
5. የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
6. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
7. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
8. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣
9. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ናቸው፡፡


**መልመጃ 9**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. የክልል መንግሥትን ምንነት ግለፁ?
2. የምትኖሩበት ክልልና የተጎራባች ክልሎችን ስም ጥቀሱ?

### 1.4.4 የከተማ አስተዳደር ምንነት፣



*ሥዕል 1.8 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር*

- የከተማ አስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው?

በየክልሉ እራሣቸውን በራሣቸው እንዲያስተዳድሩ እውቅና የተሰጣቸው ከተሞች አሉ። እነዚህ ከተሞች የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች አሏቸው። ምክር ቤቶቹ ከተማውን አስመልክቶ የሕግ አውጪ አካል ናቸው። በምክር ቤቶቹ የተመረጡና የከተሞቹን የዕለት ተዕለት ተግባር የሚያከናውኑ ከንቲባዎች አሉ። ለምሣሌ የአዲስ አበባ ከተማ የራሷ አስተዳደርና ከንቲባ አላት።

**መልመጃ 10**

*የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡*

?

1. በአካባቢያችሁ የከተማ አስተዳዳር አለ? ካለ አስተዳዳሩ በማን እንደሚመራ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።

## 1.5 የውጭ ግንኙነት

### የውጭ ግንኙነት ምንነት እና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ




*ሥዕል 1.9 ኢትዮጵያ እና ጎረቤቶቿ*

- ካርታው ላይ የምታዩዋቸው የኢትዮጵያ ጎረቤት አገሮች እነማን ናቸው? ስማቸውን ጥቀሱ።
- ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር በምን በምን ጉዳዮች ግንኙነት እንደምታደርግ ታውቃላችሁ?

አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገሮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች (በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በመሳሰሉት) የሚፈጥረው ትስስርና ወዳጅነት *የውጭ ግንኙነት* ይባላል።

*የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ* ማለት የአንድ ሀገር መንግሥት ከሌሎች ሀገራት መንግሥታት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ምን መምሠል እንዳለበት የሚያመለክት አጠቃላይ መመሪያ ነው።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር በሠላም፣ በመከባበርና በመልካም ጉርብትና ተስማምቶ አብሮ መኖር ነው።

**መልመጃ 11**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?

1. የውጭ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ዓላማው ምንድን ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሥልጣን ወይም አመራር የሕዘብ የሆነበት የአስተዳዳር ሥርዓት ዴሞክራሲ ይባላል፡፡ የዴሞክራሲ አሠራር ባለበት ሕዝብን በሚመለከት ማንኛውም ውሳኔ ላይ ሕዝብ በንቃት ይሳተፋል፡፡ ሰብዓዊ መብት ማለት ሰዎች ሰው በመሆናቸው ያገኙት መብት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በሕይወት የመኖር መብት አንዱ ሰብዓዊ መብት ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ መብት ደግሞ በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦችም ሆኑ ሕዝቦች የሥርዓቱ አባል በመሆናቸው የሚኖራቸውን በሕግ የሚደነገጉ መብቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የመደራጀት መብት ከዴሞክራሲያዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በመብቶቹ ለመጠቀም ግዴታውን መወጣት እንደሚኖርበት ጠንቅቆ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

ልዩነት ማለት በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዕድሜ፣ በፆታ፣ በችሎታ እና ወይም በሌላ ነገር አንዱ ከሌላው ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ አለመሆን ማለት ነው፡፡ በሕብረተሰብ ውስጥ ልዩነት መኖሩ የማይቀርና አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች በዚህ ልዩነት የተነሳ የየራሳቸው አስተሳሰብና የየራሳቸው እምነት አላቸው፡፡ ስለዚህ ልዩነትን በፀጋ መቀበልና ተቻችሎ በሠላም አብሮ መኖር ያስፈልጋል፡፡ ታጋሽነት ልዩነት ቢኖረንም የሌሎችን ስሜት በመረዳትና በማክበር እየተረዳዱ አብሮ ለመኖር ይጠቅማል፡፡ ልዩነቶችን በፀጋ መቀበልና አቻችሎ በሠላም መኖር ማለት እምነቱ፣ መልኩ፣ ዘሩ፣ ወዘተ ከኛ የተለየ ቢሆንም የማንኛ ውንም ሰው መብት ማክብርና ክብሩን መጠበቅ ማለት ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማለት ሁሉም ሕዝብ የሚካፈልበትና የሚሳተፍበት የመንግሥት አስተዳደር ነው፡፡ ዴሞ ክራሲያዊ መንግሥት የሕዝቦችን መብቶችና ጥቅሞች በተገቢው መንገድ ያስጠብቃል፡፡ መልካም አስተዳደርን ያሰፍናል፡፡ ሕዝቦች በሠላምና በተረጋጋ መንፈስ ሠርተው እንዲኖሩ ያስችላል፡፡

ፌዴራል ማለት የተለያዩ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ መንግሥታት በሕብረት የሚኖሩበት የመንግሥት ሥርዓት ማለት ነው፡፡ ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ በቋንቋ፣ በሕዝቦች በማንነት እና በፈቃደኝነት ላይ በመመስረት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ዘጠኝ የክልል መንግሥታትና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች አሏት፡፡

*የውጭ ግንኙነት ማለት* አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገሮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች የሚፈጥረው ትስስርና ዝምድና ማለት ነው፡፡ *የውጭ ግንኙነት ፖ*ሊሲ ደግሞ የአንድ ሀገር መንግሥት ከሌሎች ሀገራት መንግሥታት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ምን መምሠል እንዳለበት የሚያመለክት አጠቃላይ መመሪያ ነው፡፡ በዚህ መሠ ረት የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት *ፖ*ሊሲ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር በሠላም፣ በመከባበርና በመልካም ጉርብትና ተስማምቶ አብሮ መኖርን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ዴሞክራሲ፣** የሕዝብ አስተዳደር።

**ሥልጣን፣** አንድን ድርጊት ለመፈፀም የመብትና የሕግ ፈቃድ መኖር/ማግኘት።

**መብት፣** ለሰው ልጅ በህግ ጥበቃ ሲደረግለት የሚገባውን ማናቸውንም ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ነው።

**ሰብዓዊ መብት፣** ሰዎች ሰው በመሆናቸው በተፈጥሮ ያላቸው መብት ነው።

**ዴሞክራሲያዊ መብት፣** ግለሰቦችም ሆኑ ሕዝቦች በዲሞክራሲ ሥርዓት በመመራታቸው ምክንያት የሚኖሯቸው መብቶች።

**ፌዴራል፣** ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ የተለያዩ የክልል መንግሥታት ሕብረት መሥርተው የሚኖሩበት የመንግሥት ሥርዓት።

**መንግሥት፣** የሕዝብን ሥልጣን በውክልና በመውሰድ ሀገርን የሚመራ ከፍተኛ የፖለቲካ ተወካይ።

**የውጭ ግንኙነት፣** አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ (በኢኮኖሚ በፖለቲካ እና በመሳሰሉት) የሚፈጥረው ትስስርና ዝምድና ነው።

**የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ፣** አንድ መንግሥት ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያካሂድበት አጠቃላይ መመሪያ ነው።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

### I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ዴሞክራሲ ሥልጣን ወይም አመራር የሕዝብ የሆነበት አስተዳደር ነው::
2. በዴሞክራሲ ሥርዓት ሕዝቡን የሚመለከት ውሳኔ በሚደረግበት ጊዜ ሕዝቡ በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ ይሳተፋል::
3. ዴሞክራሲያዊ መብት ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ያላቸው መብት ነው::
4. ሰብዓዊ መብት ግለሰቦችም ሆኑ ሕዝቦች በዴሞክራሲ ሥርዓት በመመራታቸው ምክንያት የሚኖራቸው የነፃነት መብት ነው::
5. ልዩነት በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በመልክ፣ በችሎታ በመሳሰሉት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ አለመሆን ማለት ነው።

### II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ልዩነት ቢኖረንም የሌሎችን ስሜት መረዳትና ማክበር፣ | ሀ) ዴሞክራሲ። |
| 2. ሁሉም ሕዝብ የሚካፈልበትና የሚሳተፍበት አመራር፣ | ለ) የውጭ ግንኙነት። |
| 3. አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚፈጥረው ትስስርና ዝምድና ነው፣ | ሐ) ፌደራል። |
| 4. የሕዝብን ሥልጣን በውክልና በመውሰድ ሀገርን የሚያስተዳድር አካል፣ | መ) መቻቻል። |
| | ሠ) መንግሥት። |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት ሆኖ እራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ከተማ የትኛው ነው?
   - ሀ) ባሕር ዳር
   - ለ) ድሬዳዋ
   - ሐ) መቀሌ
   - መ) መልሱ አልተሰጠም::
2. እራሱን በራሱ የማስተዳዳር ሥልጣን ያለውና የፌደራሉ መንግሥት ርዕስ ከተማ የትኛው ነው?
   - ሀ) አዲስ አበባ፣
   - ለ) ድሬዳዋ፣
   - ሐ) መቀሌ፣
   - መ) ባሕር ዳር::
3. የዲሞክራሲ ሥርዓት መለያ የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ) የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣
   - ለ) የዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣
   - ሐ) መቻቻል፣ መደማመጥ እና መከባበር፣
   - መ) ሁሉም::

4. የዲሞክራሲያዊ መንግሥት መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ) መሪዎች ሕዝቡ የመረጣቸው ናቸው፣
   ለ) መሪዎች በሃይል ሥልጣን የያዙ ናቸው፣
   ሐ) ሕዝቡ በሀገሩ ጉዳይ ላይ በንቃት ይሳተፋል፣
   መ) መልሱ የለም።

5. በሠላምና በፍቅር አብሮ ለመኖር የሚጠቅመው የትኛው ነው?
   ሀ) ልዩነትን እንደ ጠቃሚ ሀብት በመቁጠር ማድነቅ፣
   ለ) ሁሉም ዓይነት የሰው ልጅ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ወዘተ በጐና ጠቃሚ አስተዋፅኦዎ እንዳለው ማመን፣
   ሐ) አንዱ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ወዘተ ከሌላው የተሻለ እንደሆነ ማመን፣
   መ) ሀ እና ለ።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. ልዩነትን አቻችሎ ከሌሎች ጋር በሠላም ለመኖር የሚያስፈልገን ነገር------------ ነው።
2. የተለያዩ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ መንግሥታት በሕብረት የሚኖሩበት የመንግሥት ሥርዓት -------------------ይባላል።
3. ለሰው ልጅ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባውን ማናቸውንም ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ------------- በመባል ይታወቃል።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ።

1. የዴሞክራሲን ምንነት ግለፁ።
2. በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ መከበር ያለባቸውን መብቶች ዘርዝሩ።

# ምዕራፍ ሁለት


# የሕግ የበላይነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሕገ መንግሥትና የሌሎች ሕጎችን ምንነትና ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ፡፡
- የሕግ የበላይነት ለምን እንደሚያስፈልግ ትረዳለህ/ ትረጂያለሽ፡፡
- የትምህርት ቤት ሕጎችና ደንቦች ለምን እንደሚያስፈልጉ ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፡፡

## 2.1 ሕገ መንግሥት ምንድነው?

- ሕገ መንግሥት ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- ሕገ መንግሥት ምን ጥቅም ይሰጣል?




ሕገ መንግሥት የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መርሆዎች ተደንግገው የሚገለጹበት ሰነድ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕገመንግሥት የዜጐች መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች የሠፈሩበት ሰነድ ነው፡፡

በተጨማሪም ሕገ መንግሥት የአንድን ሀገር የአስተዳደር ሥርዓትን፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጉዳዮችን ያመላክታል፡፡ ሕገ መንግሥት የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ ሲሆን የመንግሥትም ሥልጣን ከዚሁ ይመነጫል፡፡

ሌሎች የሀገሪቱ ሕጐችም መሠረታቸው ሕገ መንግሥት ነው፡፡ ማንኛውም ሕግና አሠራር ከዚህ ሕግ ጋር ተስማሚ መሆን ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

ኢትዮጵያም የራሷ ሕገ መንግሥት አላት፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መንግሥት ፌዴራላዊ አወቃቀርን የሚከተል መሆኑንና ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሥልጣን ባለቤት መሆናቸውንም ይደነግጋል፡፡

**መልመጃ 1**

?

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡፡***


1. ሕገ መንግሥት ምንድን ነው?

### 2.1.1 የሕገ መንግሥት አስፈላጊነት

- ሕገ መንግሥት ለምን ያስፈልጋል?

ሕገ መንግሥት ለአንድ ሀገርና ለዜጐቹ የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ ለምሳሌም ያህል ዜጐች በመብታቸው እንዲጠቀሙና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይደነግጋል፡፡ መንግሥትም ያሉበትን ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ተገንዝቦ እንዲሠራ ይረዳል፡፡ በተለይም ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ዜጐች ወደውና ፈቅደው በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲተዳደሩ ያደርጋል፡፡

## 2.1.2 የክልሎች ሕገመንግሥታት




- *ከዚህ በላይ ከቀረበው ቻርት ምን ትገነዘባላችሁ?*

*በፌዴራል ደረጃ የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ሆኖ ያገለግላል ማለታችን ይታወሣል። ክልሎችም ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚያስችላቸውን የየራሳቸው ሕገ መንግሥት አላቸው። የክልሎች ሕገ መንግሥታት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገው ይዘጋጃሉ። ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ክልል ሕገ መንግሥት የራሱን ተጨባጭ ሁኔታ አገናዝቦና ትኩረት ሰጥቶ ይዘጋጃል።*

**መልመጃ 2**

?

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው፡፡***

1. ሕግ ምንድነው? ስምን ዓላማ ይዘጋጃል?
2. ሕገ መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው?
3. አንድ ሀገር ሕገ መንግሥት ለምን ያስፈልገዋል?
4. ክልሎች የየራሳቸው ሕገ መንግሥት እንዲኖራቸው ለምን አስፈለገ?

## 2.1.3 ሌሎች ሕጐችና ደንቦች

- *ሕግ ለምን ዓላማ ነው የሚወጣው?*
- *ከሕገ መንግሥት ሌላ ሌሎች ሕጐች ሊኖሩ የሚችሉት በምን ሁኔታ ነው?*


*ከሕገ መንግሥት ሌላ በርካታ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አሉ። እነሱም የሚዘጋጁት የሁሉም የበላይ የሆነውን ሕገ መንግሥትን መሠረት አድርገው ነው።*

*የሕግ ዓላማዎች ከሚባሉት ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡*


- *መሠረታዊ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር፣*

- ግጭቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ ማስወገድ፣
- ሠላምና መረጋጋትን ማስፈን፣

### 2.1.4 የትምህርት ቤት ደንቦች



*ሥዕል 2.1 በሥርዓትና ደንብ የሚመራ የመማሪያ ክፍል*




*ሥዕል 2.2 በሥርዓትና ደንብ የማይመራ የመማሪያ ክፍል*

- ከሥዕል 2.1 እና ከሥዕል 2.2 ምን ትረዳላችሁ?
- በየትኛው ክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ነው ውጤታማ ሊሆን የሚችለው?
- እናንተ የምትመርጡት በየትኛው ክፍል የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት ነው?

በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የደንብ መኖርን አስፈላጊነት ከሚያረጋግጡ በርካታ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፤

- ሥርዓት ያለው የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ለማድረግ፣
- በተማሪዎች መካከል እኩልነትን ለማስፈን፣
- ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም፣
- የሥነ ሥርዓት ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣
- የትምህርት ቤቱን አመራርና አሰራር የተ ስተካከለ ለማድረግ ወ.ዘ.ተ፡፡

በአንፃሩም በአንድ ትምህርት ቤት ሥርዓትን የሚያስከብር ደንብ ከሌለ የተማሪዎች መብት አይከበርም፣ በርካታ የሥነ ሥርዓት ችግሮች ይከሰታሉ፣ የጊዜ ብክነት ይፈጠራል፣ የመማር ማስተማሩም ሂደት ውጤታማ አይሆንም፡፡

**መልመጃ 3**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. በትምህርት ቤት ውስጥ የደንብ መኖር ለምን አስፈለገ?
2. በትምህርት ቤት ውስጥ ሕግና ደንብ ባይኖር ምን ችግር ይፈጠራል?

## 2.2 ለሕግ የበላይነት መገዛት

### 2.2.1 ለሕግ የበላይነት መገዛት ምንነት

- ለሕግ የበላይነት መገዛት ማለት ምን ማለት ነው?

ለሕግ የበላይነት መገዛት ማለት ማንኛውም ዜጋ ባለሥልጣናትን ጨምሮ ሕግ ከሁሉም በላይ መሆኑን መቀበል እንደሚገባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ሕግ ሁሉን ሰው እንደሚገዛና ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ የሕግ የበላይነት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደ ምሰሶ ሆኖ የሚያገለግል መርህ ነው፡፡

**መልመጃ 4**

?

***በሚቀጥሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩባቸውና አጭር ሪፖርት በጽሑፍ አቅርቡ፡፡***

1. የሕግ የበላይነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የሕግ የላይነት ለምን ያስፈልጋል?

### 2.2.2 ለሕግ የበላይነት መገዛት ለምን ያስፈልጋል?

- ለሕግ የበላይነት መገዛት የሚያስፈልግባ ቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ዜጐች በሠላምና በደስታ እንዲኖሩ የሕግ የበ ላይነት ያስፈልጋል፡፡ የሕግ የበላይነት የዜጐች መብት በማንኛውም አካል እንዳይጣስ ዋስትና ይሰጣል፡፡ በትምህርት ቤት የሕግ የበላይነት መከበር የትምህርት ቤቱ አመራር፣ መምህራንና ተማሪዎች ሥራቸውን ከሕግ ውጪ እንዳ ይፈጽሙ ያደርጋቸዋል፡፡ የተማሪዎች መብት በማንኛውም አካል እንዳይጣስም ያደርጋል፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ ሕግ የበላይ ሆኖ ካልሠራና ለሕግ የበላይነት መገዛት ከሌለ፤

- አቅመ ደካሞች፣ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ ወዘተ የበርካታ ችግሮች ተጠቂ ይሆናሉ፡፡
- አስገድዶ መድፈር፣ የህፃናት መብት አለመከበር፣ የሰውን ንብረት መዝረፍ፣ ሰውን መግደል ወዘተ ሊከሰት ይችላል፡፡
- ጉልበተኞች ይበዛሉ፣ ደካሞች ይጠቃሉ፣ ሕገ ወጥነት ይበራከታል፣ ሠላም ይጠፋል፣ ፀጥታ ይደፈርሣል፡፡

**የአቶ ነሞምሳ ብሶት**

በዕድገት በሥራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካለፈው የትምህርት ዘመን ጀምሮ የተማሪዎች ንብረት በብዛት ይጠፋል፡፡ በየክፍሉ ንብረት ያል ጠፋባቸው ተማሪዎች ቁጥር ጥቂቶች ናቸው፡፡ የአቶ ነሞምሳ ቱምሣ ሶስት ልጆች እዚሁ ትም ህርት ቤት ይማራሉ፡፡ እንደ አጋጣሚ ከሶስቱም ልጆቻቸው ቦርሣ ውስጥ ዘወትር ዕቃቸው ይሠ ረቃል፡፡ አቶ ነሞምሳ ነገሩ በጣም ስላናደዳቸው ወደ ርዕሰ መምህሩ ቢሮ በመሄድ፤ «ለመሆኑ ትምህርት ቤቱ ሕግ የለውም? ወይስ ሕጉ አይከበርም? ተማሪዎችንስ አትቆጣጠሩም? ትም ህርት ቤቱ እንዴት አጥፊዎችን ማፍሪያ ሊሆን ቻለ በማለት በምሬት ተናገሩ፡፡

በተለይ ኪሩቤል የተባለው የ5ኛ ክፍል ተማሪ ቦርሣ ሲፈተሽ የተወሰኑ ተማሪዎች ዕቃ ተገኘበት:: በዚህም የተነሣ ወላጅ አባቱን ይዞ እንዲመጣ ተደርጐ ሲመረመር እንዴት ይሰርቅ እንደነበር እውነቱን ተናገረ:: ድርጊቱን ይፈጽም የነበረው መስረቅና መደበቅ ጀብድ ስለመሰለው ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ይቅርታ እንዲደረግለትም ጠየቀ:: በዚህም ምክንያት ሁለተኛ ይህንን የመሰለ ጥፋት እንዳይፈጽም ተመክሮና ተገስጾ ይቅርታ ተደረገለት:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የጽህፈት መሣሪያችን ይጠፋል የሚል ሥጋት ተወግዶላቸው በሰላም መማር ጀመሩ::

**መልመጃ 5**

***ከዚህ በላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የእናንተን ትምህርት ቤት ከዚህ ትምህርት ቤት ጋር ስታወዳድሩት ሥነ ሥርዓትን በማስከበር ረገድ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
2. አቶ ነሞምሳ ትምህርት ቤቱ «ሕግ የለውም? ወይስ ሕጉ አይከበርም?» ብለው ሲጠይቁ ምን ማለታቸው ነው?
3. የኪሩቤልን ባህሪ እንዴት ታዩታላችሁ? ተወያዩበት?

### 2.2.3 የዜጐች በሕግ ፊት እኩል መሆን

- ዜጐች በሕግ ፊት እኩል ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

የዜጐች በሕግ ፊት እኩል መሆን ማለት በዜጐች መካከል ልዩነት ሣይኖር ሰዎች ሁሉ በሕግ እኩል የሚዳኙበት ሥርዓት መኖር ማለት ነው:: ይህም ሲባል ዜጐች ሁሉ ለሚፈጽሙት ጥፋት እኩል በሕግ ፊት ተጠያቂ ይሆናሉ ማለት ነው::

በሠላምና በመከባበር ለመኖር ሕግ ያስፈልጋል:: ሕግ ደግሞ ሁሉንም በእኩል ዓይን ያያል:: ስለሆነም ተማሪዎችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት ስለ ሕግ የበላይነት በሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል:: የሕግ የበላይነት እንዲከበርና ሕግ በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ድጋፍ ይፈልጋል:: እንዲሁም በአመራር ላይ ያሉ ሰዎችንም ድጋፍና ክትትል ይጠይቃል::

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው::***

1. ስሕግ የበላይነት መገዛት ስምን ያስፈልጋል?
2. የዜጐች በሕግ ፊት እኩል መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
3. ሕግ የበላይ ሆኖ ካልሠራ ምን ይከሰታል?

## 2.3 ሥነ-ምግባር

### 2.3.1 ሥነ-ምግባር ምንድነው?

- በቤተሰባችሁ ተመስግናችሁ ወይም ተወቅሣችሁ ታውቃላችሁ?
- ምን ምን ነገሮችን ስታደርጉ ነው የምትመሰገኑት?

***ሥነ-ምግባር፡-***

- ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ ባህሪይ መለኪያ ነው፣
- አንድ ሀሳብ ወይም ድርጊት ተቀባይነት ያለው ወይም የሌለው፣መልካም ወይም መጥፎ፣ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑ የሚገለጽበት ነው፣
- የሚያስመሰግኑንን ድርጊቶች ስንፈጽም መልካም ሥነ-ምግባር፣ የሚያስወቅሰን ከሆነ ደግሞ መጥፎ ሥነምግባር አሳይ ተናል ማለት ነው::

- ከዚህ በታች ካለው ሥዕል ምን ትገነዘባላችሁ?



*ሥዕል 2.3. መልካም ቤተሰብ የመልካም ሥነምግባር መሠረት ነው።*

በቤተሰብ ደረጃ ልንፈጽማቸው የሚገቡ በርካታ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች መካከል የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፣

### 1. እናትና አባትን ማክበር፣

- እናትና አባት ሲናገሩና ሲመክሩን በትዕግሥት ማዳመጥና ምክራቸውን በሥራ ላይ ማዋል፣
- የቤተሰብን አቅም በመረዳት ፍላጐትን በአግባቡ መግለጽ፣
- እናትና አባት ከውጪ ሲገቡ ተነስቶ በአክብሮት መቀበል፣
- አቅም በሚፈቅድ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ቤተሰብን ማገዝ ወዘተ...

### 2. ታላቅን ማክበር፣

- ከእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ጋር መከባበርና መፈቃቀር፣
- በዕድሜ ከፍ ላሉ የቤተሰብ አባላት ተገቢውን አክብሮት መስጠት፣
- ወንድምን፣ እህትንና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን ማክበርና ማፍቀር ወዘተ...

### 3. ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት፣


- የግል ንጽህናን መጠበቅ (እጅን፣ ፊትን፣ እግርን፣ ፀጉርን ዘወትር መታጠብ፣ ሰውነትን በንጽህና መጠበቅ፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ ልብስን ማጠብ፣ አቧራ ወይም ቆሻሻ ላይ አለመቀመጥ፣ ወዘተ)
- ትምህርትን በሥርዓት መከታተል (የቤት ሥራን መሥራት፣ ማጥናት፣ ግልጽ ያልሆነውን ነገር መጠየቅ፣ መምህራንን ማክበር፣ እርስ በእርስ መማማር ወዘተ) ናቸው።

**መልመጃ 7**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ሥነምግባር ምንድነው?
2. በቤተሰብ ደረጃ የሚጠበቅ መልካም ሥነ ምግባርን በተመለከተ በትምህርቱ ከተገለፁት ውጪ ለእያንዳንዱ ሶስት ሶስት ምሳሌዎች ስጡ።

ሀ. እናትና አባት ማክበርን በሚመለከት፣
ለ. ታላቅን ማክበር በሚመለከት፣
ሐ. የግል ንጽህናን መጠበቅ በሚመለከት፣




## 2.4 ሥልጣን

### 2.4.1 የሥልጣን ምንነት

- በትምህርት ቤታችሁ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ማን ነው?

በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ትምህርት ቤት ውስጥ ሌሎችን ሰዎች የማዘዝ የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚችሉ የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ሥልጣን ይባላል።

### 2.4.2 የሥልጣን ገደብ ምንነትና ጠቀሜታ

- በሥልጣን ላይ ገደብ ማድረግ ምን ጠቀሜታ አለው?

አባትና እናት ለልጆቻቸው ይበጃል ባሉት መንገድ ቤተሰባቸውን የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው፡፡ ርዕሳነ መምህራንም መምህራንና ተማሪዎችን የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው፡፡ የክፍል አለቆች የክፍሉን ጸጥታና ደህንነት የማስጠበቅ ሥልጣን አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛቸውም ይህንን ሥልጣናቸውን እንደፈለጉ ሊጠቀሙበት አይችሉም፡፡

የአንድ ሰው ሥልጣንና ኃላፊነት ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው ሰው የላቀ የኃላፊነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

መምህርና ርዕሰ መምህር እኩል ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡ ርዕሰ መምህሩ ትምህርት ቤቱን በሚመለከት በርካታ ኃላፊነቶች ስለ አሉበት ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችል በቂ ሥልጣን አለው፡፡ እያንዳንዱ ኃላፊ ሥልጣኑን በአግባቡ መጠቀም ይጠበቅበታል፡፡

ሥልጣኑን በአግባቡ ካልተጠቀመ የሥልጣን ገደቡን አለፈ ይባላል፡፡ በዚህ ምክንያትም የሕግ የበላይነት ይጣሳል፡፡ ይህም ዜጐችን ጉዳት ላይ የሚጥል ሲሆን በፈጻሚው ላይ የሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

**መልመጃ 8**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

?

1. ሥልጣን ምንድነው?
2. በሥልጣን ላይ ገደብ ማድረግ ለምን ይጠቅማል?
3. የክፍል አለቃ የሥልጣን ገደብ ሳይደረግበት ሙሉ ሥልጣን ቢሰጠው ምን ሁኔታ ሊከሰት ይችላል?
4. አንድ መምህር የሥልጣን ገደብ ሳይደረግበት ተማሪዎቹን እንደፈለገ መቅጣት ቢችልስ ምን ጉዳት ሊከተል ይችላል?

## 2.5 ምሥጢር

### የግል ምሥጢር

- የግል ምስጢር የሚባለው ምን ዓይነት ምስጢር ነው?

**ምሥጢር ማባከን**

የወይዘሮ ቀለሟ ባለቤት አቶ ዘመድኩን ባለቤቱን የግል ምሥጢሩን መጠበቅ አለመጠበቋን ለመፈተን ስለፈለገ አንድ ዘዴ ፈጠረ፡፡ የሚነግራትን ምሥጢር ለማንም እንዳትነግር ቃል አስገብቶ ዛሬ ሌሊት ዕንቁላል ወለድኩ ብሎ ትኩስ እንቁላል አሣያት፡፡ ወይዘሮ ቀለሟም አላስችል ብሏት በነጋታው ለጓደኛዋ ቃል አስገብታ ባለቤቴ እኮ ትናንትና ማታ ሁለት ዕንቁላል ወለደ ብላ ነገረቻት፡፡

ያቺም ጓደኛዋ ለሌላ ጓደኛዋ ቃል አስገብታ የእከሊት ባል ሶስት ዕንቁላል ወለደ ብላ ነገረች፡፡ ወሬው በእንደዚህ ሁኔታ እየተባዛ ሄዶ አቶ ዘመድኩን በሚኖርበት መንደር መጠቋቆሚያ ሆነ፡፡ በመጨረሻም ወሬው አቶ ዘመድኩን ጆሮ ደረሰ፡፡ አቶ ዘመድኩንም ወሬውን ሲሰማ በገዛ እጁ ያመጣሁት ጣጣ በተከበርኩበት ሠፈር ተዋረድኩ በማለት በራሱ ላይ ማማረር ጀመረ፡፡ ባለቤቱንም ጠርቶ ምነው ምሥጢሬን መጠበቅ ተሳነሽ እንቁላል የሚወልድ ዶሮ እንጂ ሰው አይደለምን ብሎ ገሰጻት፡፡

ምሥጢር ተብሎ የተነገረን ነገር ቸኩሎ ለሌላው መናገር ለችግር እንደሚዳርግም አስረዳት፡፡ በተከበረበት መንደርም እንዳዋረደችው ገለጸላት፡፡ ከዚህ በኋላ በአቶ ዘመድኩንና በወይዘሮ ቀለሟ መካከል መተማመን የሚባል ነገር ስለጠፋ ሠላም ከቤታቸው ራቀ፡፡

*(ምንጭ አባባ ተስፋዬና ተረቶቻቸው አንደኛ መጽሀፍ)*

**መልመጃ 9**

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. አቶ ዘመድኩን የግል ምሥጢሩን በማባከኑ የደረሰበት ችግር ምንድነው?
2. አቶ ዘመድኩን የግል ምሥጢሩን መጠበቅ ነበረበት ወይስ አልነበረበትም?

ምሥጢር በአንድ ሰው ብቻ ወይም በጓደኛሞች መካከል ወይም ደግሞ በቤተሰብ ደረጃ ወይም በተለያዩ ዓላማዎች ዙሪያ በተሰባሰቡ ሰዎች መካከል ተጠብቆ ለሌላ ሳይተላለፍ የሚያዝ ጉዳይ ነው፡፡

አንዳንድ መረጃዎች ከአንዱ ወደ ሌላው ከተላለፉ በተናጋሪው ወይም በሰሚው ላይ ጉዳት እንደሚያስከትሉ ከተገመተ ወይም ከተረጋገጠ ጉዳዩን ደብቆ የመያዝ ዘዴ ምሥጢር ይባላል፡፡

ምሥጢርን መጠበቅ የመልካም ሥነምግባርና የታማኝነት መለኪያ ነው፡፡ ምሥጢር፤ የግል ምሥጢር፣ የቤተሰብ ምሥጢር፣ የጓደኛ ምሥጢር፣ የሕዝብና የሀገር ምሥጢር ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡

የግል ምሥጢር ሰዎች በሕይወታቸው ለማንም ሳያካፍሉ የሚይዙት ጉዳይ ነው፡፡ ምሥጢሩ ቢታወቅ በራስ ወይንም በሌሎች ላይ ችግር ያስከትላል፡፡ በዚህም ምክንያት ምሥጢር ተብሎ የተነገረንን ነገር በጥንቃቄ ጠብቆ ማቆየት አግባብ ይሆናል፡፡

**ምሥጢርን መጠበቅ የመልካም ሥነምግባር መለኪያ ነው፡፡**

**መልመጃ 10**

?

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. የግል ምሥጢርን አለመጠበቅ ምን ጉዳት ያስከትላል?
2. ምሥጢርን መጠበቅ የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫ ነው የሚባለው ለምንድ ነው?

## 2.6 ሙስና

### 2.6.1 ሙስና ምንድን ነው?

- በሙስና የማይጐዳ የሕብረተሰብ ክፍል ይኖራል ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ሙስናን ለመግታት የመምህራንና የተማሪዎች ሚና ምን መሆን አለበት?

ሙስና አንድ ሰው ያልደከመበትንና የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚፈፀም ድርጊት ነው፡፡ ሙስና ሥልጣንን መከታ በማድረግ በሕገወጥ መንገድ የግል ጥቅምን ለማግኘት የሚፈፀም ድርጊት ነው፡፡ ሙስና ሥፍራ ሣያግደው በየትም ቦታ ሊፈፀም የሚችል ሕገወጥ ድርጊት ነው፡፡ በትምህርት ቤትም ሙስና ሊፈፀም ይችላል፡፡ ሙስና በትምህርት ቤት አካባቢ በተለያዩ አካላት ሊፈፀም ይችላል፡፡

#### 2.6.1.1 በተማሪዎች የሚፈፀሙ የሙስና ዓይነቶች

በተማሪዎች ከሚፈፀሙ የሙስና መገለጫዎች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

- የቤት ሥራን ወይም ፈተናን በራስ ከመሥራት ይልቅ ከሌሎች መኮረጅ ወይም መገልበጥ፣
- የሌላ ተማሪን ንብረት ሰርቆ መውሰድ፣
- የትምህርት ቤትን ንብረት በጥንቃቄ አለመያዝ፣ ማበላሸት ወይም መውሰድ፣
- ትምህርት ቤት ዘግይቶ መምጣት ወይም ከሰዓቱ በፊት ቀድሞ መውጣት ወዘተ...

#### 2.6.1.2 በመምህራን ከሚፈፀሙ የሙስና ዓይነቶች

በመምህራን ከሚፈፀሙ የሙስና መገለጫዎች መካከል ጥቂቶቹ፣

- ተማሪዎችን በእኩል ዓይን አለማየት ወይም አድሎ ማድረግ፣
- ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ለተማሪ ማርክ መጨመር ወይም መቀነስ፣
- የትምህርት ክፍለ ጊዜን በተገቢው መንገድ አለመጠቀም፣
- የትምህርት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ አለመያዝና ማባከን፣
- ለትምህርት ቤቱ ደንብና ሥርዓት ተገዥ አለመሆን ወዘተ. ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

**መልመጃ 11**

?

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የሙስና መገለጫዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. በትምህርት ቤት ደረጃ የሚፈጸሙ የሙስና ዓይነቶችን ጥቀሱ፡፡

### የሙስና አድማስ

መምህርት ዐይናለም ሰዓት አክባሪና የሚያስተ ምሩትን ትምህርት በሚገባ እያዘጋጁ የሚመጡ ነበሩ፡፡ ከጊዜ በኋላ ግን ይህንን ትጋታቸውን እየቀነሱ መጥተዋል፡፡ አርፍዶ ወደ ክፍል መግ ባትና ፈጥኖ ከክፍል መውጣት ማዘውተር ጀም ረዋል፡፡ ትምህርታቸውን በሚገባ ማስተማር ትተዋል፡፡

ፈተናቸው እንደሌሎች መምህራን ፈተና ግልጽ አይደለም፡፡ ሌሎች መምህራን የጥያቄ ወረቀት ሲመልሱ እሳቸው አይመልሱም፡፡ ለሁሉም ተማሪ ከሰማንያ በላይ ውጤት በመስጠት ይታ ወቃሉ፡፡ ባጠቃላይ መምህርቷ የሙስና መገለጫ ባህሪያት ይታይባቸዋል፡፡

**መልመጃ 12**

*ከዚህ በላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. የመምህርት ዐይናለም ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር አስቀም ጧቸው?
2. መምህርቷ ይህንን ባህሪያቸውን እንዲያሻሽሉ ምን ዓይነት አስተያየት ትሰጡአቸኋላችሁ?
3. መምህርቷ ይህንን ባህሪያቸውን ካላሻሻሉ በተማሪው ላይ ምን ችግር ሊፈጠር ይችላል?

#### 2.6.1.3 በትምህርት ቤትና በመኖሪያ አካባቢ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራት

- በአካባቢያችሁ የተፈፀሙ የሙስና ተግባ ራት አሉ? ካሉስ ምንድን ናቸው?

በመኖሪያ አካባቢ ሙስና የሚፈጸምባቸው የተለ ያዩ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በመኖ ሪያ አካባቢያችሁ የጽዳት ዘመቻ የሚካሄድ ቢሆን ሁሉም የአካባቢው ሰው በጽዳት ዘመቻው የተ ግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ይጠ በቅበታል፡፡ ነገር ግን የጽዳት ዘመቻውን የሚ ያስተባብረው ሰው ሌሎች ሲሳተፉ የእርሱ የቤ ተሰብ አባላት እንዳይሳተፉ ቢያደርግ ይህ የሙ ስና መገለጫ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች በተ ለየ የቤተሰቡን አባላት የሚጠቅም ተግባር ፈፅ ሚል፡፡

እንዲሁም በምትኖሩበት ቀበሌ የቀበሌው መስተ ዳደር የተለያዩ መደለያዎችን በመውሰድ አንድ ድርጊት ለእናንተ ወይም ለወላጆቻችሁ ቢፈፅም ይህም የሙስና ተግባር ነው፡፡

በሌላ በኩልም መደለያ ካልሰጣችሁኝ በማለት የቀበሌ ኃላፊዎች ወላጆቻችሁን ወይም እናንተ የሚገባችሁን መብት ቢከለክሏችሁ ይህ የሙስና መገለጫ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር እናንተ ማንኛውንም ጨዋታ በምትጫወቱበት ጊዜ ጨዋታውን ለሚመራው ዳኛ ጥቅም በመስጠት ጨዋታውን ብታሸንፉ ይህ በሙስና የተገኘ ውጤት ነው፡፡

### 2.6.2 ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

- አድሎአዊ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፣
- በተማሪዎች መካከል አለመግባባትን ይፈጥራል፣
- የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ከተማሪዎችና ከወላጆች ያራርቃል፣
- የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲዛባ ያደርጋል፣
- መጥፎ ሥነምግባር እንዲሰፍን ያበረታታል፣ ወዘተ...

**መልመጃ 13**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. በትምህርት ቤት ከሚታዩ የሙስና መገለጫ ምሣሌዎች መካከል በተማሪዎች ሲፈፀሙ የሚችሉትን ዘርዝሩ፡፡
2. በትምህርት ቤት የሚፈፀም ሙስና ምን ጉዳት ያስከትላል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሕገ መንግሥት የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ ሲሆን፣ ማንኛውም ሕግና አሠራር ከዚህ ሕግ ጋር ተስማሚ መሆን አለበት፡፡ ሕገ መንግሥት ዜጐች በመብታቸው እንዲጠቀሙና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይረዳል፡፡

የክልሎች ሕገ መንግሥቶች የፌደራሉን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገውና የክልሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ አገናዝበው ይዘጋጃሉ፡፡ ከሕገ መንግሥት ውጪ በርካታ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አሉ፡፡ የሚዘጋጁትም ሕገ መንግሥትን መሠረት አድርገው ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የትምህርት ቤት ደንብ ነው፡፡ የትምህርት ቤት ደንብ ሥርዓት ያለው የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስፈን ይጠቅማል፡፡

በማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ሕግ ከሁሉም በላይ መሆኑን አምኖ የመቀበል ሁኔታ የሕግ የበላይነት ይባላል፡፡ በአንድ ሀገር ወስጥ ሕግ የበላይ ሆኖ ካልሠራና ለሕግ የበላይነት መገዛት ከሌለ አቅመ ደካሞች ህፃናት፣ ሽማግሌዎች፣ በሽተኞች፣ አነስተኛ ቁጥር ያለቸው የሕብረሰተሰብ ክፍሎች ችግር ሊገጥማቸው ይችላል፡፡

በዜጐች መካከል ያለአንዳች ልዩነት ሰዎች ሁሉ በሕግ የሚዳኙበት ሥርዓት ሲኖር ዜጐች በሕግ ፊት እኩል ሆኑ ማለት ነው፡፡ ሥልጣን በአንድ መሥሪያ ቤት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ሌሎች ሰዎችን ለመምራትና ለማስተባበር የተመደቡ ሰዎች ምን ምን ተግባራትን ለመምራትና ለማስተባበር እንደሚያከናውኑ ይገልፃል፣ እንዲሁም ምን ምን ነገር ላይ መወሰን እንደሚችሉ ያሣያል፡፡

ምሥጢር በአንድ ሰው ብቻ ወይም በጓደኛሞች መካከል ወይም በቤተሰብ ደረጃ ወይም ተመሣሣይ ዓላማ ኖሯቸው በተሰባሰቡ ሰዎች መካከል ተጠብቆ ለሌላ ሳይተላለፍ የሚያዝ ጉዳይ ነው፡፡ የግል ምሥጢር ሰዎች በታማኝነት ለማንም ሰው ሳይነግሩ የሚይዙት ጉዳይ ነው፡፡

ሙስና አንድ ሰው ያልደከመበትንና የማይገባውን ጥቅም ለራሱ ለማድረግ የሚፈጽመው ድርጊት ነው፡፡ በትምህርት ቤትም በተማሪዎችና በመምህራን የሚፈፀሙ የሙስና መገለጫዎች አሉ፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ሕገ መንግሥት፣** | አንድ መንግሥትና ሕዝብ ሲከተለው የሚገባው የተደነገገ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሰነድ ነው፡፡ |
| **ሕግ፣** | ሕገ መንግሥትን መሠረት ያደረገ አስገዳጅነት ያለው የደንቦችና የመመሪያዎች ስብስብ፡፡ |
| **ሥነምግባር፣** | የሰዎችን ባህሪ የሚቆጣጠር ወይም በሰዎች ባህሪይ ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ፣ አንድ ሕብረተሰብ የተቀበለው የትክክለኛ እና ትክክለኛ ያልሆነ ባህሪይ መለኪያ፡፡ |
| **ምስጢር፣** | በአንድ ሰው ብቻ ወይም በጥቂት ሰዎች መካከል ተጠብቆ፣ ከሌሎች ተሰውሮ የሚያዝ ጉዳይ፡፡ |
| **ሰነድ፣** | ውሳኔ ያረፈበት መዝገብ፡፡ |
| **መደንገግ፣** | መወሰን፣ ማወጅ፡፡ |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።*

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።**

1. ኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያዋለችው የራሷ የሆነ ሕገ መንግሥት የላትም።
2. የሕግ የበላይነት ባለሥልጣኖችን አይመለከትም።
3. ሕግ የበላይ ሆኖ ካልሠራ ችግር የሚገጥማቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች አሉ።
4. የርዕሰ መምህር ሥልጣን ገደብ አይደረግበትም።
5. የቤት ሥራን ወይም ፈተናን ከሌሎች መቅዳት ሙስና አይደለም።
6. ምስጢርን መጠበቅ የመልካም ሥነምግባርና የታማኝነት መለኪያ ነው።

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. በአንድ ሰው ብቻ ወይም በጥቂት ሰዎች መካከል ተጠብቆና ከሌሎች ተሰውሮ የሚያዝ ጉዳይ፣ | ሀ. ሕገ መንግሥት |
| 2. የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ፣ | ለ. ሙስና |
| 3. ሕገ መንግሥትን መሠረት ያደረገ አስገዳጅነት ያለው የደንቦችና መመሪያዎች ስብስብ፣ | መ. ሥነምግባር |
| 4. አንድ ሰው ያልደከመበትን የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት የሚፈፀም ድርጊት፣ | ሠ. ምሥጢር |
| 5. ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ ባህሪይ መለኪያ፣ | ረ. ሕግ |
| | ሰ. ደንብና መመሪያ |

**III. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የሕገ መንግሥትን አስፈላጊነት የሚያሣየው የቱ ነው?
   ሀ. ዜጐች በመብታቸው እንዲጠቀሙ ያደርጋል፣
   ለ. ዜጐች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣
   ሐ. መንግሥት ያሉበትን ግዴታዎች እንዲወጣ ያደርጋል፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው።
2. ከሚከተሉት ውስጥ የሕግ ዓላማ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር፣ ሐ. ግጭቶችን ማጠናከር፣
   ለ. ፍትሃዊነትን ማስፈን፣ መ. ሠላም ማስፈን።

3. ስለሙስና እውነት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የስግብግብነት ድርጊት ነው፣
   ለ. የማይገባ ጥቅምን መቀበል ነው፣
   ሐ. በሕገወጥ መንገድ የግል ጥቅምን ማግበስበስ ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡
4. ሰዎች እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ለማንም ሳያካፍሉ የሚይዙት ጉዳይ ----------- በመባል ይታወቃል፡፡
   ሀ. የቤተሰብ ምስጢር፤
   ለ. የጓደኛ ምስጢር፤
   ሐ. የአገር ምስጢር፣
   መ. የግል ምስጢር፡፡

## IV. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. በትምህርት ቤት በመምህራን ሊፈፀሙ ከሚችሉ የሙስና ተግባራት መካከል ሶስቱን ጥቀሱ፡፡
2. በአንድ ትምህርት ቤት ደንብ ለምን ያስፈልጋል? ሶስት ምክንያቶችን ግለፁ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# እኩልነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የእኩልነት ምንነትን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፤
- ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ እንዲሁም ዜጐች ያሏቸውን ዋና ዋና የእኩልነትና የእኩል ተጠቀሚነት መብቶችን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ፤
- የአካል ጉዳተኝነት ምንነትን ትረዳለህ/ ትረጂያለሽ::

## 3.1 የእኩልነት ምንነት

- እኩልነት የሚለውን ቃል በመጀመሪያ ስትሰሙት ወደ አዕምሮአችሁ የሚመጣው ሃሳብ ምንድን ነው?

እኩልነት በእኩል ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች በግልም ሆነ በቡድን በተመሳሳይ ሁኔታ ሊያገኙት የሚገባ መብትና ጥቅም ነው:: በሌላ መልኩ እኩልነት ሰዎች በተመሳሳይ ደረጃ ሊወጡት የሚገባ ሃላፊነትንም ያጠቃልላል:: በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ማንኛውም ዜጋ ያለአንዳች ልዩነት በእኩልነት ሊያገኘው የሚገባ መብትና ጥቅም አለው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው፣ ሰው ስለሆነ ብቻ ከሌሎቹ እኩል መብቱ ሊከበርለት ይገባል:: በተጨማሪም በተመሳሳይ ደረጃና ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ተመሳሳይ ጥቅም የማግኘት እኩል መብት አላቸው::

**እኩልነት ማለት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ዜጐች ሁሉ በግልም ሆነ በቡድን እኩል ሊያገኙት የሚገባቸው መብትና ኃላፊነት ማለት ነው:: እኩልነት በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋና በሌሎችም ልዩነት ሳይደረግ ሊከበር የሚገባ መብት ነው::**


**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በቤተሰባችሁ ውስጥ እኩልነት በምን ጉዳዮች ይገለፃል? ምሳሌ በማቅረብ አስረዱ::

## 3.2 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት? መብቶች




*ሥዕል 3.1 ኢትዮጵያ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች የሕዝቦች ሀገር*

- ከላይ ከቀረበው ሥዕል ምን ተገነዘባችሁ?
- በአካባቢያችሁ የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አባላት ስም በደብተራችሁ ላይ ዘርዝሩ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ ይኖራሉ፡፡ አንዱ ከአንዱ ሳይበላለጡ ሁሉም እኩል ናቸው፡፡ የእኩልነታቸው መገለጫም ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደራቸው፣ በቋንቋቸው መገልገላቸው፣ ባህላቸውን የማበልፀግና የራሳቸውን ሃይማኖት የማራመድ መብቶቻቸውን ተግባራዊ ማድረጋቸው ተጠቃሽ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

**?**

1. በክፍላችሁ ውስጥ ከተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመጡ ጓደኞቻችሁ መብቶች ማክበር ምን ጥቅም ይሰጣል?
2. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሕዝቦች የተከበሩላቸውን የእኩልነት መብቶች በሚገልጹ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡

### 3.2.1 ራስን በራስ የማስተዳደር መብት

- ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው?

**የአገው ሕዝብ**

የአገው ሕዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሕዝቡም በአሁኑ ጊዜ በስፋት የሚገኘው በአማራ ብሔራዊ ክልል በዋግምኽራና አዊ ዞኖች ውስጥ ነው፡፡ በዙሪያው ከሚገኙ ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር በእኩልነትና በመከባበር እየኖረ ይገኛል፡፡ የአገው ሕዝብ የራሱ የሆነ ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ ራሱን በራሱ በማስተዳደር ላይ ነው፡፡ በሀገሪቱ ምክር ቤቶች ውስጥ እንዲሁም በክልሉ ምክር ቤት ሕዝቡ በመረጣቸው ሰዎች ውክልና አግኝቷል፡፡ በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረትም የአገው ብሔረሰብ እራሱን በራሱ በማስተዳደር የእኩልነት መብቱን እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ ይህም በአካባቢው ልማትን ለማምጣትና የሕዝቡን መብት ለማስከበር ጠቅሞታል፡፡

**መልመጃ 3**

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

**?**

1. የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት የሚያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው?
2. የአገው ሕዝብ በዙሪያው ካሉ ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር እንዴት ባለ ሁኔታ እየኖረ ነው?

### 3.2.2 በራስ ቋንቋ የመገልገል መብት

1. በአካባቢያችሁ ከሚነገሩ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች መካከል በስም የምታውቋቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ምንድን ነው?

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ቋንቋዎች አንዱ ከአንዱ ሳይበላለጡ በመግባቢያነታቸው እኩል ናቸው፡፡ ሁሉም ቋንቋዎች ለሚጠቀሙባቸው ሕዝቦች የማንነታቸው መገለጫና ባህላቸውን ማንፀባረቂያ ናቸው፡፡ ሕፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከቤተሰብ፣ ከተወለዱበት አካባቢና ሕብረተሰብ ሊማሩ ይችላሉ፡፡ በራስ ቋንቋ የመገልገል መብት በሕገመንግሥቱ የተከበረ ነው፡፡ የራስ ቋንቋን የመጠቀም መብት ስንል በቋንቋ የመናገር፣ የመፃፍና ቋንቋውን የማሳደግ እንዲሁም ለትምህርት፣ ለሥራ የመጠቀም መብቶችን ሁሉ ያካተተ ነው፡፡

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በራስ ቋንቋ የመገልገል መብት ሲባል ምን ማለት ነው?
2. በራስ ቋንቋ መገልገል ምን ጥቅም ያስገኛል?

### 3.2.3 እኩል የትምህርት እድል የማግኘት መብት

- እኩል የመማር መብት ማግኘት ምን ጠቀሜታ አለው?

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩል የትምህርት እድል የማግኘት መብታቸው በሕገ መንግሥቱ የተከበረ ነው፡፡ ይህ መብት ለሴትም ሆነ ለወንድ፤ ለከተማም ሆነ ለገጠር ነዋሪዎች ያለልዩነት በእኩል ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡ አድሎአዊ አሠራር ሲወገድና ትምህርት ለሁሉም በእኩል ሲዳረስ ሀገራችን ፈጣን ዕድገት ማስመዝገቧን ትቀጥላለች፡፡ ዜጎችም እኩል የመማር መብታቸው ሲከበር ሀገራዊ ስሜታቸው ከፍ ይላል፡፡ ይህም ለሀገሪቱ እድገት ወሳኝ ይሆናል።

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. እኩል የትምህርት ዕድል የማግኘት መብት በምን ይገለጻል?
2. የዜጎች እኩል የመማር መብታቸው መከበር ምን ጠቀሜታ ያስገኛል?

### 3.2.4 እኩል የሥራ ዕድል የማግኘት መብት፤

- እኩል የሥራ ዕድል የማግኘት መብት ሲባል ምን ማለት ነው?

ማንኛውም ሰው ባለው ዕውቀትና ሙያ እኩል የሥራ ዕድል የማግኘት መብት አለው፡፡ የሥራ ዕድል ለማግኘት በፆታ፣ በብሔርና በብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ልዩነት አይደረግም፡፡ አንድ ሰው ከሌሎች ጋር እኩል ችሎታና ልምድ ካለው በእኩልነት ተወዳድሮ ለሥራ መቀጠርና መሥራት ይችላል፡፡ ሥራ የመቀጠርና የመሥራት መብት በአድልዎ፣ በዝምድና፣ በመተዋወቅና በጥቅማ ጥቅም ወዘተ... ምክንያት መሰናከል የለበትም፡፡

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. እኩል የትምህርት ዕድል የማግኘት መብት በምን ይገለጻል?
2. የዜጎች እኩል የመማር መብታቸው መከበር ምን ጠቀሜታ ያስገኛል?

## 3.3 የእኩልነት መብት በትምህርት ቤት

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን መብቶች ዘርዝሩ፡፡

**የነጭ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤**

የነጭ ትምህርት ቤት፣ የማቻክል ወረዳ፣ የአማኑኤል ከተማ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ የአለቆች ህብረት ማቋቋም ስለሚያስፈልግ ከየክፍሉ ተወካይ ተማሪዎች ተመርጠው ስብሰባ ተካሄደ፡፡ በስብሰባውም ላይ መጀመሪያ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ንግግር ካደረጉ በኋላ ከተማሪዎቹ መካከል አስመራጭ ኮሚቴ ተመርጦ ተቋቋመ፡፡ ኮሚቴውም የተማሪዎች ምክር ቤት አባላትን ለመምረጥ የሚከተለውን መመሪያ አዘጋጀ፡፡

መመሪያውም "በምርጫው መሳተፍ የሚችሉት ወንዶችና ምንም ዓይነት የአካል ጉዳት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፡፡ "የሚል ነበር፡፡ ተማሪዎች ግን መመሪያውን በጥብቅ ተቃወሙት፡፡ ኮሚቴውም ጉዳዩን እንደገና እንዲያይና አዲስ መመሪያ እንዲያወጣ በአብላጫ ድምጽ ተወሰነ፡፡

በዚሁ መሠረት የተሻሻለው መመሪያም "ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ተማሪ ለአለቆች ህብረት አባልነት በእጩነት መቅረብና መወዳደር ይችላል፡፡" የሚል ነበር።

በተሻሻለው አዲስ መመሪያ መሠረትም አምስት አባላት ያሉት የትምህርት ቤቱ የአለቆች ህብረት ተቋቋመ።



*ሥዕል 3.2 ተማሪዎች በምርጫው ሂደት ላይ*

**መልመጃ 7**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በምርጫው ሂደት በአስመራጭ ኮሚቴው ምን ዓይነት የአድልዎ አስተሳሰቦች ተንፀባርቀዋል?
2. “ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች በተማሪ ዎች አመራር አባላት ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፡፡” የሚለው አስተሳሰብ ትክክል ነው? ለምን?
3. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የአለቆች ህብረት አለ? ስንት ሴት ተማሪዎች በአመራር ሰጪነት ቦታ ላይ ይገኛሉ?

በትምህርት ቤት ውስጥ በፆታ፣ በቀለም፣ በሃይማ ኖትና በሌሎችም ሁኔታዎች መድልዎ የማይደ ረግባቸው አሠራሮች መኖር የእኩልነት መብቶ ችን መከበር ይገልጻል፡፡ በትምህርት ቤት ግቢ ሊከበሩ ከሚገቡ መብቶች መካከል ማንኛውም ተማሪ ያልገባውን ጥያቄ የመጠየቅ፣ ለተጠየቀ ጥያቄ መልስ የማግኘት፣ በልዩ ልዩ ክበባት ውስጥ የመሳተፍ፣ ትምህርት ቤቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ የመስጠት፣ በትምህርት ቤቱ ንብረት የመጠቀምና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሆኖም ማንኛውም ተማሪ ከመብቱ ጐን ለጐን ግዴ ታዎቹንም በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ለምሳሌ፡ የትምህርት ቤቱን ሕግና ደንብ ማወቅና ማክበር፣ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሌሎች ምሳሌ ሆኖ መገኘትና የክፍልና የቤት ሥራውን በተገቢው ጊዜ መፈፀም ይጠቀሳሉ፡፡

**መልመጃ 8**


***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በትምህርት ቤት ውስጥ ሊከበሩላቸው የሚገቡ መብቶችን ግለጹ፡፡
2. ልትወጧቸው የሚገቡ ግዴታዎች ምንድን ናቸው?

## 3.4 የፆታ እኩልነት

### 3.4.1 የሴቶችና የወንዶች እኩልነት በሁሉም ዘርፍ





*ሥዕል 3.3 የወንድና ሴት በሥራ ላይ*

- የሴቶችና የወንዶች ዕኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?
- በሥዕሉ መሠረት ሴቶች በማንኛውም ጊዜና ቦታ ከወንድ እኩል መሥራት ይችላሉ በሚለው ሃሳብ ትስማማላችሁ?

**የወ/ሮ ጣይቱ ሕይወት**

ሶስናና ከድር የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: በአንድ ወቅት ወ/ሮ ጣይቱ የተባሉትን የቤት እመቤት እንደሚከተለው ቃለመጠይቅ አድርገ ውላቸው ነበር:: እናንተም ቃለ መጠይቁን በሚ ገባ ከተከታተላችሁ በኋላ ከስር በተሰጡት ጥያቄ ዎች ላይ ተወያዩ::

**ሶስና፣** የት ተወልደው አደጉ?

**ወ/ሮ ጣይቱ፣** ተወልጄ ያደኩት ጋይንት በተባለ ሥፍራ ነው::

**ከድር፣** የቤት እመቤት እንደመሆንዎ ምን ምን ሥራዎችን ያከናውናሉ?

**ወ/ሮ ጣይቱ፣** አብዛኛውን የቤት ውስጥ ሥራ ማለትም ልጆች መንከባከብ፣ ቤት ማጽዳት፣ ምግብ ማዘጋጀትና የመሳሰሉትን አከናውናለሁ::

**ሶስና፣** ይህንን ሥራ በሚያከናውኑበት ወቅት የሚገጥምዎት ችግር ካለ ቢነግሩን?

**ወ/ሮ ጣይቱ፣** በተለይ ቀደም ባለው ወቅት ትልቁ ችግር የቤት ውስጥ ሥራ የሴቶች ብቻ ተደርጎ መወሰዱ ነበር:: አሁንም ይህ አመለካከት ገና ሙሉ በሙሉ አልተወገደም::

**ከድር፣** ወንዶች በቤት ውስጥ ሥራ ላይ አይሳተፉም ማለት ነው?

**ወ/ሮ ጣይቱ፣** አዎን፤ አብዛኛውን የቤት ውስጥ ሥራ የምንሰራው እኛ ሴቶች ነን::

**ሶስና፣** የወንዶች ተግባር ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ጣይቱ፣** የኔን ቤተሰብ ብትመለከቱ፣ የምንተዳደረው በግብርና ሥራ ነው:: ባለቤቴና ወንዶች ልጆቼ በቤት ውስጥ ሥራ ብዙም አይሳተፉም::

**ከድር፣** በአካባቢያችሁ ሴቶች በርካታ ሥራና ከባድ ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው?

ወ/ሮ ጣይቱ፣ አዎ፣ የቤቷ ሥራ ብዙ ነው:: የቤቱን አባወራ ሥራ እርዳኝ ብሎ የመየቅ ልምዱና እድሉ ብዙ የለም::
ሶስና፣ ይህን ሁኔታ እንዴት ማስተካከል የሚቻል ይመስሎታል?
ወ/ሮ ጣይቱ፣ የወንዶችና የሴቶች እኩልነት እንዲከበር በማድረግ፣ ሕብረተ ሰቡን ስለ እኩልነት በማስተማር፣ እንዲሁም ለሴት ልጆች የበለጠ የመማር እድል እንደያገኙ በማድረግ ነው::
ሶስና፣ ፈቃደኛ ሆነው ለሰጡን ቃለ መጠይቅ እናመሰግናለን::
ወ/ሮ ጣይቱ፣ እኔም እድሉን ስለሰጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ::

**መልመጃ 9**

***ከላይ የቀረበውን ቃለ መጠይቅ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. የየራሳችሁን ቤተሰብ ከላይ ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ጋር ስታነፃጽሩት ምን ይመስላል? ተመሳሳይነቱንና ልዩነቱን አስረዱ::
2. ወ/ሮ ጣይቱ ብቻቸውን ይህን ሁሉ ሥራ ማከናወናቸው ቤተሰባቸውን ይጠቅማል ወይስ ይጐዳል? ለምን?
3. የወ/ሮ ጣይቱ ባለቤት በቤት ውስጥ ሥራ ለመሳተፍ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? ልጆችስ?

ሴቶች የሕብረተሰቡ ግማሽ ስለሆኑ መብቶቻቸውን ሁሉ ማክበርና እኩልነታቸውንም መቀበል ጠቃሚ ነው:: ሁሉም ዜጐች የሴቶችን እኩልነት የማይቀበል አመለካከትና ድርጊትን መታገልና የሴቶችን የእኩልነት መብት መደገፍ ይጠበቅባቸዋል::

| ሴቶች በአካላዊም ሆነ በአእምሮአዊ ብቃታቸው ከወንዶች እኩል ናቸው:: |
|---|

የፆታ እኩልነት ማለት ወንድና ሴት በማንኛውም ሁኔታና የሥራ መስክ እኩል መሆን ማለት ነው:: ለምሳሌ በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በእርሻ ሥራ፣ በከብት እርባታ፣ በንግድና በሌሎች ኃላፊነቶችም ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው::

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

?

1. በተለምዶ በአካባቢያችሁ የሴትና የወንድ ናቸው የሚባሉት ሥራዎች የትኞቹ ናቸው?
2. ሴቶች የሚሠሩትን ሥራ ወንዶች መሥራት ይችላሉን?
3. በተለምዶ የወንዶች ተብለው የሚገመቱትን ሥራዎች ሴቶች ሲሠሩ ይችላሉን?

## 3.4.2 በትምህርት ቤት የሴትና የወንድ ተማሪዎች የእኩልነት መብት መገለጫዎች



*ሥዕል 3.4 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ*

- ከሥዕሉ ምን ትገነዘባችሁ?
- በትምህርት ቤት ውስጥ የወንድና የሴት ተማሪዎች የእኩልነት መብት መከበሩ በምን ይታወቃል?

ሴትና ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሁሉም መብቶች እኩል ናቸው:: ለምሳሌ በተጓዳኝ ክበባት ውስጥ የመሳተፍ፣ በተማሪዎች ምክር ቤት አመራር እኩል ውክልና የማግኘት እና የመሳሰሉት መብቶች ሊከበሩላቸው ይገባል::

በትምህርት ቤት ውስጥ የሴትና የወንድ ተማሪዎች የእኩልነት መብት በተግባር እንዲውል ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ቤት አመራር አካላት፣ ወላጆችና መንግሥት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው::

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በክፍላችሁ ውስጥ ስንት ሴት ተማሪ ዎች አሉ? የወንድ ተማሪዎችስ ቁጥር ስንት ነው? የየትኛቹ ቁጥር ይበል ጣል?
2. በክፍላችሁ ውስጥ ለሴት ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ይመስላች ኋል? በቡድን በመወያየት አስረዱ፡፡
3. የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቁጥር እን ዲመጣጠን ምን መደረግ አለበት ትላ ላችሁ? የተመጣጠነ ከሆነስ ቀጣይነት እንዲኖረው ከትምህርት ቤታችሁና ከቤተሰቦቻችሁ ምን ይጠበቃል?

## 3.5 የባህል እኩልነት

### 3.5.1 የባህል እኩልነት ምንነት





*ሥዕል 3.5 የተለያዩ ሕዝቦች ባህል*

- *ተማሪዎች ከላይ ከምትመለከቷቸው ሥዕሎች ምን ተረዳችሁ?*

ባህል የሰው ልጆች አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤን የሚገለጹ ድርጊቶችን የሚያካትት ነው፡፡ የባህል መገለጫ ከሆኑት መካከል ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ አነጋገር፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ የደስታና የሀዘን አገላለፅ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ባህሎች አሉ፡፡ ሁሉም ባህሎች እኩል ናቸው፡፡ እነዚህ ባህሎች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ በሰው ልጅ የዕድገት ደረጃና የአኗኗር ሁኔታ፣ እንዲሁም በሚፈጠሩ አስገዳጅ ሁኔታ ዎች ሊለወጥ ይችላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገ ራችን የሚገኙ ባህሎች ሁሉ እኩልነታቸው በሕገ መንግሥቱ የተከበረ ነው፡፡

**መልመጃ 12**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ባህል ማለት ምን ማለት ነው?
2. የባህል እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ የባህልን እኩልነት ማክበር ነው:: ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና ታሪካቸውን የመጠቀምና የማበልፀግ እኩል መብት አላቸው:: በመሆኑም ሕዝቦች አንዳቸው የሌላውን ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ሊማሩ፣ ሊያውቁና ሊያከብሩ ይገባል:: በእኩልነትና በመፈቃቀድም ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነት ሊዳብር ይገባል:: ስለዚህ ባህልን ማሳደግና መጠበቅ የሚያስፈልገው ቋንቋችንን፣ ታሪካችንና ጠቃሚ የአኗኗር ዘይቤዎቻችንን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ነው::

**መልመጃ 13**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. በአካባቢያችሁ የሚታዩትን ባህላዊ መገለጫዎች ዘርዝሩ::
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ጠቃሚና ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለዩ:: በመቀጠልም ከዚህ በታች የተመለከተውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ አሥፍሩ::

| ጠቃሚ ባህላዊ መገለጫዎች | ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

### 3.5.2 ባህልን የማዳበር አስፈላጊነት

- የራስን ባህል ማዳበር ምን ጥቅም ይሰጣል?

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ ከሚታዩ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል:

*ሀ. በጐጂነት የሚፈረጁ*

- የሕፃናትን እንጥል መቁረጥ፣
- የሴት ልጅ ግርዛት፣
- ያለዕድሜ ጋብቻ፣
- በለቅሶና በሀዘን ወቅት ገላን ማቁሰልና ራስን ማጐሳቆል፣
- የሕፃናትን ጉሮሮ ማስቧጠጥ፣
- አካልን ተገቢ ባልሆነ መልኩ በስለታም ነገር መቁረጥ፣
- ለሠርግና ለድግስ ከአቅም በላይ ወጪ ማውጣት::

*ለ. ለልማትና ለዕድገት ከሚጠቅሙ ድርጊቶች መካከል፣*

- ሥራን ተጋግዞ በጋራ መሥራት/ደቦ፣ ወንፈል/፣
- እንግዳ ተቀባይነትና ታላቅን አክባሪነት፣
- እድር /በሐዘን ጊዜ የመረዳጃ ዘዴ/ እና እቁብ /የቁጠባ ዘዴ/፣
- የተቸገሩ ወገኖችን አቅም በፈቀደ መርዳት ወዘተ. ናቸው::

**የቡድን ሥራ**

በአካባቢያችሁ በሴት ተማሪዎችና በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ጐጂ ድርጊቶችንና የሚያስከትሉትን የጤንነት ችግሮች በቡድን በመሆንና መረጃ በማሰባሰብ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ጽሁፍ አቅርቡ::

## 3.6 የአካል ጉዳተኝነት

### 3.6.1 የአካል ጉዳተኝነት ምንነት

- የአካል ጉዳተኝነት ማለት ምን ማለት ነው?
- ለአካል ጉዳተኝነት የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ዘርዝሩ::

የአካል ጉዳተኝነት ማለት አንድ በሙሉ ጤንነትና ሁኔታ ላይ ያለ ሰው ሊያከናውነው የሚገባውን ተግባር ማከናወን አለመቻል ነው:: በሌላ መልኩ አካል ጉዳተኝነት ማለት አንድን ተግባር ወይም እንቅስቃሴ በተለያዩ ምክንያት መፈጸም አለመቻል ነው::

በኢትዮጵያ ውስጥ በርከት ያሉ የአካል ጉዳተኞች ይገኛሉ:: አካል ጉዳተኞች በትምህርት ቤት፣ ሥራ ቦታ፣ በማሕበራዊ ኑሮና በመሳሰሉት ሲገለሉ ይታያል:: እንደዚህ ዓይነቱ የአካል ጉዳተኞችን የማግለልና የማራቅ ሂደት በሕግ የተከለ ከለና ለሀገር እድገት የማይጠቅም ነው::

አካል ጉዳተኞች ሙሉ ክብር አላቸው፡፡ እንደ ማንኛውም ዜጋ ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም መንግሥትና ሕብረተሰቡ መብታቸውን ማክበርና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**መልመጃ 14**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ለአካል ጉዳተኞች ምን ምን ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል?
2. አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ሊያከናውኑ የሚችሉት ምን ምን ሁኔታዎች ሲመቻችላቸው ነው?

### 3.6.2 የአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጓቸው ድጋፎች

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የአካል ጉደተኞች ምን ምን ድጋፎች ይሻሉ?

የአካል ጉዳተኞች ከመንግሥት፣ ከሕብረተሰቡና ከበጐ አድራጊ ድርጅቶች ድጋፎች ሊደረጉላቸው ይገባል፡፡ ከነዚህም መካከል በሚኖሩበት አካባቢና በትምህርት ቤቶች ፍቅርና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንዲሁም የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ማየት ለተሳናቸው ወገኖች የብሬል መጽሐፍትን ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ የአካል ጉዳተኞች መብቶቻቸው ከተከበሩላቸውና አስፈላጊውን ድጋፍ ካገኙ፣ ሀገርን ከድህነትና ከኋላቀርነት ለማላቀቅ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፆ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡



*ሥዕል 3.6 አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው አምራች ዜጎች ናቸው*

**መልመጃ 15**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. በትምህርት ቤታችሁ የአካል ጉዳተኞች ካሉ እነርሱን ለመርዳት ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ተደርጓል?
2. ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ በማድረግ ረገድ የእናንተ ሚናና ኃላፊነት ምን ሊሆን ይገባል?

## 3.7 የሃይማኖት እኩልነት መብት ምንነት

- የሃይማኖት እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

ሃይማኖት ማለት ፈጣሪ አለ ብሎ ማመን ነው፡፡ በቃላት ሊገለጽ የማይችለውንና ከመታወቅ የሚያልፈውን አምላክ/ፈጣሪን መፍራትና ማምለክ ሃይማኖት ይባላል፡፡ አብዛኞቹ በአለም ላይ ያሉ ሃይማኖቶች የሚያስተምሩት መልካም ሥነምግባርንና ለሰው ልጆች መልካም ወይም በጎ የሆነውን ነገር ማድረግን ነው፡፡

የሕዝቦች የማንነታቸው መገለጫ ከሆኑት ሰብኣዊ መብቶች መካከል አንዱ የፈለጉትን ሃይማኖት የመያዝና የማራመድ መብት ነው፡፡ የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል መብት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መብቶች መካከል ይመደባል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ማንኛውንም ሃይማኖት የመከተል

መብት በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድን ሃይማኖት ወይም እምነት በሌላው ላይ በሀይል ለመጫን መሞከርንና የኃይል ተጽኖን ከልክሏል፡፡

የሃይማኖት እኩልነት መብት ሲባል የሀገራችን ማንኛውም ዜጋ የመሰለውን እምነት የመያዝ፣ የሌላውን ዜጋ እምነት ማክበርና በእምነቱ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርግ አለመከልከል ማለት ነው፡፡ አንዱ ዓይነት እምነት የተከበረና የበላይ፣ የሌላው እምነት የተናቀና የበታች ያለመሆን እኩልነት የሃይማኖት እኩልነት መብት ይባላል፡፡

**መልመጃ 16**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. ሃይማኖት ምንድን ነው?
2. የሃይማኖቶች እኩልነት መብት ስንል ምን ማለታችን ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የእኩልነት መብት የሰው ልጆች መሠረታዊ መብት ነው፡፡ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ፍላጐት ሲያከናውኑ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተ ግባር ይረጋገጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሕዝቦች በራሳቸው ቋንቋ ሲገለገሉ፣ ባህላቸውን ሲያበለጽጉና ታሪካቸውን ሲንከባከቡ የእኩልነት መብቶቻቸው ይከበራሉ፡፡

እኩል የትምህርት ዕድል የማግኘት መብት በተግባር መዋሉ በሀገራችን እድገትና ልማትን ለማፋጠን ያስችላል፡፡ የፆታ እኩልነት በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የአድሎ አሠራርና ጉጂ ልማድ ለማስቀረት የሚጠቅም መብት ነው፡፡ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተገቢው ሁኔታ ማክበርና ማስከበር ለሁላችንም እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ እንክብካቤና ፍቅርን ልናሳያቸው ይገባል፡፡ የሃይማኖት እኩልነት በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያችን የተረጋገጠ የዜጎች መብት ነው፡፡ ስለሆነም አንዱ የሌላውን ሃይማኖት በማክበር በሰላም አብሮ መኖር የሚገባ ሲሆን ለሀገር እድገትም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**መብት፣** አንድ ሰው ሊያገኘው የሚገባ ማንኛውም ጥቅም፣ አገልግሎትና ሙሉ ክብር ወዘተ።

**ባህል፣** የአንድን ሕዝብ ቋንቋው፣ ሃይማኖቱ፣ አኗኗሩ፣ ልምዱ ወዘተ።

**ብሔር፣** ብሔረሰብና ሕዝብ፣ የጋራ ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክ ያለውና በአንድ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ/ ማህበረሰብ።

**ብሬል፣** ማየት የተሳናቸው ወገኖች እንደ ወረቀት ለመጻፊያና ለማንበቢያ የሚገለገሉበት።

**አድልዎ፣** ሆን ብሎ አንዱን ወገን በመጉዳት ሌላውን ወገን የመጥቀም ዝንባሌ፣ ድርጊት።

**እኩልነት፣** ሳይበላለጡ ትክክለኛውን ወይም ተገቢውን ደረጃ/ድርሻ ማግኘት።

**ወንፈል፣** በገጠር አካባቢ በየተራ የሚደረግ የመረዳዳት ሥራ።

**ደቦ፣** ብዙ ሰዎችን እያበሉ፣ እያጠጡ ወይም በአንድነት እየሆኑ በመረዳዳት መሥራት።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።

1. ባህል የሰው ልጆችን ከፊል የአኗኗር ሁኔታ የሚገልጽ ነው።
2. ሥራን ተጋግዞ መሥራት በሀገራችን የተለመደ ጠቃሚ ባህል ነው።
3. ያለዕድሜ ጋብቻ ጠቃሚ ከሆኑ ድርጊቶች መካከል ልንመድበው እንችላለን።
4. ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የዕኩልነት መገለጫ ነው።
5. የፆታን እኩልነት በወንድና በሴት መካከል ልዩነትና አድሎ እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው።

## II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የሴት እና ወንድ እኩል መሆን፣ | ሀ. ታላላቆችን ማክበር። |
| 2. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ማንነት መገለጫ፣ | ለ. ቋንቋ። |
| 3. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ | ሐ. የሃይማኖት እኩልነት። |
| 4. መልካም ሥነምግባር፣ | መ. የፆታ እኩልነት። |
| 5. ሁሉም ሰው የራሱን ሃይማኖት የመከተል መብት፣ | ሠ. አካል ጉዳተኞች። |

## III. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት መካከል የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ራስን በራስ ማስተዳደር የሚያስገኘው ጥቅም የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. በአካባቢያቸው ልማትን ለማምጣት፣
   ለ. የሕዝቡን መብት ለማስከበር፣
   ሐ. ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ተቻችሎ ለመኖር፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።
2. ከሚከተሉት መካከል በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች እኩልነት መብትን የማይገልጸው የትኛው ነው?
   ሀ. በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ጥያቄ መጠየቅ፣
   ለ. በልዩ ልዩ ክበባት ውስጥ መሳተፍ፣
   ሐ. በትምህርት ሰዓት ጨዋታ መጫወት፣
   መ. ተማሪዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሃሳብ መስጠት።

3. የሴቶችን ሰብዓዊ መብትና ክብር የሚነካ ጐጂ ድርጊት የሆነው _________ ነው።
   - ሀ. ያለዕድሜ ጋብቻ፣
   - ሐ. ወንድ የሚሠራውን ሥራ መሥራት፣
   - ለ. የሴት ልጅ ግርዛት፣
   - መ. ሀ እና ለ።
4. ለአካል ጉዳተኞች ሊደረጉላቸው ከሚገቡ ድጋፎች መካከል ያልሆነው______
   - ሀ. ፍቅርና እንክብካቤ፣
   - ሐ. የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣
   - ለ. ማግለልና መድሎ፣
   - መ. በእኩል መብታቸውን ማክበር።
5. የአንድ ሕዝብ የባህል መገለጫ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
   - ሀ. አለባበስ፣
   - ሐ. የደስታና የሀዘን አገላለፅ፣
   - ለ. አመጋገብ፣
   - መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሐረግ ሙሉ፡፡

1. በሀገራችን ገጠር አካባቢዎች በየተራ የሚደረግ የመረዳዳት ሥራ ________ይባላል፡፡
2. ህፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከ________፣ ________እና ________ ሊማሩት ይችላሉ፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ተማሪዎች በራሳችሁ ቋንቋ መማራችሁ ያስገኘላችሁን ጥቅሞች ጥቀሱ፡፡
2. በትምህርት ቤታችሁ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በአጭሩ አስረዱ፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ፍትሐዊነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የፍትሕን ምንነት ትረዳለህ/ትረጂያለሽ::
- ፍትሕ ሊጣስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች እና የአድሎዊ አሠራር ምንነትን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ::
- የማሕበራዊ ተቋማትን ምንነትና አስፈላጊነት ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የፍትሐዊ አሠራሮች መኖር ለአካባቢው ሠላም መስፈን አስፈላጊ መሆኑን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ::
- የግብር ምንነትን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::

## 4.1 ፍትሕ

### 4.1.1 የፍትሕ ምንነት

- ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው? የምታውቁትን በወረቀት ላይ በማስፈር ተራ በተራ ለሌሎች አንብቡላቸው::



*ሥዕል 4.1 ሚዛን*

- ያጋደለው ሚዛን ምንን ይገልፃል?
- የተስተካከለው ሚዛንስ ምንን ያመለክታል?
- ከነዚህ ሚዛኖች ምን ትረዳላችሁ? የትኛውን ሚዛን ትመርጣላችሁ? ለምን?

**ፍትሕ** በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትክክለኛ ፍርድ ወይም ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ መስጠትን የሚያመለክት ሀሳብ ነው:: በሌላ አገላለፅ ፍትሕ ከአድሎ ወይም ከወገንተኝነት የፀዳ ዳኝነት ወይም ምስክርነት መስጠትን ይገልፃል:: ፍትሕ ለየትኛውም ወገን ሳያዳሉ እውነተኛ ሀሳብ መሰንዘርን፣ እውነት መናገርን፣ እውነትን መሰረት በማድረግ መሥራትን ያመለክታል::

**«ፍትሕ ማለት ትክክለኛ ፍርድ ተገቢነት ሀቅ፣ ትክክል መሆን ማለት ነው::»**

**መልመጃ 1**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::***

1. በቤተሰብ አስተዳደር ፍትሕን የሚገልፁ ድርጊቶችን አብራሩ::
2. በትምህርት ቤት ውስጥ ፍትሕን የሚገልፁ ድርጊቶችን ዘርዝሩ::

### 4.1.2 የፍትሕ አስፈላጊነት

- በእናንተ ደረጃ ፍትሕ ያስፈልጋል የምትሉባቸውን ጉዳዮች ዘርዝሩ::
- ፍትሕ ለሰው ልጆች ያስፈልጋል ብላችሁ ታምናላችሁ? ምክንያቶቻችሁን ዘርዝሩ::

**የነፍቅር ቤተሰብ**

የነፍቅር ቤተሰብ በአካባቢው ሕብረተሰብ በመልካም የቤተሰብ አስተዳደር በምሳሌነት ይጠራል:: ቤተሰቡን ለመልካም ስም ካበቁት ጉዳዮች መካከል ፍትሕ የተሞላበት ቤተሰባዊ አስተዳደራቸው ነው:: ለዚህም የሚከተሉት ነጥቦች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ::

የፍቅር ወላጆች ገንዘባቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ:: ስለልጆቻቸው የትምህርት ጉዳዮች በመመካከር እና በመወያየት ይወስናሉ:: እናሳድጋለን ብለው በተረከቧት የዘመድ ልጅና በልጆቻቸው መካከል ልዩነት ሳይፈጥሩ አንድ ትምህርት ቤት ያስተምሯቸዋል::

ከትምህርት ቤት ሲመለሱም ለሁሉም ልጆች እንደአቅማቸው ተመጣጣኝ እና እኩል የሥራ፣ የጥናትና፣ የጨዋታ ጊዜ ተመድቦላቸዋል:: እነ ፍቅርም በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ በነፃነት ሀሳብ ወይም አስተያየታቸውን ይሰጣሉ:: የሚፈልጉትንም ጥያቄ ይጠይቃሉ:: ልጆቹም በትምህርታቸው ታታሪዎችና ጎበዞችናቸው:: አልፎ አልፎ በጓደኞቻቸው መካከል በአጋጣሚ ቅራኔዎች ሲፈጠሩ አድሎ የሌለበት መፍትሄ ይፈልጋሉ።

## መልመጃ 2

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በነፍቅር ቤተሰብ አስተዳደር ፍትሐዊ አሠራርን የሚገልፁ ተግባራትን ዘርዝሩ::
2. እነፍቅርን ታታሪና ጎበዝ ተማሪዎች ያደረጋቸው ምንድን ነው?
3. ፍትሕ የሰፈነበት ቤተሰባዊ አስተዳደር ያሉትን ጥቅሞች ዘርዝሩ::

## የላሎ ቤተሰብ

የነላሎ ቤተሰብ ከነፍቅር ቤተሰብ በተለየ ሁኔታ የሚተዳደር ነው:: ቤተሰቡ ከበቂ በላይ የገቢ ምንጭ ቢኖረውም ባለው ንብረት ላይ ሁሉ ልዘዝ የሚሉት የላሎ አባት አቶ ሽብሩ ብቻ ናቸው:: እሳቸው ይደረግ: ያሉት ሁሉ መፈፀም አለበት:: የነላሎ እናት ምንም ዓይነት ሀሳብ ቢሰጡም የሚያዳምጣቸው የለም:: አቶ ሽብሩ ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ሳያማክሩ አሳድጋለሁ አስተምራለሁ ብለው የተረከቧቸውን የዘመድ ልጆች የቤት ውስጥ አገልጋይ አድርገዋቸዋል::

ከዚህም በላይ አቶ ሽብሩ ስለወንዶች ልጆቻቸው ትምህርት ጉዳይ እንጂ ስለ ሴቶች ልጆቻቸው ደንታ የላቸውም:: ወንዶቹም ቢሆኑ በአግባቡ ክትትል ስለማይደረግላቸው በትምህርታቸው ደካሞች ናቸው::

በዚህ ፍትሕ በጎደለው ቤተሰባዊ አስተዳደር የተነሳ በቤተሰቡ ውስጥ ሠላም፣ ፍቅርና ስምምነት የለም:: ልጆቹም በትምህርት ቤትም ሆነ በሰፈር ውስጥ በረባሽነት የሚታወቁ ሆኑ::

የላሎ እናት በአቶ ሽብሩ ከፍተኛ ተፅእኖ ተማረው ቤታቸውን ጥለው ከወጡ ቆይተዋል:: ከሰሞኑ የመኖሪያ ቤታቸው ተሽጦ ንብረት ክፍፍል ላይ መሆናቸው በሰፊው ይወራል::

## መልመጃ 3

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በቤተሰብ አስተዳደር ውስጥ ፍትሐዊ ያልሆነ አሠራርን የሚገልፁ ተግባራትን ጥቀሱ::
2. የቤተሰብ አስተዳደር ፍትሐዊ አለመሆኑ ልጆቹ ምን ዓይነት ባህሪያት እንዲኖራቸው አደረገ?
3. በቤተሰብ ውስጥ ፍትሐዊ አስተዳደር ሲጓደል የሚጎዳው ማን ነው?
4. ከላይ ከተጠቀሱት ቤተሰቦች መካከል የየትኛው ቤተሰብ አባል ብትሆኑ ትመርጣላችሁ? ለምን?

ፍትሕ የሰዎች ሕይወትና ኑሮ መልካም እንዲሆን በማድረግ ያለው ጠቃሜታ ከፍተኛ ነው:: ፍትሕ በሁሉም የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ለምሳሌ በትምህርት ቤት፣ በቀበሌና በቤተሰባዊ ኑሮ አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: በሰዎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነቶችና መድሎ እንዳይፈጠር ያደርጋል:: ልዩነቶችም ካሉ እንዲስተካከሉ ማድረጊያ መሳሪያ ነው::

በጓደኝነት ደረጃ ፍትሕ የሰዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት ሚዛናዊ እንዲሆን በማድረግ አንዱ የበታች ሌላው የበላይ እንዳይሆን ያደርጋል:: ከጓደኞቻችሁ ጋር ተስማምታችሁ የምታጠኑትና

ወይም የምትጫወቱት በመካከላችሁ ፍትሕዊ ግንኙነት በመኖሩ እንደሆነ ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ:: ፍትሕ አንዱ ተጎጂ ሌላው ያላግባብ ተጠቃሚ እንዳይሆን በማድረግ የዜጎች መብት እንዲከበር ያደርጋል::

በቤተሰብ ደረጃ ፍትሕ ቤተሰባዊ ኑሮ ሠላም የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የወደፊት ሕይወት እንዲሻሻል ያደርጋል::

በሀገር ደረጃ ፍትሕ በሕብረተሰብ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችንና ቅራኔዎችን በሠላማዊ መንገድ በመፍታት አድሏዊ አሠራሮችን ይከላከላል:: ዜጎች ሀብትና ንብረታቸውን ያለአግባብ በሕገወጦችና በዘራፊዎች እንዳይነጠቁ ዋስትና ይሰጣል:: ፍትሕ ለሕብረተሰብ እድገት፣ ብልፅግና እና ልማት መሠረት ነው::

ዜጎች በሀገራቸው በእኩልነትና በነፃነት የመኖር፣ የመማርና የመሥራት መብታቸውን ያረጋግጣል:: ፍትሕ በሀገር ላይ ሠላም እንዲሰፍን ያደርጋል:: በዚህም ህጻናት፣ ሴቶች፣ አቅመ ደካሞችና እናቶች ጥቃት እንዳይደርስባቸው ይከላከላል::

**ፍትሕ ሠላምን የማስፈኛ ፡ ለእድገት ለብልፅግና እና ለሕዝቦች እኩልነትና የእርስ በእርስ ግንኙነት ማጠናከሪያ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል::**

**መልመጃ 4**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ::*

1. ፍትሕ በሚከተሉት አካባቢዎች ያሉትን ጥቅሞች ዘርዝሩ::
   ሀ. በቤተሰባዊ ሕይወታችሁ፣
   ለ. በሰፈር ግንኙነት ደረጃ፣
   ሐ. በትምህርት ቤት፤
2. ከላይ በተቀመጡት አካባቢዎች ልትፈፅሚቸው የምትችሏቸውን የፍትሕ ድርጊቶች አስረዱ::

## 4.2 የፍትሕ አሠጣጥ ሂደትና በአካባቢያችን የሚገኙ የፍትሕ አካላት

### 4.2.1 የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት በማሕበረሰብ ደረጃ

- በክፍል ውስጥ በደል ቢደርስባችሁ ድርጊቱን የምታሳውቁት ለማን ነው?
- በአካባቢያችሁ በሰዎች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ አለመግባባቱን የሚያስወግዱ ሰዎች አሉ? እንዴት ነው አለመግባባቱን የሚያስወግዱት?

**አቶ በልሁ "ብልሁ"**

አቶ በልሁ በአካባቢያቸው ፍትሐዊ ውሣኔ በመስጠት እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው:: የተጣሉ ሰዎችን በማስማማት በሰፈር ውስጥ ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ሠላም እና እርቅ እንዲኖር በማድረግ የሚወዳደራቸው የለም:: አቶ በልሁ ይህን ተግባር ሲያከናውኑ አንዳንድ ጊዜ ብቻቸውን በሌላ ጊዜ ከሌሎች ጋር በመሆን ነው:: አቶ በልሁ በማስታረቅ ሥራቸው ስኬታማ የሆኑት ተአምረኛ ወይም የተለዩ ፍጡር ሆነው አይደለም::

የአቶ በልሁ ዋናው የማስማማት ሚስጢር ተገቢ የፍትሕ አሰጣጥ መንገድ ወይም ዘዴን በመከተላቸው ነው:: አቶ በልሁ መጀመሪያ ባለጉዳዮች ወደ እሳቸው ሲመጡ፣ የችግሩን ወይም የአለመግባባቱን መንስኤ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። የሁለቱንም ወገኖች ሀሳብ ያዳምጣሉ:: የችግሩን ምንነት በሚገባ ከተረዱ በኋላ ለማንም ያላዳላ ውሳኔ ይሰጣሉ:: በዚህ የተነሳ አቶ በልሁ የሚሰጡት የሽምግልና ውሳኔ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል::

**መልመጃ 5**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. የአቶ በልሁ አብዛኛው ውሳኔዎች ስምን ተቀባይነት ያገኙሉ? ሦስት ነጥቦችን ጥቀሱ፡፡
2. የአቶ በልሁን የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቶች ዘርዝሩ? ከአቶ በልሁ ዘዴዎች ምን ትማራላችሁ?
3. ከጓደኞቻችሁ መካከል ጨዋታችሁን በዳኝነት እንዲመራ የምትመርጡት ምን ዓይነት ባህሪ ያለውን ልጅ ነው? ስምን?

ፍትሕ በተለያዩ ቦታዎች፣ ፍትሕ በተለያዩ አጋጣሚዎች እና ጉዳዮች ላይ ይሰጣል፡፡ የፍትሕ አሰጣጥ ሁኔታ ከሰዎች የእለት ከእለት ኑሮ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ በትምህርት ቤት፣ በመጫወቻ ቦታዎችና በቤት ውስጥ እለት በእለት የሚሰጡ ውሳኔዎችን አስታውሱ፡፡ እነዚህ ሁሉ ውሳኔዎች ፍትሕን የሚገልፁ ድርጊቶች ናቸው፡፡ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት ለተለያዩ ቅራኔዎች ወይም ችግሮች ተገቢ መፍትሄ ወይም ውሳኔ የመፈለግ አሠራርን መከተልን ያመለክታል፡፡ እነዚህን መሰል ፍትሀዊ የውሳኔ አሠጣጥ ድርጊቶች የራሳቸው የሆኑ ሂደቶች አሏቸው፡፡

በማንኛውም የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት መታወቅ ያለባቸው መሠረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ እነሱም፡-
- የችግሩን መንስኤ በአግባቡ ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣
- ጉዳዩን በሚገባ መረዳት፣
- በእውነት ላይ ተመስርቶ ሳያዳሉ ተገቢ ውሳኔ መስጠት ናቸው፡፡

**መልመጃ 6**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*


1. የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቶች ምን ምን ነጥቦችን ይይዛሉ?
2. በአካባቢያችሁ ፍትሕን የሚሰጡ አካላት አለመግባባቶችን እንዴት ይፈታሉ?

## 4.2.2 የፍትሕ አካላት

- በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያ አካባቢና በመማሪያ ክፍል ፍትሕን የሚሰጡ አካላትን ጥቀሱ፡፡
- እናንተ በቤታችሁ፣ በትምህርት ቤታችሁ፣ ወይም መማሪያ ክፍላችሁ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ምን ዓይነት ኃላፊነት ተወጥታችሁ ታውቃላችሁ?

**የፍትሕ አካላት** ማለት በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን ግጭቶች ወይም አለመግባባቶችን ለማስወገድ መፍትሄ የሚሰጡ አካላት ማለት ነው። ይህን ዓይነት ኃላፊነት የሚወጡ የፍትሕ አካላት ባህላዊ እና ዘመናዊ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህ አካላት በህብረተሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩ የፍትሕ ችግሮች ላይ ውሳኔ በመስጠት ያገለግላሉ፡፡

### *ሀ. ባህላዊ የፍትሕ አካላት*



*ሥዕል 4.2 ባሕልዊ የፍትሕ አሰጣጥ*

- ከላይ ካለው ሥዕል ምን ትረዳላችሁ?
- በአካባቢያችሁ የተጋጩ ሰዎችን የሚያስማሙ አካላትን ዘርዝሩ፡፡

ባህላዊ የፍትሕ አካላት፡- ከጥንት ጀምሮ በሀገራችን የሚኖሩ ሕዝቦች በውስጣቸው የሚፈጠሩ አለመግባባቶች እና በደሎች መፍትሄ ለመስጠት ባህላዊ አሰራሮችን ይከተላሉ:: እነዚህ ባህላዊ የፍትሕ ተቋማት በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ስያሜ አላቸው:: ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ የሚባሉ ሲሆኑ እነሱም በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ:: እነዚህም ተቋማት በቅርበት በመገኘት ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የፍትሕ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ:: የአቶ በልሁ “ብልሁ” ተግባር ለባህላዊ የፍትሕ አካል አንድ ምሳሌ ነው::

### ለ. ዘመናዊ የፍትሕ አካላት፣




*ሥዕል 4.3 የኢትዮጵያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*



*ሥዕል 4.4 የቀበሌ ጽ/ቤት*




*ሥዕል 4.5 የፖሊስ ጣቢያ*

- ከላይ የሚታዩትን ሥዕሎች በመመልከት የእያንዳንዱን ተቋም ተግባራት ዘርዝሩ::

ዘመናዊ የፍትሕ አካላት ዜጎች በመንግስት አካላትም ሆነ በሌሎች መድሎ እንዳይደርስባቸው ጥበቃ ያደርጋሉ:: ዜጎች የተለያዩ የፍትሕ ችግሮች ሲያጋጥማቸው ለነዚህ ተቋማት ያቀርባሉ:: አካላቱም ሕግና ደንብን ተከትለው ተገቢ መፍትሄ ይፈልጋሉ:: በሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ:: ከነዚህ ዘመናዊ የፍትሕ አካላት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

| የቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤቶች | ፖሊስ ጣቢያዎች | ፍርድ ቤቶች |
|---|---|---|
| በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፍትሕ ውሳኔ በመስጠት ሕብረተሰቡን ያገለግላሉ:: ከማንኛውም ዘመናዊ የፍትሕ አካላት መካከል በቅርበት የሚገኙ ናቸው:: | በአካባቢያችሁ የምታይዋቸው የፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች የሕብረተሰቡንና የእናንተን ደህንነት ይጠብቃሉ:: በዚህም ተግባራቸው የህብረተ ሰቡን ሠላምና ፀጥታ የሚያስከብሩ ዘመናዊ የፍትሕ አካላት ናቸው:: | አንድ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ የፍትሕ አካላት መካከል ፍርድ ቤቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ:: ሰዎች ችግሮች ሲያጋጥ ሚቸውና በደሎች ሲደርሱ ባቸው ወዘተ ፍትሕ የሚሰጡባቸው ተቋሞች ናቸው:: |

መልመጃ 7

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. ፍትሕን በማስፈኑ ሂደት የሚከተሉትን አካላት ተግባር ዘርዝሩ::
   ሀ. ቀበሌያችሁ፣ ለ. ፍርድ ቤቶች፣
   ሐ. ፖሊስ ጣቢያ፣
2. የፖሊስ አባላት በአካባቢያችሁ ባይኖሩ ሲደርሱ የሚችሉ የፍትሕ ችግሮችን ዘርዝሩ::

## 4.3 ፍትሕ ሲጣስ የሚችልባቸው ሁኔታዎች

### 4.3.1 ሕግን አለማክበር

- የትምህርት ቤታችሁን ሕግ ማክበር ያለበት ማን ነው?
- ሕጉን የማያከብር ካለ ምን ይሆናል? ምን ዓይነት እርምጃዎች መውሰድ ይበጃል ትላላችሁ?

**“የቻነር መንደሮች” /*ክፍል አንድ*/**

የቻነር መንደሮች ለረጅም ዘመናት ለአጎራባች ሕዝቦች የፍቅርና የሠላም ምሳሌዎች ነበሩ:: ታዋቂ ካደረጓቸው ጉዳዮች መካከል ሁሉም ሕብረተሰብ ያለምንም ልዩነት የመንደሮቻቸ ውን ሕግ በሚገባ በማክበራቸው ነበር:: በተጨ ማሪም የፍትሕ ሥርዓታቸው ከአድሎ የፀዳ አሠራርን መሰረት ያደረገ ነበር:: ለሚፈጠሩ ግጭቶችና በደሎች በጊዜ ሚዛናዊ መፍትሄ የሚሰጥ አሠራርን ይከተላሉ:: በዚህም ምክንያት ቻነር “የፍትሕ መንደር፣ የፍትሕ ሀገር” በመባል ስትሞገስ ኖራለች::

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በቻነር መንደሮች ሁኔታዎች እነደቀደሙት ጊዜያት አይደሉም:: በሕብ ረተሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ፍትሕን ሲያስጠብቁ የቆዩ ተቋማት የሚያከብራቸው ጠፉ:: ሕግና ደንብ መጣስ ከተጀመረ ቆይቷል:: የመንደሩ አስተዳዳሪ ዎች ከሕግና ሥርዓት ውጪ ውሳኔ መስጠት ጀመሩ::

ሕብረተሰቡ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግ ሎት የሚያገኘው በገንዘብና በትውውቅ ወዘተ... ሆነ:: የሚፈልጉትን ነገር በጉልበትና በገንዘብ ወይም በዘመድ ማግኘት የተለመደ አሠራር መሆን ከጀ መረ ቆየ:: ዝርፊያና የድብደባ ወንጀሎች በርክተ ዋል::

ወንጀለኞችም በቀላሉ በፀጥታ ኃይሎች የሚያዙ አልሆኑም:: ቢያዙም ወዲያውኑ ከእስር ይፈታሉ:: በሕዝቡ ላይ ለሚደርስ በደል እና ግፍ ተገቢ መፍ ትሄ የሚሠጥ ጠንካራ የፍትሕ አካል የለም:: የሕብ ረተሰቡ የጋራ ንብረቶች ለምሳሌ የእርሻና የቤት መሥሪያ ቦታዎች፣ ደኖች ወዘተ በግለሰቦች በመያዝ ላይ ናቸው:: የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የፍትሕ ተቋማት በመድሎና በባለሥልጣናት ተፅእኖ ሕግን እያዛቡ ይፈርዳሉ:: ነዋሪዎች የመንደሮቻቸው ሁኔታ እጅግ አሳስቧቸዋል:: ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ “ቻነር የፍትሕ መንደር” ምን ትሆን ይሆን?

**መልመጃ 8**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በቻነር መንደሮች ችግር የተፈጠረው በምን ምክንያት ነው? ተወያዩበት፡፡
2. ፍትሕን የጣሱ ድርጊቶች ናቸው የምትሏቸውን ዘርዝሩ፡፡

ፍትሕ እንዲጣስ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሕግን አለማክበር ነው፡፡ ሕግ ማለት ሁሉም ማክበር ያለበት ሥነ ሥርዓት እንደማለት ነው፡፡ በየትም ቦታ የሚገኝ ሕግ በዜጎች ሊከበር ይገባል፡፡ ሕግ በሁሉ ቦታና የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኛል፡፡ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በክፍል ውስጥ፣ በጨዋታ ቦታ፣ በሥራ ቦታ፣ ወዘተ. ሕግ አለ፡፡ የትምህርት ቤት ሕግ ወይም ሥርዓት በአግባቡ ካልተከበረ የትምህርት ሥራው ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተገቢ ደረጃ መከታተል ስለማይችሉ የወደፊት ሕይወታቸው ይበላሻል፡፡

እንዲሁም እያንዳንዱ ጨዋታ የራሱ የሆነ ሕግ አለው፡፡ ሕጉ በአግባቡ መከበር ይኖርበታል፡፡ ሕጉ በአግባቡ ካልተከበረ ጨዋታው መቋረጥ ብቻ ሳይሆን ሌላም የከፋ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡

በቤተሰብ ደረጃም መልካም ቤተሰባዊ አስተዳደርን የማይከተል ቤተሰብ ችግር ውስጥ መውደቁ የማይቀር ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል ያነበባችሁት የቻነር መንደሮች ታሪክ የዚህ ምሳሌ ነው፡፡ በሀገር ደረጃ የወጡ ሕጎች በዜጎች ሊከበሩ ይገባቸዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ፍትሐዊ አሠራር ሊኖር አይችልም፡፡ “ሕግ ሲጓደል ሀገር ይበደል” የሚለው አባባል በቀላሉ ይገልፀዋል፡፡

ሕግን ባለማክበር በግለሰብ፣ በሕብረተሰብና በሀገር ላይ ከፍተኛ የሆነ በደልና ጉዳት ይደርሳል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ለራሳቸው ለቤተሰባቸው፣ ለሀገራቸው ሰላምና እድገት ሲሉ ሕግን ሊያከብሩ ይገባል፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ የፍትሕ ችግሮች የሚከሰቱት ሰዎች ሕግንና ደንብን ባለማክበራቸው ነው፡፡

**መልመጃ 9**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች ስጡ፡፡***

1. በሚከተሉት ተቋማት ለፍትሕ መጣስ ምክንያት ይሆናሉ የምትሏቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ፡፡
   ሀ. በቤተሰብ ውስጥ፣
   ለ. በትምህርት ቤት፣
   ሐ. በክፍል ውስጥ፡፡
2. ሕግን አለማክበር በትምህርት ቤት እና በቀበሌ ደረጃ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ፡፡

### 4.3.2 አድሏዊ አሠራሮችን መፈፀም

- በሚከተሉት አካባቢዎች ይታያሉ የምትሏቸውን አድሏዊ አሠራሮች ዘርዝሩ።
  ሀ. በመማሪያ ክፍል፣
  ለ. በትምህርት ቤቶች፣
  ሐ. በቀበሌዎች።
- ሰዎች ለምን አድሎዊ አሠራሮችን ይፈፅማሉ? ምክንያት ናቸው የምትሏቸውን ነጥቦች ጥቀሱ፡፡

ፍትሕ እንዲጣስ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል ሁለተኛው አድሎአዊ አሠራር መፈፀም ነው፡፡ አድሎአዊ አሠራሮች የፍትሐዊ አሠራር ተቃራኒ ናቸው፡፡ አድሏዊ አሠራሮች በሕብረተሰብ ውስጥ ሲስፋፉ ፍትሕ ይጓደላል፡፡ አድሏዊ አሠራር ማለት ከሕግና ከሥርዓት ውጪ ሥራዎችን መሥራት ማለት ነው፡፡ አድሏዊ አሠራር ማለት ያላግባብ አንዱን የሚጠቅም ሌላውን የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም በሚል ሊገለፅም ይችላል፡፡

አንዳንድ ሰዎች በዝምድና፣ በቋንቋ፣ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በመቀራረብ ገንዘብ በመቀበል ወዘተ አድሏዊ ተግባራትን ይፈፅማሉ:: አድሏዊ አሠራሮች በተለያዩ ቦታዎች ለምሳሌ በትምህርት ቤት፣ በቀበሌ፣ በፍትህ ተቋማት ወዘተ ሊፈፀሙ ይችላል::

እነዚህ አድሏዊ ድርጊቶች ሕግ እንዲዛባ በማድረግ ፍትሐዊ አሠራር እንዳይሰፍን እንቅፋት ይሆናሉ:: ሆኖም ግን በየትኛውም አካባቢ የሚፈፀሙ አድሏዊ አሠራሮች ፈፅሞ የሚደገፉ ድርጊቶች አይደሉም::

**መልመጃ 10**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

1. አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስወገድ ከእናንተ ምን ይጠበቃል?
2. በትምህርት ቤት የሚፈጸሙ አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?

### 4.3.3 አድሏዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች

**“የቻነር መንደሮች” /ክፍል ሁለት/**

በቻነር መንደሮች ሁኔታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ እና ከቁጥጥር ውጪ እየወጡ ስለሆነ ለመኖር አስፈሪ ሆኗል:: የመንደሮቹ የቀድሞ ወታደራዊ ጥንካሬና ሕብረት ባለመኖሩ ምክንያት በሌሎች አጎራባች ሕዝቦች በተደጋጋሚ እየተወረሩ ነው:: ህጻናት በሜዳዎች ላይ ሲጫወቱ፣ እንስሶች ሲቦርቁ አይታዩም:: ጠለፋም በእጅጉ በመባባሱ ምክንያት ሴት ልጆች ትምህርት ቤት መሄድ አቁመዋል:: እናቶች ገበያ ለመሄድ ሲያስቡ ከፍተኛ ፍርሀት ይሰማቸዋል:: አልፎ አልፎም ሰዎች እየተገደሉ እንደሆነ በሰፊው ይወራል:: ሰዎች መንደሮቻቸውን እየለቀቁ መሰደድ ጀምረዋል:: በመጨረሻም መንደሮቹ ሰው አልባ ሆኑ:: እንደ ዋዛ ፈረሱ፤ ጠፉ:: አሁን ሰዎች በፈራረሱት መንደሮች በኩል ሲያልፉ “ቻነር የፍቅር መንደር የፍትሕ ሀገር” በማለት ይቀልዳሉ፤ ያፌዛሉ::

**መልመጃ 11**

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ሕግን አለማክበር እና አድሏዊ አሠራሮች የሚያደርሱአቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ::
2. የቻነር ነዋሪዎች ችግር እንዳይፈጠር ምን ማድረግ ነበረባቸው? ሁለት ነጥቦችን ጥቀሱ::



*ሥዕል 4.6 ጠብና ሥርቆት*



*ሥዕል 4.7 ጠለፋ*



*ሥዕል 4.8 ንብረት አውድሞ መሸሽ*

***አድሏዊ አሠራሮች ቀጥሎ ያሉትን ችግሮች ያስከትላሉ***

- ዜጎች ከሀገራቸው ማግኘት የሚገባቸውን የዜግነት ጥቅም እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ ለም ሳሌ አድሎአዊ አሠራር በትምህርት ቤት ከተስፋፋ ህፃናት ማግኘት የሚገባቸውን የትምህርት እድል ሊነፈጉ ይችላሉ፡፡ አድ ሏዊ አሠራር በጤና ተቋማት ውስጥ ከተ ስፋፋ ለዜጎች ተገቢ የሆነ የህክምና አገል ግሎት መስጠት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡
- አድሏዊ አሠራሮች በቤተሰብ ውስጥ ከተ ስፋፉ ኑሮው ይናጋል፡፡ ከዚህም በላይ አድ ሎአዊ አሠራር ሕግና ደንብ እንዳይከበር በማድረግ ዜጎች በመንግሥት ላይ እምነት እንዲያጡ ያደርጋል፡፡ አመፅና ብጥብጥ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ በዚህ የተ ነሳም የሀገር ሠላምና ፀጥታም ይደፈር ሳል፡፡ ዜጎች ሀብትና ንብረታቸውን በጉል በተኞች ይቀማሉ፡፡ በሕይወታቸውም ላይ ጥቃት ሊፈፀምባቸውም ይችላል፡፡

**መልመጃ 12**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. አድሎአዊ አሠራር መኖር በዜጎች ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል?
2. አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስወገድ ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?

## 4.4 ማሕበራዊ ተቋማት

### 4.4.1 የማሕበራዊ ተቋማት ምንነት










*ሥዕል 4.9 ማሕበራዊ ተቋማት*

- የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ ተቋማቱ በአካባቢያችሁ መኖር አለመኖራቸውን በማጤን ሠንጠረዡን ሙሉ፡፡

| የተቋማት ዝርዝር | አለ | የለም | ብዛት | በተቋማቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. ትምህርት ቤት | | | | |
| 2. የጤና ኬላ | | | | |
| 3. ቀበሌ ጽህፈት ቤት | | | | |

ማሕበራዊ ተቋማት የሚባሉት በአንድ አካባቢ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ታስበው የተቋቋሙ መሥሪያ ቤቶችን የሚገልፅ ሀሳብ ነው:: ከላይ በሠንጠረዥ የተቀመጡት መሥሪያ ቤቶች የማሕበራዊ ተቋማት ምሳሌ ዎች ናቸው::

እነዚህ ተቋማት ለሕብረተሰቡ የተለያዩ ጠቃሚ እና አስፈላጊ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ:: ለምሳሌ እናንተ የምትማሩበት ትምህርት ቤት ለአካባ ቢያችሁ ሕብረተሰብ የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የተሠራ ነው:: የጤና ማዕከሉም እን ደዚሁ ሕብረተሰቡ ለሚያጋጥሙት የጤና ችግ ሮች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የተመሠ ረተ ማሕበራዊ ተቋም ነው::

መልመጃ 13

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?
1. ማህበራዊ ተቋማት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፁ::
2. ማህበራዊ ተቋማት ምን ምን አገልግሎቶችን ይሰጣሉ?

### 4.4.2 የማሕበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሐዊነት

- ፍትሐዊ ማሕበራዊ አገልግሎት መስ ጠት ማለት ምን ማለት ነው?
- የማሕበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍት ሐዊነት በምን ይገለፃል?

ማሕበራዊ ተቋማት የሚቋቋሙት ሁሉንም ሕብረተሰብ ያለምንም ልዩነት እኩል እንዲያገ ለግሉ ነው:: ለዚህም ተቋማት በእኩልነት እና በፍትሐዊነት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት አሰ ጣጥ ሥርዓትን መከተል ይኖርባቸዋል:: ፍት ሐዊ አገልግሎት ማለት ሀብታም፣ ድሀ፣ ሥል ጣን ያለው፣ ሥልጣን የሌለው፣ ዘመድ ያለው፣ ዘመድ የሌለው፣ ወዘተ ሳይሉ ዜጎች ከተቋ ሞቹ የሚፈልጉትን አገልግሎት በተገቢ ሁኔታ መስጠት ማለት ነው::

መልመጃ 14

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?
1. ማህበራዊ ተቋማት ፍትሐዊ አገልግ ሎት እንዳይሰጡ እንቅፋት ይሆናሉ የምትሏቸውን ነጥቦች ጥቀሱ::
2. ፍትሐዊ አገልግሎት ካልሰጡ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ዘርዝሩ::

## 4.5. ግብር

### 4.5.1 የግብር ምንነትና ጥቅም



*ስዕል 4.10 የግብር አከፋፈል ሁኔታ*

- በሥዕል 4.10 የሚታዩት ሰዎች ምን እያደ ረጉ ይመስላችኋል?
- ግብር የሚለውን ቃል ሰምታችሁ ታውቃ ላችሁ? የምታውቁትን ሀሳብ ግለፁ::

## የከድጃ ጥያቄ

ከድጃ ሰሞኑን "ስለማህበራዊ ተቋማት ምንነት" ከተማረች በኋላ በአካባቢያቸው ያሉትን የተ ለያዩ ተቋማት ማን እንደሠራቸው ማወቅ ፈለ ገች:: በዚሁ ጥያቄ ዙሪያ ከአባቷ ከአቶ አሊ ጋር ውይይት አድርጋለች:: ውይይቱ ከድጃ ስለማሕበራዊ ተቋማት ካገኘችው እውቀት በተ ጨማሪ "ስለግብር ምንነት" እንድታውቅ ረድ ቷታል:: አባትና ልጅ ያደረጉት ውይይት በሁ ለት ክፍሎች በሚከተለው መልኩ ቀርቧል::

## የከድጃ ጥያቄ /ክፍል አንድ/

***ከድጃ፣*** አባባ በአካባቢያችን የሚገኙትን ትምህ ርት ቤቶች፣ የጤናና የግብርና ጣቢያ ዎች፣ መንገድ ወዘተ ማነው የሠራቸው?

***አቶ አሊ፣*** እነዚህ የጠቀስሻቸው አብዛኞቹን ተቋማት የሠራው መንግሥት ነው:: መንግሥት ማለት የሕዝቦችን ሠላምና ደህንነት የሚጠብቅ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን የሚሠራና የሚያሠራ የሕ ዝብ ውክልና የተሰጠው አካል ነው::

***ከድጃ፣*** አባባ መንግሥት እነዚህን ሁሉ ሥራ ዎች ለመሥራት ገንዘብ ከየት ያመጣል?

***አቶ አሊ፣*** መንግሥት እነዚህን ተግባራት የሚያከናውነው ከዜጎቹ በሚሰበስበው ገንዘብ ወይም ግብር ነው::

***ከድጃ፣*** አባባ ለመሆኑ ግብር ምንድን ነው?

***አቶ አሊ፣*** ግብር ማለት ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ላይ የተወሰነውን ለመንግሥት የሚ ከፍሉት ገንዘብ ነው:: መንግሥት ከግ ብር በሚሰበስበው ገንዘብ ለሕብረተ ሰቡ የሚያስፈልጉ ማሕበራዊ ተቋማ ትን ያስፋፋል:: መሰረተ ልማቶችን/ መንገድ፣ ውሀ፣ መብራት፣ ስልክ፣ ወዘተ/ ይገነባል:: የሀገርን ደህንነትና ሠላምን ያስከብራል::

***ከድጃ፣*** አባባ ሁሉም ሰው ለመንግሥት ግብር ይከፍላል?

***አቶ አሊ፣*** አዎ ነጋዴውም፣ ገበሬውም፣ የመን ግሥት ሠራተኛውም፣ የፋብሪካ፣ የጉልበት ሠራተኛውም፣ ወታደሩም ግብር መክፈል ይገባቸዋል::

**መልመጃ 15**

***ከላይ የቀረበውን ውይይት መሠረት በማ ድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ግብር ማለት ምን ማለት ነው?
2. ግብር በአግባቡ ካልተከፈለ ምን ምን ችግሮች ይደርሳሉ ብላችሁ ትገምታ ላችሁ?
3. መንግሥት በግብር የሰበሰበውን ገንዘብ በምን በምን ዓይነት ተግባራት ላይ ያውለዋል?

## የከድጃ ጥያቄ፣ /ክፍል ሁለት/

***ከድጃ፣*** አባባ ሁሉም ሰው የሚከፍለው ግብር እኩል ነው?

***አቶ አሊ፣*** አይደለም ልጄ ዜጎች የሚከፍሉት የግብር መጠን አንድ ዓይነት አይደ ለም:: የሚከፈለው የግብር መጠን የአንዱ ከሌላው ይለያል:: የግብሩ ክፍያ መጠን የገቢ ሁኔታን መሠረት ያደርጋል:: ስለዚህ ከፍተኛ ገቢ ያለው ሰው ከፍተኛ ግብር ይከፍላል:: ዝቅ ተኛ ገቢ የሚያገኘው እንደ ገቢው ዝቅተኛ ግብር ይከፍላል ማለት ነው::

***ከድጃ፣*** አባባ አንተስ መክፈል ያለብህን ግብር ከፍለሀል?

***አቶ አሊ፣*** በሚገባ፤ እኔ ያንቺ አባት፣ ከብዙዎች ግብር ከፋዮች ቀድሜ ነው ግዴታዬን የተወጣሁት፣ በቅርብ ጊዜ የከፈልኩ በት ማስረጃ ይኸውልሽ እይው።

*ከድጃ፡-* አባባ ግብር በአግባቡ ካልተከፈለ ምን ችግር ያደርሳል?

*አቶ አሊ፡-* አይ ልጄ ዜጎች በአግባቡ ለመንግሥት ግብር ካልከፈሉ፣ በእናንተ ደረጃ የሚገኙ ህጻናት ትምህርት መማር አይችሉም:: የጤና ጣቢያዎችንም በአግባቡ መገንባት ስለማይቻል ህብረተሰቡ በበሽታ ይጠቃል:: መንገዶች፣ የውሀ ጉድጓዶች፣ መብራት ወዘተ ሌሎችም አስፈላጊ አገልግሎቶች አይስፋፉም:: ስለዚህ የሀገር ልማትና እድገት ይደናቀፋል:: ሀገራችን ከድህነት መላቀቅ አትችልም::

*ከድጃ፣* አባባ አደጉ ወይም ሠለጠኑ የሚባሉ ሀገሮች ያደጉትና የሠለጠኑት ዜጎቻቸው ግብር በመክፈላቸው ነው?

*አቶ አሊ፣* አዎ የኔ ልጅ ዜጎቻቸው ጠንክረው በመሥራታቸውና የሚጠበቅባቸውን ግብር ለመንግሥታቸው ስለሚከፍሉ ነው:: መንግሥት እንደ አንድ ቤተሰብ ኃላፊ ይመሰላል:: የቤተሰብ ኃላፊዎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለቤተሰባቸው እንደሚያሟሉ ሁሉ መንግሥትም ለህብረተሰቡ የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራል:: ይህንም ተግባር የሚያከናውነው ከዜጎቹ በሚሰበስበው ግብር ነው::

*ከድጃ፣* አባባ አሁን ማህበራዊ ተቋማትን ማን እንደሚሠራቸው እና ስለግብር ምንነት በሚገባ ተረድቻለሁ:: የተረዳሁትን ሁሉ ነገ ለጓደኞቼ እነግራቸዋለሁ:: እኔም ወደፊት ሳድግና የራሴ ሥራ ሲኖረኝ የሚፈለግብኝን ግብር ለመንግሥት እከፍላለሁ::

*አቶ አሊ፣* ጎሽ፣ ጎሽ፣ ልጄ ይህን እንደምታደርጊ አምናለሁ::

**መልመጃ 16**

### *ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. የግብርን ጥቅሞች ዘርዝሩ::
2. ዜጎች የሚከፍሉት የግብር መጠን የሚወሰነው ምንን መሠረት በማድረግ ነው?
3. ግብር በአግባቡ ካልተከፈለ በእናንተ ደረጃ ያሉ ህፃናት ላይ ምን ዓይነት ችግር ይፈጥራል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ፍትሕ ማለት ሚዛናዊ የሆነ እውነተኛ ፍርድን ወይም ውሳኔ መስጠትን ወይም በእውነት መሥራትን የሚያብራራ ሀሳብ ነው፡፡ ፍትሕ በሁሉም የሕብረተሰብ ሕይወትና እንቅስቃሴ ውስጥ አስፈላጊ እና ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡ የአንድ ሕዝብ መሠረት የሆነውን ቤተሰባዊ አስተዳደርን የተረጋጋና ጤናማ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በዜጎች መካከል አድሏዊ አሠራር እንዳይኖር በማድረግ የእኩልነት ሥርዓትን ያጠናክራል፡፡ የአደገችና ሰላም የሰፈነባትን ሀገር ለመገንባት የሚያስችል ትልቅ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ፍትሐዊ አሠራር እንዲጠናከር ዜጎች በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ሕጎችን ሊያከብሩ ይገባል፡፡ ለፍትሕ አሠራር እንቅፋት የሚሆኑ አድሏዊ ተግባራትን መከላከል ያስፈልጋል። ሲፈፀሙ የሚያያቸውን አድሏዊ አሠራ ሮችንም በግልፅ መቃወም የአንድ መልካም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ፍትሐዊ አሠራር በተለያዩ ማሕበራዊ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ማህበራዊ ተቋማት እንዲስፋፉ ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ግብር ለመንግሥት መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በአንድ ሕብረተብ ውስጥ ፍትሐዊ አሠራር እንዲጠናከር ዜጎች በቤተሰብ ሕይወት በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያ አካባቢ፣ በሥራ ቦታዎች ወዘተ ፍትሐዊ አሠራርን ተግባራዊ ሊያርጉ ይገባል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ፍትሀዊነት፣** ከመድሎ የፀዳ ሥራ ወይም ተግባር፡፡
**ቅራኔ፣** መጋጨት፣ መጣላት፣ አለመስማማት።
**አድሎ፣** ለአንድ ወገን ያመዘነ፣ ሌላውን የሚጎዳ ተግባር ወይም ውሳኔ።
**በደል፣** ጉዳት፡ ጥቃት፡፡
**ተቋም፣** የተወሰነ ሥራን እንዲያከናውን ሥልጣን የተሰጠው መስሪያ ቤት።
**ዳኝነት፣** በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት ድርጊት ወይም ተግባር።
**ሚዛን፣** በእርስ በእርስ ግንኙነት አንዱ ሌላውን እንዳይበድል የሚያገለግል መሳሪያ፣ ዕኩልነትን እና ፍትሐዊነትን የሚገልጽ ምልክት።
**ባህሪ፣** ፀባይ።
**ሙያተኞች፣** በተለያዩ የትምህርትና የእውቀት መስኮች በቂ እውቀት፡ ወይም ችሎታ ያላቸው።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::***

### I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ሚዛናዊ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ ለሀገር እድገት ጠቃሚ አይደለም::
2. ባህላዊ የፍትሕ መስጫ ተቋማት ፍትሕን ለማስፈን ጥቅም አላቸው::
3. የፖሊስ አካላት ከዘመናዊ የፍትሕ አካል ውስጥ አይመደቡም::
4. ግብር ማሕበራዊ ተቋማትን ለማስፋፋት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ነው::
5. ፍትሐዊ አሠራሮች በሰዎች የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ጠቃሚ አይደሉም::

### II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሕግን ያለማክበር፣ | ሀ. ባህላዊ የፍትሕ ተቋም። |
| 2. ፍትሐዊነት፣ | ለ. ትክክለኛ ውሳኔ። |
| 3. ሽምግልና፣ | ሐ. ዘመናዊ የፍትሕ ተቋም። |
| 4. ማሕበራዊ ተቋም፣ | መ. ማርፈድ። |
| 5. ፍርድ ቤት፣ | ሠ. የጤና ኬላ። |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ፍትሐዊ አሠራር ወይም ሥርዓት አስፈላጊ የሚሆነው በየትኛው አካባቢ ነው?
   ሀ. በቤተሰብ፣ ሐ. በቀበሌ፣
   ለ. በትምህርት ቤት፣ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
2. ከሚከተሉት መካከል ለፍትሐዊ ውሳኔ እንቅፋት የሚሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሐሰተኝነት፣ ለ. ሀቀኛነት፣ ሐ. እውነተኛነት፣ መ. ሚዛናዊ ፍርድ።
3. ግብር መክፈል ያለበት የሕብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው?
   ሀ. ነጋዴ፣ ለ. የመንግሥት ሰራተኛ፣ ሐ. ገበሬ፣ መ. ሁሉም።
4. ማሕበራዊ ተቋም ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጤና ጣቢያ፣ ለ. ፖሊስ ጣቢያ፣ ሐ. ትምህርት ቤት፣ መ. ሁሉም።
5. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትሐዊ አሠራር ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የቤተሰብ መበተን፣ ለ ሠላም እና እድገት፣ ሐ. እኩልነት፣ መ. መፈቃቀር።

### IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. ሦስቱ ዋና ዋናዎቹ ዘመናዊ የፍትሕ ተቋማት ----------፣--------እና ------------ ናቸው::
2. ለዜጎች እውቀትን የሚያስፋፋ ማሕበራዊ ተቋም --------------- ነው::
3. ዜጎች እንደ ገቢያቸው መጠን ለመንግሥት የሚከፍሉት ገንዘብ ---------------- ይባላል::

### V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::

1. በትምህርት ቤት ውስጥ ፍትሐዊ አሠራር እንዲሰፍን ምን መደረግ አለበት።
2. ግብር በአግባቡ ካልተከፈለ ይደርሳሉ የምትሏቸውን ችግሮች ዘርዝሩ::

# ምዕራፍ አምስት

# የሀገር ፍቅር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ ስታጠናቅቂ፤***

- የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትረዳለህ/ ትረጂያለሽ፤
- በዜግነትና በሀገር ፍቅር መካከል ያለውን ግንኙነት ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፤
- የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚጎዱ አፍራሽ ተግባራትን ትለያለህ/ ትለያለሽ፡፡

## 5.1 የሀገር ፍቅር

### 5.1.1 የሀገር ፍቅር ምንነት



*ሥዕል 5.1 የልማት አርበኞች*

- *ሥዕሉ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት የሚያስተላልፈውን መልዕክት ግለጹ፡፡*
- *በአካባቢያችሁ ከሚነገሩ ምሣሌዎች፣ አባባሎች፣ አጫጭር ሕዝባዊ ግጥሞች፣ ዘፈኖችና መዝሙሮች መካከል ስለ ሀገር ፍቅር የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሏቸው፡፡*

*ለምሣሌ፤* *በፍቅር ሀገር ይሠራል፣*
*በዕውቀት ሕዝብ ይከብራል፣*
*በጥበብ ሕዝብ ይኰራል።*
*(ሕዝባዊ ግጥም)*

**የሀገር ፍቅር ማለት** የራስን ሀገር ከልብ መውደድ ማለት ነው፡፡ የአንድ ቤተሰብ አባላት የተለያየ መልክና ባህርይ ያላቸው ቢሆንም የቤተሰቡ አባላት ተግባብተው፣ ተፈቃቅረው፣ ተቻችለውና ተዋደው ይኖራሉ፡፡ የቤተሰቡ አባላት በዚያ ቤት ውስጥ እኩል መብትና ግዴታ እንዳላቸውም ይገነዘባሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ልዩ ልዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ልማድ ያላቸው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችም እንዲሁ በጋራ በሀገራቸው ውስጥ እኩል የመኖር መብት እንዳላቸው ሕገ መንግሥታችን አረጋግጦላቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለሀገራቸው የሚኖራቸው ፍቅር ከፍ ያለ ይሆናል፡፡

ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው የሀገራችን የግዛት ክልል ለብሔሮች፣ ለብሔረሰቦችና ለሕዝቦች እንደ አንድ ቤተሰብ መኖሪያነት በእኩልነት ያገለግላል፡፡ በዚህም ምክንያት ዜጐች ሁሉ በሀገራቸው ውስጥ በፍቅር ተቻችለውና ተከባብረው እየኖሩ ነው፡፡

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው።***

?

1. አንድ ሰው ሀገሩን ይወዳል ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ሀገራችንን የምንወደውስ ለምንድን ነው?

### 5.1.2 የሀገር ፍቅር መገለጫ ባህሪያት



*ሥዕል 5.2 ከሀገር ፍቅር መለማመጃ መድረኮች አንዱ*

- *ከሥዕሉ ምን ትገነዘባላችሁ?*

**አባባ ጉተማና የእነዶጨ ሰፈር ልጆች፤**

የአባባ ጉተማ ሰፈር አፍንጮ በር ነው፡፡ አፍንጮ በር በአዲስ አበባ ከተማ ስድስት ኪሎ አካባቢ የሚገኝ ሰፈር ነው፡፡ የአፍንጮ በር ልጆች አባባ ጉተማን በጣም ስለሚወዱቸው የሚጠሯቸው አባቢ እያሉ ነው፡፡

በ1928 ዓ.ም. ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በግፍ ስትወር አባቢም ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ዘማች ነበሩ፡፡ አባቢ ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ጋር ሲፋለሙ አንድ እግራቸውን ያጡ የሀገር ባለ ውለታ አርበኛ ናቸው፡፡

አባቢ የዶጨ ቅድመ አያት ናቸው፡፡ ዶጨ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ሲሆን ለአባቢ ልዩ ፍቅር አለው፡፡ የዶጨ ጓደኞች፤ ሀሊፍ፣ ዘምዘም፣ ታንቱ፣ ሚደቅሳና ንፅህት ይባላሉ፡፡ ዶጨና ጓደኞቹ ከአባቢ ጋር መጫወት ስለሚወዱ ከትምህርት ቤት መልስ ሁልጊዜም የሚከተለውን የመሰለ ውይይት ያደርጋሉ፡፡

***ዘምዘም፣*** አባቢ ይሄ እግርዎ ምን ሆኖ ነው የታመመው?

***አባቢ፣*** ልጄ ዘምዘም እግሬ መታመም ሳይሆን የተቆረጠው ለሀገሬ ነጻነት ከወራሪው የኢጣሊያን ጦር ጋር ስፋለም ነው፡፡

***ዘምዘም፣*** አባቢ ሀገርዎን በጣም ይወዳሉ ማለት ነው?

***አባቢ፣*** ከሀገር የሚበልጥ ምን የሚወደድ ነገር ይኖራል?

***ታንቱ፣*** አባቢ እኛስ ሀገራችንን መውደዳችንን እንዴት እንገልጻለን?

***አባቢ፣*** ጐሽ የእኔ ጐበዝ! ታንቱ ጥሩ ጥያቄ ጠይቆኛል፡፡ ሀገርን መውደድ የሚጀምረው ከቤተሰብና ከአካባቢ ነው፡፡ ወላጅን ማክበር፣ ጐረቤቶች ጥሩ ባህሪ ማሳየት፣ አቅም በፈቀደ መጠን አካባቢን በንጽህና መያዝ፣

ለትምህርት ቅድሚያ መሥጠት፣ የግልና የጋራ መገልገያ መሳሪያዎችን በጥንቃቄ መያዝ የሀገር ፍቅር መገለጫዎች ናቸው።

**ሚደቅሳ፣** አባቢ እኔ እንደርስዎ ወታደር ብሆን ጥሩ አይደለም?

**አባቢ፣** በጣም ጥሩ ሃሣብ ነው። ግን እኮ ሚደቅሳ ሀገር የምትጠበቀው በጦር ሜዳ ብቻ አይደለም፡፡ ለምሣሌ በዚህ በሰፈራችን የሕዝቡን ሠላም የሚያውኩትን ልጆች መምከር፣ ሀገርንና ሕዝብን ሊጐዱ ከሚችሉ መጥፎ ባህርያት መጠበቅ፣ ራስን ለታላላቆች ምሣሌ አድርጐ ማቅረብ ሀገርን ከመጠበቅ እኩል ይቆጠራል።

**ንጽሕት፣** አባቢ የሀገር ጠላት ሲመጣስ ምን ማድረግ አለብን?

**አባቢ፣** ንጽሕት የእኔ ቆንጆ የሀገር ጠላት ወራሪ ጦር ብቻ አይደለም፡፡ ወራሪ ጠላት ሲመጣማ ሕዝቡ ተረባርቦ ይመክታል፡፡ ትልቁ የሀገር ጠላት ርሃብና ድህነት ነው፡፡ ዛሬ ከፊታችን የተጋረጠው ግዙፉ ጠላት ድህነታችን ስለሆነ እያንዳንዱ ዜጋ በቅድሚያ ሊዋጋው የሚገባው ይህንኑ ክፉ ጠላት ነው፡፡

**ሀሉፍ፣** ድህነትን የምንዋጋው እንዴት ነው?

**አባቢ፣** ድህነትን የምንዋጋውማ በመማርና የሥራ ፍቅር በማዳበር ነው። የመንግሥትና የሕዝብ ሀብትን እንዳይባክን በመጠበቅ ድህነትን ማሸነፍ ይቻላል፡፡ የአካባቢያችሁ ቧንቧ ተሰብሮ ውሃ ሲፈስ ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅ፡፡ የመንገድ ዳር አምፖሎችን ያለመስበር፡፡ የእሣት አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ተግባራት መራቅ፣ አካባቢን በንፅህናና በጥንቃቄ መንከባከብ ከእናንተ ይጠበቃል፡፡

**ዶሬጮ፣** አባቢ ከዛሬ ጀምሮ ሀገራችንን ለመውደድና የመከሩንን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡

ሁሉም በአንድ ድምጽ፣ አዎን አባባ ሁላችንም በአንድነት ቃል እንገባለን።

**አባቢ፣** እደጉልኝ! እደጉልኝ! ጐበዝ ተማሪዎች ሁኑልኝ ልጆቼ። የዛሬ አበባዎቻችን የነገ የሀገራችን ፍሬዎች እናንተ ናችሁ፡፡

**መልመጃ 2**

*ከላይ የቀረበውን ውይይት መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. በአባቢና በእነዶጮ ውይይት መሠረት የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የሀገር ፍቅር መገለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ተጨማሪ ሃሣቦችን ዘርዝሩ፡፡
3. የሀገር ድንበር በሠራዊትና በሕዝብ እንደሚጠበቀው ሁሉ የሀገር ሀብትም ከብክነት ሲጠበቅ ድህነት አቅም አይኖረውም፡፡ በእነዚህ ሁለት ሃሣቦች ላይ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩባቸው፡፡

ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ሁሉ ለሀገሩ ያለውን ፍቅር በተግባር ማሳየት አለበት፡፡ የሚከተሉትን የሀገር ፍቅር መገለጫ ባህርያት በተግባር ላይ ማዋል ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፤

- ኢትዮጵያ ሀገራችን መተኪያ የሌላትና በታሪኳ የኮራች መሆኗን መገንዘብና የበለጠ እንድታድግ አስተዋጽኦ ማድረግ።
- ሕዝብን ሊጠቅም የሚችል ሥራ መሥራት፡፡
- ሀገርን ከሚጐዱ ተግባራት መራቅ፡፡

- የሌሎችን ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነትና አመለካከት በማክበር፣ በመቻቻልና በሠላም አብሮ መኖር፡፡
- የበለፀጉ ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ጠንክሮ መሥራት፡፡

## 5.2 የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ አፍራሽ ተግባራት

- ከራስ በላይ ነፋስ።
- "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል"
- የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ።
- ጉቦና ሌባ በር አይወድም።

ከዚህ በላይ ያሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች ምን መልእክት እንደሚያስተላልፉ ግለጹ፡፡

### አብራር ቀስቶ

የዕውቀቴ ወገኔ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጉብዝ ናቸው የታወቁ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ በ8ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤትም ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ከአካባቢው ትምህርት ቤቶች አንደኛ ወጥቷል፡፡ የተማሪዎቹ ጉብዝና በትምህርት ብቻ ሳይሆን በፀባይም የተመሰገኑ ናቸው፡፡ አብራር "ቀስቶ" የዚሁ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው፡፡

አብራር "ቀስቶ" በትምህርት ቤቱ የሚታወቀው እንደ ጓደኞቹ በትምህርቱ ጉብዝናና በፀባዩ መልካምነት ሳይሆን በአስቸጋሪ ባህርይው ነው፡፡ ተማሪዎቹ "ቀስቶ" ብለው የቅጽል ስም የሰጧቸው አባቱ መምህር ሃይደር የዕውቀቴ ወገኔ ትምህርት ቤት መምህር ናቸው፡፡ አብራር በአባቱ በመምህር "ቀስቶ" እየተመካ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ብዙ ጥፋት አጥፍቷል፡፡ ለምሣሌ፣ ከትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍት አባቱ የተዋሱትን መጻሕፍት ገፆች እየቦጨቀ ይወስዳል፡፡

ከአባቱ ከመምህር "ቀስቶ" የፈተና ጥያቄዎች እየሠረቀ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሸጥ ተገኝቷል፡፡ እንዲያውም አንድ ጊዜ ለአክስቱ ልጅ ለዘይነብ የፈተና ጥያቄዎች ሠርቆ ሰጥቷታል፡፡ በክፍል ውስጥም የተማሪዎችን ዕቃ እየሰረቀ መውሰዱም ተረጋግጧል፡፡ የትምህርት ቤቱን ቧንቧ ሰብሯል፡፡ በክፍላቸው ውስጥ ያለውን አምፖል በወንጭፍ መስበሩም ተደር ሶበታል፡፡

በትምህርት ቤቱ ጓሮ የተተከለውን የአትክልት ማሣ የአካባቢው ከብቶች ገብተው ሲያበላሹት አያገባኝም ብሎ ከፍተኛ ጥፋት እንዲደርስ ምክንያት ሆኗል፡፡ የአብራር "ቀስቶ" ባህርይ ከዕለት ዕለት መበላሸት ያሳሰባቸው የክፍል ጓደኞቹ ጥፋቱን ሁሉ ዘርዝረው ለርዕሰ መምህራቸው ለማቅረብ ከስምምነት ላይ ደረሱ፡፡



ሥዕል 5.3 ንብረትን ማበላሸት የሀገር ፍቅር ካለው ዜጋ አይጠበቅም

**መልመጃ 3**

***ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የአብራርና ቀስቶ የክፍል ጓደኞች ስርዕሰ መምህሩ ለማቅረብ የተስማሙባቸው ጥፋቶች በየትኞቹ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ በ(✓) ምልክት አመልክቱ፡፡

   ሀ. በጉቦና በዝምድና ውስታ __________ መዋል፡፡

ሰ. የሕዝብን ንብረት ማጥፋት ____________::

ሐ. በክፍል ውስጥ በሚያሳየው የጥፋት ተግባራት__________::

መ. በምን ችገረኝነት ጥፋትን አይቶ ማለፍ_____________::

ሠ. የአካባቢውን ሕዝብ አለማክበር ___________::

2. የአብራር አባት የመምህር ሃይደር ጥፋቶች ሊሆኑ የሚችሉ ሦስት ምክንያቶችን ጥቀሱ::
3. የአብራር "ቅስቶ" ያልተገቡ ባህርያት የሀገር ፍቅርን ሊጐዱ የሚችሉ አፍራሽ ተግባራት መሆን ወይም ያለመሆናቸውን ከአስተማሪያችሁ ጋር ተወያዩበት::

## 5.3 የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ምንነት

### 5.3.1 በቤት ውስጥ የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች

- *በቤታችሁና በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የጋራ መገልገያዎች ዘርዝሩ?*

የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች የሚባሉት ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች፣ ወይም ቡድኖች አገልግሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶች ናቸው:: የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን በርካታ ሰዎችን ያገለግላሉ::

ከግል መሣሪያዎች በተጨማሪ የሰው ልጆች ሁሉ የሚኖሩት የጋራ መሣሪያዎችን እየተጠቀሙ ነው:: የአንድ ቤተሰብ አባላትም በጋራ የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች አሏቸው። እነዚህ መሣሪያዎች፤ አልባሳት፣ መጻሕፍት፣ የመመገቢያና የማብሰያ ቁሳቁሶችና የንጽህና መጠበቂያዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ የጋራ መገልገያዎች በሁሉም የቤተሰብ አባላት በጥንቃቄ ሊጠበቁ ይገባል::

አንዱ የቤተሰብ አባል ጥንቁቅ፣ ሌላው ደንታቢስ ከሆነ የቤተሰቡ አባላት ሠላም ይናጋል:: በግዴለሽነት የተሰበረውን ዕቃ ለማስጠገን ወይንም ለመተካት የሚወጣው ተጨማሪ ወጪ የቤተሰቡን ባጀት ያናጋል። ስለዚህም እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የጋራ መገልገያ መሣሪያ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በቤት ውስጥ የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ዘርዝሩ::

### 5.3.2 በትምህርት ቤት የሚገኙ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች

- *በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ መሣሪያዎችን ዘርዝሩ::*



*ሥዕል 5.4 የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች*

"ከዚህ ከማይሞተው የሰው ልጅ ማደጊያ ሥፍራ ግቡ!" የሚልጥቅስ በብዙ ትምህርት ቤቶች መግቢያ በር ላይ ተጽፎ ይገኛል። ትምህርት ቤት ሕያው የሆነ የጥበብ መፍለቂያ ሥፍራ ነው:: በዚህ የትምህርት ተቋም ውስጥ በርካታ የጋራ መገልገያዎች ይገኛሉ::

እያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት ቤቱ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ቢሠበሩ ጉዳቱ የጋራ ነው፡፡ የመጸዳጃ ቤቶች በጥንቃቄ ካልተጠበቁ ተማሪው ህመምተኛ ይሆናል፡፡ ተማሪው ሲታመም ደግሞ ወላጅና መንግሥት ለህክምና ወጭ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ንጽህና የጐደለው የመማሪያ ክፍል በተማሪው የትምህርት አቀባበል ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ትምህርት ቤት የትናንትን፣ የዛሬንና የነገን ትውልድ የሚያስተሳስር የዕውቀት ማዕከል ስለሆነ የትምህርት ቤት የጋራ መገልገያዎች በጥንቃቄ ሊያዙ ይገባል፡፡

### 5.3.3 ለጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች

- ለጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ጥንቃቄ ማድረግ ለምን ያስፈልጋል?

በቤት ውስጥ የምንገለገልባቸውን መሳሪያዎች የሚያሟሉልን ወላጆቻችን ናቸው፡፡ የአካባቢያችንንና የትምህርት ቤት መሣሪያዎችን የሚያሟሉልን ደግሞ ሕዝብና መንግሥት ናቸው፡፡ ከሕዝብ የሚሰበሰብ ግብር እና ቀረጥ ለጋራ መገልገያዎቻችን ማሟያነት ይውላል፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ እነዚህን የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች በጥንቃቄና በንፅህና ሊይዝ ይገባል፡፡ የቆሻሻ መድፊያ ገንዳ በንጽህና ካልተጠበቀ ነዋሪው በጤና ችግር ይጐዳል፡፡ የመብራት፣ የስልክና የውሃ መስመሮች ከጥንቃቄ ጉድለት ቢበላሹ ተጐጂው ሕዝቡ ነው፡፡

ከሀገሪቱ ድህነት አንጻር አላስፈላጊ ወጭዎች ድህነታችንን ያባብሱታል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ ለጋራ መገልገያ መሳሪያዎች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ የሕዝብ መገልገያ መሳሪያዎችን ያበላሸም በሕግ ይጠየቃል፡፡

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. የግል መገልገያዎች ከሆኑት መካከል አራቱን ዘርዝሩ፡፡
2. በምትኖሩበት አካባቢ ሕዝቡ በጋራ ከሚገለገልባቸው መሣሪያዎች መካከል ሦስቱን በመዘርዘር ስለ አያያዛቸው በቡድን ተወያዩ፡፡
3. የተሰበረ ወይንም የተበላሸ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ካለ በመሰበሩ ምክንያት ያስከተለውን ጉዳት በተመለከተ ተወያዩበት፡፡

## 5.4 ከድኅነትና ከኋላቀርነት መላቀቅ

### 5.4.1 የድኅነትና የኋላቀርነት መገለጫዎች

ልጅ "እንጀራ! እንጀራ!" እናት "የለም! የለም!" ድኅነት ክፉ ነው ጠግቦ መብላት የለም፡፡

(ሕዝባዊ ግጥም)

- ግጥሙ የድኅነትን አስከፊነት እንዴት እንደገለጸ ተወያዩበት?

ድህነት የሚባለው፣ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና ሌሎች ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን በተሟላ ሁኔታ አለማግኘት ነው፡፡ ኋላቀርነትም በእድገት የበለፀጉ ሀገራት የደረሱበት የአመራረት፣ የአሠራርና የአኗኗር ደረጃ ላይ አለመድረስ ነው፡፡

ሀገራችን ደሃ ከሚባሉ ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ናት፡፡ የድኅነታችን መንስዔ ከሆኑት አንዱ ተግተን ያለመሥራታችን ነው፡፡ ድህነት ሁል ጊዜም የሌሎች ጥገኛ ያደርጋል፡፡ ድኅነት ለተመጽዋችነት ይዳርጋል፡፡ ደሃ ሕዝብ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋዎች በቀላሉ ይጠቃል፡፡

በቤተሰባችሁና በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎችን ልብ ብላችሁ ብታስተውሉ አንዳንድ ልጆች ከቤተሰባቸው ድህነት የተነሳ ትምህርት ለመ ማር አይችሉም:: ብዙ ልጆች ተገቢና ተመ ጣጣኝ ምግብም አያገኙም::

በድኅነት የተጠቃ ሕዝብ ኑሮው የተጐሳቆለ ይሆናል፣ የጤና ችግርም ይኖርበታል:: በእነዚህም ምክንያት በበቂ ሁኔታ ማምረት ስለማይቻል ድህነት ይንሠራፋል::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. በድኅነት ምክንያት መማር ያልቻሉ ልጆች አዋዋላቸው ምን እንደሚመስል ተወያዩበት::
2. የድህነትና የኋላቀርነት መገለጫዎች ከሆኑት ነገሮች መካከል ሦስቱን ጥቀሱ::

### 5.4.2 ከድኅነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ የመፍትሔ ርምጃዎች

- ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመላቀቅ የመ ፍትሔ እርምጃዎች ናቸው የምትሏቸ ውን ዘርዝሩ::

ከድኅነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ ዋናው መፍ ትሔ ተግቶ መሥራት ነው:: ከፍተኛ ዕድ ገት ላይ ለመድረስ የዜጐች የሥራ ፈጣሪ ነትና ሥራ ወዳድነት አስፈላጊ ነው:: በሀገራ ችንም እየታየ ያለው የዜጐች ለሥራ የመነ ቃቃት መንፈስ ጠንክሮ ሊቀጥል ይገባል:: በመንግሥት የተዘጋጁ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ዜጐችን ለሥራ የሚያነሳሱ ናቸው:: ስለሆነም በስትራቴጂዎቹና በፖሊሲ ዎቹ ታግዘን ጠንካራ የሥራ ባሕልን አዳብ ረን ሀገራችንን ከድህነት ማውጣት እንች ላለን።

**መልመጃ 7**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. በአካባቢያችሁ ከሚታዩ የልማት እንቅስቃ ሴዎች መካከል ሦስቱን ጥቀሱ::
2. በሀገራችን እየታዩ ካሉት ፈጣን የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ።

### 5.4.3 የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት

- የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?
- በበጐ ፈቃደኝነት የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ማህበራት በአካባቢያችሁ ምን ምን ተግባራት እያከናወኑ እንደሆነ ዘርዝሩ::

**በፈቃደኝነት የተፈፀመ በጐ ተግባር፣**

በአንድ ሀገር የሚኖር አንድ ታዳጊ ወጣት ነበር:: በወጣቱ መኖሪያ ቤት አካባቢ የሚያ ልፍ የባቡር ሀዲድ አለ:: ይህ ወጣት ሁልጊዜ በባቡር ሀዲዱ ዳር ቆሞ እጁን እያ ውለበለበ ተጓዦችን በፍቅር ሰላም ስለሚ ላቸው መንገደኞች ሁሉ ይወዱታል:: በተለ ይም ሁሉም የባቡር ሹፌሮች በሚገባ ስለ ሚያውቁት አንዳንዴ ትንንሽ ስጦታ እየወ ረወሩለት ያልፋሉ::

አንድ ማለዳ ግን ይህ ታዳጊ ወጣት አስደ ንጋጭ ነገር ያያል:: ከቤታቸው በታች ከሚ ገኘው ድልድይ ላይ የተዘረጋውን ሃዲድ የተ ሸከመው ድልድይ ፈርሶ ይመለከታል::

የባቡሩ መምጫ ሰዓት ደግሞ እየተቃረበ ነበር:: ለባቡሩ ሹፌር የተፈጠረውን ችግር ቀድሞ ካልተናገረና ባቡሩ ካልቆመ በስተቀር ተሳፋሪው በሙሉ እንደሚያልቅ ያውቃል:: ስለ ዚህም የለበሰውን ቀይ ሸሚዝ አውልቆ በእጁ በመያዝ የባቡሩን መምጣት መጠባበቅ ጀመረ::

ባቡሩም በአካባቢው እንደደረሰ ያ ወጣት ቀይ ሸሚዙን እያውለበለበ ከባቡሩ ጋር በመሮጥ ሹፌሩ ባቡሩን እንዲያቆም "እባክህ አቁም፣ ድልድዩ ተሰብሯል" እያለ መጮህ ጀመረ፡፡ የባቡሩ ሹፌርና መንገደኞቹ ግን እንደወትሮው ሠላምታ የሚሰጣቸው መስሏቸው እጃቸውን እያውለበለቡ ሰላምታ ሰጡት፡፡ ልጁም እያለቀሰ በመሮጥ ሸሚዙን እያውለበለበ ቢጮህ ማንም ጭንቀቱን ሊረዳለት አልቻለም፡፡

በመጨረሻም ባቡሩ ወደ ፈረሰው ድልድይ እየተጠጋ ሲሄድ ልጁ ባቡሩን በእጁ እየደበደበ ለማስቆም ሲሞክር አደናቅፎት በባቡሩ ሥር በመውደቁ ባቡሩ ጨፍልቆ ገደለው፡፡ ይህንን ሁኔታ በመስታወት ይከታተል የነበረው የባቡሩ ሹፌር ባቡሩን ቀስ ብሎ ካቆመ በኋላ በልጁ ድርጊት ተናዶና ተቆጥቶ ወርዶ ሁኔታውን ሲያጣራ ለካንስ ያ ታዳጊ ወጣት ለሕይወቱ ሳይሳሳ ራሱን አሳልፎ የሰጠው የባቡሩ ተሳፋሪዎች እንዳያልቁ ነበር፡፡

*(በብዙ ሀገሮች የሚነገር ጣፋጭ ታሪክ)*

**መልመጃ 8**

***ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ምንባቡ ስለ ታዳጊው ወጣት በጐ ተግባር ምን ያስተምራል?
2. ልጁ ያንን ተግባር ባይፈፅም ኖሮ ምን ሁኔታ ሊከሰት ይችል ነበር?
3. እንደ ባለታሪኩ ዓይነት መልካም ልጆች ለሌላው ጥቅም ሲሉ ሕይወታቸውንም ይሰጣሉ፡፡ እናንተስ በአካባቢያችሁና በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በበጐ ፈቃደኛነት የአቅማችሁንና የችሎታችሁን ያህል ታበረክታላችሁ? ተወያዩበት፡፡

በጐ ፈቃደኝነት በራስ ተነሳሽነት ሌሎችን ለመርዳት የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ በበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ዜጐች ሁሉ ሊሳተፉ ይገባል፡፡ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ከልጅነት ዕድሜ ጀምሮ መዳበር የሚገባው መልካም ተግባር ነው፡፡ ማንም ሰው በበጐ ፈቃደኝነት አንድ ተግባር እንድንፈጽም ላያዘን ይችላል፡፡ ወገኖችንን ለመርዳት ስሜታችን ለበጐ ሥራ የተነቃቃ ሊሆን ይገባል፡፡

አንዳንድ ሰው በገንዘቡ፣ አንዳንድ ሰው በዕውቀቱ ወይንም በምክሩ በጐ ተግባራት ሊፈፅም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ በአካባቢያችን ያሉ ችግረኞችንና ህሙማንን ልንረዳ እንችላለን፡፡ በትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥም የተጓደሉ ነገሮችን ለማሟላት በበጐ ፈቃደኝነት አቅማችን የፈቀደውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንችላለን፡፡

**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. በጎ ፈቃደኝነትን ለማጎልበት ምን መደረግ አለበት?
2. በምትኖሩበት አካባቢ በበጎ ፈቃደኝነት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ያከናወኑትን ተግባር ግለፁ?

## 5.5 ዜግነት

### 5.5.1 የዜግነት ምንነት

ሰው በሀገሩ፣ ሰው በወንዙ
ቢበላ ማር ቢበላ መቅመቆ፣
ይከበር የለም ወይ ማንነቱ ታውቆ፡፡
(ሕዝባዊ ግጥም)

- ይህ ሕዝባዊ ግጥም ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

ዜግነት ማለት የአንድ ሀገር ሕጋዊ አባል መሆን ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው የአንድ ሀገር ዜጋ ሲሆን የሀገሩ መንግሥት ለሚያወጣው

ሕግና ሥርዓት ተገገር ነው፡፡ በዜግነቱም ሕጉ በሚደነግጋቸው መብቶች ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ ሲሆን ግዴታውንም በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ዜጋ በማንኛውም የሀገሩ ጉዳይ በግንባር ቀደምትነት ተሣታፊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ሀገሩንና ሕዝቡን ከሚጐዱ ድርጊቶችም ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሰዎችንና ድርጊቶችንም በጽናት ሊቃወም ይገባል፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩም ለሕግ አካላት በፍጥነት የማሳወቅ የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት ነው፡፡

**መልመጃ 10**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ዜግነት ምንድን ነው?
2. ከአንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ምን ምን የዜግነት ተግባራት ይጠበቃሉ?
3. "ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረግሁላት ብለህ ጠይቅ" የሚለው አባባል ምን መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

## 5.6 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ

### 5.6.1 የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና የብሔራዊ የሕዝብ መዝሙር ምንነትና አስፈላጊነት



*ስዕል 5.5 ተማሪዎች በሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ላይ*

- ፎቶግራፉ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?

**ሠራዊትና ጓደኞቹ**

ሠራዊትና ሦስቱ ጓደኞቹ የኅብረት አምባ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አራቱ ጓደኞች በትምህርት ቤት ውስጥ ያልተገባ ባህርያት በማሳየታቸው ብዙ ጊዜ ተቀጥተዋል። በተለይም ጥዋት ጥዋት ትምህርት ከመጀመሩ አስቀድሞ በሚደረገው የሰንደቅ ዓላማ ማውጣት ሥነ ሥርዓት ላይ በሰልፍ ላይ እየረበሹ አስቸግረዋል። አንዳንድ ቀን ተማሪዎች ብሔራዊ የሕዝብ መዝሙር ሲዘምሩ አራቱ ጓደኞች ሌላ መዝሙር በመዘመር ረብሸዋል። ሌላ ቀን ደግሞ በሰልፍ ላይ የቆሙትን ተማሪዎች እየተነኰሱ ሁከት ፈጥረዋል።

ይህን መሰሉን የአራት ጓደኞች ረብሻ በተደጋጋሚ ያስተዋሉት የትምህርት ቤቱ የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ክበብ ተወካይ ተማሪዎች አራቱን ተማሪዎች አቅርበው አነጋገሯቸው። ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የአንድ ሉዓላዊ ሀገር ክብርና መገለጫ ስለሆኑ ተገቢ አክብሮት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በጥሩ ሁኔታ አስረዷቸው። ከብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር በስተጀርባ በየዘመናቱ ታላላቅ ጠቃሚ ሀገራዊ ታሪኮች መፈጸማቸውንም አስገነዘቧቸው።

በተለይም የሀገራችንን ብሔራዊ ክብርና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ጀግኖች አባቶቻችን ሰንደቅ ዓላማችንን በማስቀደም የከፈሉትን የአካልና የሕይወት መስዋዕትነት እየዘረዘሩ አስረዷቸው። ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በስፖርት አደባባዮችና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ሲውለበለብ ለተመልካች ታላቅ ትርጉም እንደሚያስተላልፍ በርካታ መረጃዎችን በመዘርዘር ሊያስረዷቸው ሞከሩ።

ከዚህ መሰሉ ሰፊ ውይይት በኋላ አራቱ ወጣቶች ስህተታቸውን አምነው ይቅርታ በመጠየቅ ይህንን የመሰለ ስህተት እንደማይደገሙም ቃል ገቡ።

ቀደም ብለው በሰንደቅ ዓላማ አወጣጥ ሥነሥርዓት ላይ ስለፈጸሙት ያልተገባ ስህተትም የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች በሙሉ በሰልፍ ላይ ይቅርታ እንደሚጠይቁ ቃል ገቡ::

**መልመጃ 11**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. አራቱ ጓደኛሞች በሰንደቅ ዓላማ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ከሚፈጸሙት ያልተገባ ተግባራት ምን ተረዳችሁ?
2. እንደዚህ ዓይነት ተማሪዎች በእናንተ ትምህርት ቤት አሉ? ካሉስ በሰንደቅ ዓላማ አወጣጥ ሥነሥርዓት ወቅት የሚፈጽሙት ጥፋት ምን ይመስላል?
3. የትምህርት ቤቱ የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ክበብ አባላት ከፈጸሙት ተግባር ምን ተማራችሁ?
4. ከትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ሰንደቅ ዓላማንና ብሔራዊ መዝሙርን አስመልክቶ ተማሪዎች ተገቢ እውቀት እንዲኖራቸው ምን ቢደረግ ይሻላል?

የአንድ ሀገር ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በብሔራዊ ምልክትነቱ ላቅ ያለ ትርጉም አለው:: ለምሳሌ ዜጎች ሁሉ ቁም ነገር ላለው ሀገራዊ ጉዳይ እን ዲተባበሩና እንዲነሳሱ ታላቅ ጠቀሜታ አለው:: ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ነፃነትን፣ ጀግንነትን፣ መደጋገፍን፣ የሉዓላዊነት ክብርን የሚወክል ተም ሳሌት ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብም ሀገሩን ከሰንደቅ ዓላማው ለይቶ እንደማያይ በበጎም ይሁን በክፉ ታሪካዊ ወቅቶች አስመስክሯል:: የመንግሥት ሥርዓቶች እንኳ አስከፊና ጨቋኝ በሆኑበት ወቅት ሕዝቡ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማውን በማስቀደም በጨቋኝ ሥርዓቶችና የሥርዓቱ አራማጆች ላይ ዘምቶ ነፃነቱን አውጇል:: ለሰንደቅ ዓላማው ክብር ሲልም የሕይወትና የአካል መስዋዕትነት በመክፈል የውጭ ወራሪዎችን አሳፍሮ መልሷል::

ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን በትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በመንግሥትና በግል ተቋማት፣ በቤተ እምነቶች፣ በየሀገሩ ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጽ/ቤቶች፣ በታላላቅ የመንግሥታት ስብሰባዎች፣ በስፖርት ሜዳዎች፣ በጦር ሜዳ ወዘተ በብሔራዊ መዝሙራችን እየታጀበ ሲውለበለብ ሀገርን ከመ ወከል ጐን ለጐን ብሔራዊ ስሜትን በከፍተኛ ሁኔታ ያነሳሳል::

ሕዝባዊነትን፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝ ቦችን ድንቅ ባህልና የአኩሪ ቅርሶች ባለቤት ነትን፣ የታደልነውን የተፈጥሮ ፀጋና ጀግንነታች ንን አጉልቶ የሚያሳየው ብሔራዊ መዝሙራች ንም ሰንደቅ ዓላማችን በሚውለበለብበት ወቅት ሲዘመር የሀገራችንን ሉዓላዊነት ክብር ከፍ ያደ ርጋል::

**መልመጃ 12**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ሀገርን ይወክላል ሲባል ምን ማለት ነው?
2. «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በድል ሲውለበለብ የተሰማኝ ደስታ» በሚል ርዕስ የየግላችሁን ገጠመኞች በማስታወስ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::
3. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥና በአካባቢ ያችሁ የሚውለበለቡ ሰንደቅ ዓላማዎችን በተመለከተ ስለአያያዛቸው አጭር የጽሑፍ ዘገባ በማቀረብ ተወያዩበት? ሰንደቅ ዓላማው በጥሩ ሁኔታ ተይዟል ወይንስ ከእርጅና የተነሳ ተጐሳቁሏል? ይህንን መሰሉ ድርጊትስ አግባብ ነው ትላላችሁ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የሀገር ፍቅር ስሜት የሚዳብረው በቤት ውስጥ፣ በአካባቢና በትምህርት ቤት ውስጥ በምናደርጋቸው ውጤታማ እንቅስቃሴዎች ነው፡፡ የሀገር ፍቅርን የሚጐዱ ዝርዝር ተግባራትም ተገልፀዋል፡፡ ማንኛውም ሰው ሌላውን ሰው በሃይማኖቱ፣ በባህልና በቋንቋው ልዩነት ሳያደርግ ሊያከብረው ይገባል፡፡ ፍትሐዊነትና እኩልነት ሰፍኖ ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመላቀቅም ዜጎች ሁሉ በሥራ ማመንና ስጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ዜግነት የአንድ ሀገር ሕጋዊ አባል መሆን ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን መብት መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ግዴታውንም ሊወጣ ይገባል፡፡

ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ብሔራዊ መዝሙር ክብር መስጠት የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ሕገ መንግሥት፣** ዓለማቀፋዊ መብቱ፣ ጥቅሙና ክብሩ የተጠበቀለት ነጻ ሀገር።

**ጉቦ፣** ሌላውን ሰው አለአግባብ በመጥቀም የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት ያልተገባ ጥቅም።

**ሕዝባዊ ግጥሞች፣** ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡና ደራሲያቸው የማይታወቅ ግጥሞች።

**አርበኛ፣** ሀገር በመከላከል፣ በተሰማራበት መስክ ውጤታማ ሥራ በመሥራት፣ የታወቀ ሰው።

**ሠርዶ ሣር፣** ባለ አንጓ መሬት ለመሬት ተሳቢ ሣር።

**መቅመቆ፣** ጨው ጨው የሚል ጣዕም ያለው የዕፅዋት ዓይነት። በአንዳንድ አካባቢዎች ከሣር ዝርያ ጋር ይመድቡታል፡፡ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍልም መቅመቆ የሚባለው እርድ እየተባለ የሚጠራው የቅመም ዓይነት ነው፡፡

**ግብር እና ቀረጥ፣** ከንግድ፣ ከፍጆታና ከመገልገያ ንብረቶች ጋር በተያያዘ መንግስት ከድርጅቶች፣ ከተቋማትና ከዜጎች ለልማት ሥራ እንደ ገቢያቸው መጠን የሚሰበስው ገንዘብ።

**ፖሊሲ፣** ለአንድ ተግባር አፈፃፀም መንግሥት የሚያወጣው መመሪያና ደንብ።

**ስትራቴጂ፣** ለአንድ ተግባር ክንውን መንግሥት የሚነድፈው የአፈፃፀም መመሪያ።

**መገናኛ ብዙሃን፣** ሬዲዮ፣ ጋዜጣ፣ ቴሌቪዥንና ሌሎች የመረጃ ማግኛ ምንጮች።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡***

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ባህል ሳይበላለጥ ሁሉም በእኩልነት መታየት አለበት።
2. ዜጎች ቢያልፉም ሀገር ግን ነዋሪ ነች።
3. የትምህርት ቤታችን ንብረት ቢባክን የሚጎዳው መንግሥት ብቻ ነው።
4. ጉቦኝነት ራስን ከችግር ለማላቀቅ የሚጠቅም መልካም ተግባር ነው።
5. በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዜጎች ሁሉ እኩል መብት የላቸውም።
6. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የአንድ ሀገር ክብር መገለጫ ነው።

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ነፃ መንግሥት፣ | ሀ. በራስ ተነሳሽነት የሚከናወን ተግባር። |
| 2. ዜግነት፣ | ለ. የሕዝቦች የማንነት መገለጫ። |
| 3. ጉቦ፣ | ሐ. ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚገኝ ጥቅም። |
| 4. በጎ ፈቃደኝነት፣ | መ. የአንድ ሀገር ሕጋዊ አባል መሆን። |
| 5. ባህል፣ | ሠ. ሉዓላዊ። |

**III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት የሚረጋገጠው እንዴት ነው?
   ሀ. በመገናኛ ብዙኃን ትምህርት ስለሚሰጥ፣
   ለ. ቋንቋቸው ብቻ ስለሚከበር፣
   ሐ. የራሳቸውን ክልል በመንግሥት ፈቃድ ስለሚያቋቁሙ፣
   መ. ያለምንም ተፅዕኖ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ስለሚወስኑ።

2. አንድ ዜጋ የዜግነቱን ኃላፊነት የሚወጣው እንዴት ነው?
   ሀ. ለሀገሩ ሕገ መንግሥት ተገዢ በመሆን፣
   ለ. ዴሞክራሲያዊ መብቱ እንዲጠበቅ የሚፈለገውን ያህል እርሱም የሌላውን መብት ሲጠብቅ፣
   ሐ. ግዴታውን በመወጣት የሌላውን ሰው መብት በማክበር፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል፡፡

3. የጋራ መገልገያ መሣሪያ እንዲሆን የማይመረጠው የትኛው ነው?
   ሀ. የትምህርት ቤት ዴስክ፣
   ለ. የመኖሪያ ቤት ቴሌቪዥን፣
   ሐ. የጥፍር መቁረጫ ምላጭ፣
   መ. የአካባቢ የውሃ ቧንቧ።

4. ከሚከተሉት አንዱ ጉቦ ሊባል ይችላል፤
   ሀ. ለጐበዝ ተማሪ የሚሠጥ ሽልማት፣
   ለ. ጉዳይ ለማስፈፀም በሕጋዊ ደረሰኝ የሚከፈል ገንዘብ፣
   ሐ. በዘመድ እርዳታ ሥራ መቀጠር፣
   መ. በሥራ ልምድ አሸንፎ ሥራ መያዝ።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ሀገራችን ነፃ  ሀገር ነች ስንል____________ሀገር ነች ማለታችን ነው፡፡
2. የሀገራችን ሕዝቦች ከሀገራቸው ሀብት እኩል____________መሆን ይገባቸዋል፡፡
3. ____________የማንነታችን መገለጫ ምልክት ነው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ዜግነት ምንድን ነው?
2. የጋራ መገልገያ መሳሪያ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የሀገር ፍቅር እንዴት ይገለፃል?

# ምዕራፍ ስድስት

# የኃላፊነት ስሜት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ ስታጠናቅቂ፤***

- የኃላፊነትን ምንነት ትረዳለህ/ ትረጂያለሽ፤
- የተለያዩ የኃላፊነት ዓይነቶችን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፤
- ተግባርን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት በመፈፀም በየደረጃው የዜግነት ኃላፊነትን መወጣትን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ፡፡

## 6.1 ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ ምንነት፤



*ሥዕል 6.1 ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ችግኞችን ውሀ በማጠጣትና በመኮትኮት ላይ*

- በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ተማሪዎች ተግባር ምንን ያመለክታል?
- ችግኝ መትከል ጥቅሙ ምንድነው?

### ስምስም ግቢ

ወ/ሮ ጫልቱና አቶ ጋሻው ባለትዳርና የአራት ልጆች ወላጆች ናቸው፡፡ አቶ ጋሻው ሸማኔ ሲሆኑ ወ/ሮ ጫልቱ ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስተምራሉ፡፡ ብሩክ፣ ገላኔ፣ ቤዛና ገመቹ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡

ቤተሰቡ ሥራን በኅብረት ይሠራል፡፡ እነ ብሩክ የቤት ውስጥ ሥራን በመከፋፈልና በየሣምንቱ በመለዋወጥ ይሠራሉ፡፡ የሴትና የወንድ የሚለውን ባህላዊ የሥራ ምደባና ገደብን አያምኑበትም፡፡ ጊዜያቸውን በአግባቡ መድበው ስለሚጠቀሙበት በቂ የጥናት ጊዜ አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየዝንባሌአቸው የልማት ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡ ብሩክ የጓሮ አትክልት ያለማል፣ ቤዛ ንብ ታንባለች፣ ገመቹ ዶሮ ያረባል፣ ገላኔ የአባቷን ሞያ ይዛ ሽመና ትሠራለች፡፡ ግቢያቸው ለምለምና ልዩ ልዩ ምርት የሚታይበት በመሆኑ በአካባቢው ሰዎች "ለምለም ግቢ" በሚል ስያሜ ይታወቃል፡፡ የአካባቢያቸው ነዋሪዎችም ምርቶቻቸውን ይገዛሉ፡፡

እነ ብሩክ ከሽያጩ በሚያገኙት ገቢ የቤተሰቡን ኑሮ በደንብ ይደግፋሉ፡፡ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጋቸውንና ሌሎችም ወጪዎቻቸውን በአብዛኛው በልማታቸው ገቢ ይሸፍናሉ፡፡ በተጨማሪም የሰፈራቸው ዕድር ባቋቋመው የአረጋውያን መርጃ ማሕበር አባል ሆነው የአባልነት መዋጮም ይከፍላሉ፡፡ በትምህርት ቤትም በክበባት በመሳተፍ የሥራ ልምዳቸውን ለጓደኞቻቸው ያካፍላሉ፡፡ እነ ብሩክ ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ተጨባጭ ውጤት በማሳየታቸው በትምህርት ቤትና በቀበሌያቸው እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱና የሚመሰገኑ ሆነዋል፡፡

**መልመጃ 1**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. **እነ ብሩክ የኃላፊነትን ተግባር ያከናወኑት በምን ሁኔታ ነው?**
2. **ሥራን የሴትና የወንድ ብሎ መመደብ ትክክል ነው ወይስ አይደለም?**
3. **በቤትና በትምህርት ቤት የምትሠሩት ሥራ አለ? ካለ ምን ምን እንደሆኑ ለጓደኞቻችሁ ገለፁ።**

ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ ማለት አንድን ጉዳይ በራስ ተነሳሽነት ወይም በሚሰጥ መመሪያ በአግባቡ ለመፈጸም ኃላፊነትን መቀበልና መወጣት ነው፡፡ ሁሉም ሰው በተሰማራበት ሙያና ሥራ ጠቃሚ ውጤት የማሳየት ኃላፊነት ይጠበቅበታል፡፡ ኃላፊነት እንደሙያው ዓይነትና ደረጃዎች ይለያያል፡፡

ለምሳሌ ወላጆች ልጅ ወልደው ማሳደጋቸው፣ ሀኪሞች ማከማቸው፣ መምህራን ማስተማራቸው፣ ሠራዊቱ ሀገር መጠበቁ፣ ገበሬው ማረሱና ማምረቱ፣ ተማሪዎች መማራቸው በተለያዩ የኃላፊነት ሥራዎች መሠማራታቸውን ያመለክታል፡፡ በዚሁ መሠረት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በመሳተፍ ኃላፊነትን ወስደው ለማከናወን ችግሮችን በመፍታት አስተዋጽኦ የማድረግ ልምድ መውሰድ አለባቸው፡፡

የኃላፊነት ደረጃ ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል፡፡ ሆኖም ማንኛውም ሰው በተሠማራበት ሥራ አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡ የእያንዳንዱ ሰው ሥራ ጥሩ ውጤት ለራሱ፣ ለኅብረተሰቡ፣ ቀጥሎም ለሀገር እድገት ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ በተማሪነታችሁ ጊዜ ሥራችሁ ትምህርት በመሆኑ በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ ዓላማ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በቤት ውስጥ በአቅማችሁ ኃላፊነትን በመውሰድ ለቤተሰቦቻችሁ የሥራ እገዛ ማድረግ አለባችሁ፡፡

ወላጆቻችሁ ጊዜ፣ ጉልበትና ሀብታቸውን ሁሉ ለእናንተ በጐ ዕድገት መስዋዕት ማድረጋቸው ጥሩ ዜጋ ለማፍራት መሆኑን መገንዘብ አለባችሁ፡፡ ስለዚህ በአቅምና በችሎታችሁ ኃላፊነትን መውሰድና ጥሩ ውጤት ማሳየት ወላጆችን ማስደሰትና የዜግነት ግዴታን የመወጣት ምልክት ነው፡፡

ኃላፊነትን መውሰድ በትምህርት ቤትም መደረግ ያለበት ተግባር ነው፡፡ የጋራ መገልገያ የሆኑትን የትምህርት ቤት ንብረቶች ከጉዳት መጠበቅ የእያንዳንዱ ተማሪ ኃላፊነት በመሆኑ በባለቤትነት መንፈስ እንክብካቤ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪም፣ የህፃናትና የሴቶችን ጥቃት መቃወምና መከላከል ከትምህርት ቤት ሕይወት ጀምሮ ሊዳብር የሚገባው የኃላፊነት ግዴታ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. **ኃላፊነትን መወጣት ማለት ምን ማለት ነው?**
2. **በፈቃደኝነት የሚሠራ ሥራ ኃላፊነትን መወጣት ነው አይደለም? እንዴት?**
3. **የትምህርት ቤትን ንብረት ተማሪዎች ለምን ይንከባከባሉ?**
4. **የህፃናትና የሴቶችን ጥቃት መከላከል መጀመር ያለበት ከየት ነው?**

## 6.2 የቃል ኪዳን ምንነትና አስፈላጊነት፤

"የተናገረውን በውጤት አብሳሪ
እውነተኛ ሰው ነው ቃልኪዳን አክባሪ፡፡"

- እላይ በተሰጡት ስንኞች መሠረት ቃልኪዳን ምንድነው?
- ቃልኪዳን በምን ይገለጻል?
- ቃሉን የሚያከብር ሰው ምን ተብሎ ይጠራል?

## ጨለማና ክረምት

ባለፈው ሐምሌ 30 ቀን የጣለው ዝናብ እጅግ ከባድ ነበር:: የለቡ ቀበሌ ነዋሪዎች ከየሥራቸው ወደ ቤት ለመግባት ተቸግረው አመሹ:: ጉርፍና ጨለማ ካስቸገራቸው ሰዎች መካከል አንዱ አና ጢው አማረ ነው:: ዝናብ እየመታው ቶሎ ቶሎ ቢራመድም ጨለማው እየከበደ በመሔዱ መን ገዱንና እርሻውን መለየት አቃተው::

ቢቸግረው የብርሀን ጭላንጭል ወዳየበት ወደ አንዱ ቤት አቅጣጫ ሔደ:: ደጋግሞም ተጣራ:: ብቅ ያሉት አዛውንት ሁኔታውን በባትሪያቸው ብርሀን አይተው አዘኑለት:: ወደ ቤታቸው ገብቶ እንዲጠለል ጋበዙት::

አማረ ግን ልትወልድ የደረሰች ሚስቱ ተጨንቃ እንደምትጠበቀው ገልጾላቸው ባትሪያቸውንና ጥላ እንዲያውሱት ለመናቸው:: አዛውንቱም ጉህ ሲቀድ እንዲያመጣላቸው ቃል አስገቡት:: ቃሉንም እን ዲያከብር ደጋግመው አሳሰቡት:: አማረም የገ ባውን ቃልኪዳን እንደሚፈጽም አረጋገጠላቸው ና አመስግኖአቸው ወደ መንደሩ ተጓዘ:: እቤቱ ሲደርስ እንደገመተው ሚስቱ አቻሜ በር ላይ ቆማ ስትጠብቀው አገኛት:: ከዚያም ወደ ሞቀ ቤ ታቸው ገብተው፣ ራት በልተው፣ ቡና ጠጥተው በሰላም ተኙ:: ሊነጋጋ ሲል አቻሜን ምጥ ያዛት:: አማረም ተጨነቀ:: ወደ ጉረቤቶቹ በመ ሔድ የሚስቱን በምጥ መያዝ ነገራቸው::

እንደባህላችን በጉርብትና ወግ ሁሉም ሊረዷት ፈጥነው ተሰባሰቡ:: ጉህ እንደ ቀደደ ለአዛውንቱ የገባውን ቃል ላለማጠፍ ሚስቱን ለጉረቤቶቹ አደራ ሰጥቶ በሩጫ ገሠገሠ:: አንዳንድ ጉረቤ ቶችና ሚስቱም ጭምር ተቹት:: አድራጐቱንም ከጭካኔ ቆጠሩበት:: እሱ ግን ጥላና ባትሪውን ለማድረስ በሩጫ እንደሔደ በሩጫ ሲመለስ አቻሜ ሴት ልጅ ወልዳ እልል ሲባል ደረሰ::

### መልመጃ 3

***ከላይ በቀረበው ታሪክ መሠረት የሚከተ ሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ቅንነት የሚታየው በማን ተግባር ነው?
2. በአዛውንቱና በአማረ መካከል የተደረገው ቃልኪዳን እንዴት ተፈጸመ?
3. አማረ ሚስቱ በምጥ ተይዛ ወደ አዛውንቱ መሔዱ ጭካኔ ነው? ወይስ አይደለም?
4. በታሪኩ ውስጥ ሀቀኝነት እንዴት ተገለጸ?
5. አዛውንቱን ደግ ናቸው ካልን አማረን ምን እንለዋለን?

ቃልኪዳን ማለት አንድ ሰው የተናገረውን እንደ ሚፈጽመው ለሌላ ሰው የሚሰጠው የቃል መተ ማመኛ ነው:: የተናገረውን በተግባር ያሳየ ሰው እውነተኛ ታማኝ ሲባል፣ የተናገረውን በሥራ መተርጐም ያቃተው ደግሞ ቃል አባይ ተብሎ ይናቃል::

ቃልኪዳን ሰውን ለውጤታማ ሥራ የሚገፋፋ ኃይል ነው:: እያንዳንዱ ሰው ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለማኅበረሰቡና ለሀገሩ ቃልኪዳን መግባት አለ በት:: ለሀገር የሚገባ ቃል ኪዳን በሥራ ሲተረ ጐም የዜግነት ድርሻን መወጣትን ያመለክታል:: ለኅብረተሰቡ ኑሮ መለወጥ፣ ለሥልጣኔ መስፋ ፋትና ለሀገር ዕድገት የዜጐች ቃልኪዳን መግ ባት አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም ቃልኪዳን ወደተ ግባር የሚያራምድ የህሊና አንቀሳቃሽ ኃይል ነው::

በቤት ውስጥ የሥራን ድርሻ በአግባቡ ከተወ ጣችሁ ትምህርታችሁን በጥሩ ሁኔታ መከታተል ከቻላችሁ ቃል አክባሪ ትባላላችሁ:: ቃልን አክ ብሮ የመገኘት ኃላፊነት የሚጀምረው ከቤተሰባዊ የሥራ ተሣትፎ ነውና:: ይህም ሁኔታ እድገት እየጨመረ በትምርት ቤት ውስጥ በሚደረጉ ልዩ ልዩ ተሣትፎዎች ይዳብራል:: ለምሳሌ ተማሪ ነት በራሱ ቃል ኪዳን ነው:: ምክንያቱም ለጥሩ ውጤትና ብቃት ለመድረስ ተማሪዎች የሚሠ ሩት ሥራቸው መማር መማር ሁልጊዜም ጠን ክሮ መማር ነውና::

በተጨማሪም የክፍል አለቃ፣ የክበብ መሪና አስተ ባባሪ ሆኖ ተመርጦ ለማገልገል ቃል መግባትና ኃላፊነትንም ለመወጣት መነሳሳት ነው::

### መልመጃ 4

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ቃልኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቃሉን የማይፈጽም ሰው ምን ተብሎ ይጠራል?
3. የቃልኪዳን ጥቅም ምንድነው?

## 6.3 የቅነት፣ የታማኝነትና የሀቀኝነት ምንነት

### 6.3.1 ቅንነት፣ ታማኝነትና ሀቀኝነት ማለት ምን ማለት ነው?

**የነጩሎ ዕቁብ**

በአዲስ አበባ ደቡብ ለቡና ላፍቶ የሚባሉ ሁለት ሰፋፊ መንደሮች ይገኛሉ:: በመካከላቸው አንድ ሰፊ አደባባይና አስፋልት መንገድ ተሠርቷል:: በበጋም ሆነ በክረምት ወደ መንገዱና አደባባዩ ብዙ ነዋሪዎች ከየአቅጣጫው ይመጣሉ:: ጩሎና አምስት ጓደኞቹ ደግሞ የሰዎቹን ጫማዎች በክረምት ከጭቃ፣ በበጋ ከአቧራ በማጽዳት ዓመቱን ሙሉ በትጋት ይሠራሉ::

እነጩሎ ዓላማና ራዕይ አላቸው:: ትምህርት መማርና ሱቅ መክፈት ዋናዎቹ ዕቅዶቻቸው ናቸው:: ይህን እቅዳቸውን ለማሳካት ከገቢያቸው የተወሰነ ይቆጥባሉ:: በየቀኑ ሠርተው ከሚያገኙት ገቢ የሃምሣ ሣንቲም ዕቁብ ይጥላሉ:: ለዚህም ጩሎ ዳኛ፣ አረጋ ፀሐፊ፣ ቱሉ ገንዘብ ያዥ ሆነው ተመርጠዋል::

የአረጋ ተግባር በየወሩ በዕጣ ወረቀቶች ላይ ስም ጽፎ ጠቅልሎ ማቅረብ ነው:: ሆኖም የተሰጠውን ኃላፊነት በመዘንጋት ሁለት ሁለት ብር እየተቀበለ ማጭበርበርን ፈጸመ:: ይኸውም በሚጠቀልላቸው ወረቀቶች ላይ የአንድ ሰው ስም በተደጋጋሚ በመጻፍ የዕለቱ ዕጣ ያለተወዳዳሪ ለአንድ ሰው እንዲወጣ ማድረግ ነበር::

በአጭር ጊዜ ውስጥ ማንበብና መጻፍ በጥረቱ የተማረው አንዱ እቁብተኛ ግርማ፣ አረጋ ደጋግሞ የጻፈውን ስላነበበበት አጋለጠው:: እነጩሎም ባደረጉት ማጣራት አረጋ እምነት ማጉደሉንና ሀቀኛ አለመሆኑን አረጋገጡ:: በዚህ ጊዜ ሀቅ በመናገሩ አረጋ ግርማን ሊደበድበው ሞከረ:: ጓደኞቹም ታማኝነቱን በማጉደሉ ወቀሱት:: አረጋም በሠራው ስህተት ተፀፅቶ ይቅርታ ጠየቀ:: እነጩሎም ከቅንነት ውጭ የሆነ ሥራ በመሥራቱ የታማኝነትን ክብር እንዳጣ በመግለጽ ከስህተቱ እንዲማር መክረው ይቅርታ አደረጉለት:: የፀሐፊነቱን ኃላፊነት ደግሞ ለግርማ ሰጡት::

**መልመጃ 5**

*ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. እምነትን ማጉደል በታሪኩ መሠረት ውጤቱ ምን ሆነ?
2. የግርማ ተግባር ምንን ያመለክታል?
3. አረጋ ከፀሐፊነቱ መነሳቱ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?

ማንኛውንም ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ማከናወን ማለት በትህትናና በሠላማዊ ሁኔታ ያለሽፍጥና ማታለል ትክክለኛውን ጉዳይ መግለጽ ወይም በድርጊት ማሳየት ማለት ነው:: ታማኝነትም ኃላፊነትን በብቃት መወጣት ሲሆን ሀቀኝነት ደግሞ ቃልኪዳንን በተግባር ፈጽሞ መገኘትን ይገልጻል:: ሶስቱ ጽንሰ ሀሳቦች ተያያዥነት አላቸው:: አንዱ በሌላው ውስጥ ይገኛል::

ቅንነት፣ ታማኝነትና ሀቀኝነት ለእውነተኛ ተግባር መሠረት የሆኑ ባህርያት ናቸው:: በማንኛውም የሥራ መስክ ላይ የተሰማራ ሰው በሙሉ ኃይሉና እውቀቱ፣ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በትክክል ሠርቶ በማጠናቀቅ ውጤቱን ካሳየ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ተወጥቷል ማለት ነው:: ከዚህ ውጭ በራስ ወዳድነትና እምነትን በማጉደል ሥራን መበደል አሳፋሪና ሀገርን መበደል ነው:: ስለዚህ ብቁ ዜጋ ለመሆን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት ለመሥራት የህሊና ዝግጅት አድርጉ:: በቤት፣ በአካባቢ እንዲሁም በትምህርት ቤት ኃላፊነትን የመወጣት ልምድ ማዳበር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

**መልመጃ 6**

*ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡*

?

1. ራስ ወዳድነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የብቁ ዜጋ መገለጫው ምንድነው?
3. በትምህርት ቤት ተሣትፎ ቅንነት ታማኝነትና ሀቀኝነት የሚገለጹባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝሩ::

## 6.4 ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት





*ሥዕል 6.2 አካባቢን መንከባከብ ሀላፊነትን መወጣት ነው*

- አካባቢን መንከባከብን ባንፈቅድ ምን ችግር ሊፈጠር ይችላል?
- የአካባቢን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ተሣትፎ ምን ይባላል?
- ሰዎች የአካባቢያቸውን ችግር ለመፍ ታት የሚያደርጉት ተሳትፎ ምን ይባላል?

### እምዬ አስቴር

በብርሃን ጮራ ትምህርት ቤት በሚገኙ ልዩ ልዩ ክበባት መካከል በየዓመቱ ውድድሮች ይካሄዳሉ:: ባለፈው ዓመት አሸናፊውና ተሸላሚው የበጐ አድ ራጐት ክበብ ነበር:: የክበቡ ሊቀ መንበር አስቴር አበራ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነበረች:: ያለ መመሪ ያና ማሳሰቢያ በቤት ውስጥ ማከናወን ያለባ ትን ተግባር በደንብ ትሠራለች:: ሁልጊዜ በማ ለዳ ተነስታ ለዶሮዎች ጥራጥሬ ሰጥታ ማደሪ ያቸውን አጽድታ ጥራጊውን ለማዳበሪያነት በአት ክልት መደቦቿ ላይ ትበትናለች:: ውሻቸው እን ዲናፈስ ከፈታችው በኋላ ቤት ትጠርጋለች:: ከዚያም ተዘጋጅታ ቁርሷን በልታ ወደ ትምህርት ቤት ፈጥና በመሔድ በሰዓቱ ትደርሳለች:: በዚ ህም እናትዋና ጐረቤቶቻቸው የልብ አውቃ በማ ለት ያደንቋታል::

በትምህርት ቤትም የምትሳተፍበት ክበብ ውጤ ታማነት በትጋት ትሠራለች አባላቱንም ታስተ ባብራለች:: ትምህርት ቤቷን ወክላ በተሣተፈች በት የጥያቄና መልስ ውድድር አሸንፋ አንድ ሺህ ብር ተሸልማለች:: የተሸለመችውን ብር ለበጐ አድራጐት ክበብ በመስጠት ጠቃሚ ተግባር እን ዲሠራበት አድርጋለች::

ክበቡ በኑሮ ችግር ትምህርታቸውን መከታተል ያልቻሉትን ተማሪዎች ይረዳል:: ችግረኛ ልጆች በአቅማቸውና በትርፍ ጊዜያቸው በመሥራት ራሳቸውን እንዲረዱ የምክርና የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል:: ይህም የሥራን ባህል እንዲያ ዳብሩ መሠረት ሆኖአቸዋል::

ከዚህም ሌላ አስቴር በሰፈሯ የወጣቶች የልማት ኮሚቴ ተሣታፊ ነች:: ቀበሌው በሰጣቸው ቦታ ላይ ከሚሠራው የልማት ውጤት ገቢ በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ በኤድስ የተጐዱ ሰዎች ይረዱ በታል:: በየወሩ በሚደረገው የቦይ መጥረግ፣ የቆ ሻሻ ማስወገድና የፀረ-ኤድስ ትምህርት ላይ በብ ቃት ትሠራለች::

ሕሙማንና አረጋውያንን በርኅራኄ ስለምትረዳ በብዙዎች ዘንድ የተመሰገነችና የተመረቀች ናት:: ስለዚህም አስቴር በዕድሜዋ ሳይሆን በሥራዋ "እምዬ" እየተባለች ትጠራለች::

**መልመጃ 7**

***ከምንባቡ በመነሣት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::***

?

1. ኃላፊነት መወጣት ማለት ምን ማለት ነው?
2. አስቴር በቤት፣ በትምህርት ቤትና በአካ ባቢዋ የምትሠራቸውን ተግባራት ዘርዝሩ::
3. እንደ አስቴር ሁሉ ኃላፊነታችሁን ትወጣላችሁ? እንዴት?

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኃላፊነትን መወጣት ማለት በራስ ተነሳሽነት ወይም ከሌሎች እንዲከናወን የተሰጠን ሥራ በብቃትና በታማኝነት መሥራት ማለት ነው። እያንዳንዱ ሰው በግልና በጋራ ኃላፊነትን የመወጣት ግዴታ አለበት። ተማሪ ስለሆናችሁ ትምህርታችሁን በአግባቡ መማርና በብቃት ማጠናቀቅ ልትወጡት የሚገባ የግል ኃላፊነት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በቤተሰብና በአካባቢ ሥራ ከሌሎች ጋር ተሣትፎ ማድረግ ደግሞ የጋራ ኃላፊነትን ማከናወን ነው። በአካባቢ ልማት መሳተፍ በራስ ተነሳሽነት ኃላፊነትን የመወጣት ምሳሌ ነው።

ኃላፊነትን መወጣት ለአስተሳሰብና ለኑሮ ለውጥ፣ ለሥልጣኔና ብልጽግና መምጣት፣ በአጠቃላይም ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት በተሠማራበት ተግባር ኃላፊነቱን የሚወጣ ከሆነ እድገትና ለውጥ ሊመጣ ይችላል።


**መልመጃ 8**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. የሥልጣኔና የዕድገት መሠረቱ ምንድነው?
2. ከእናንተ የሚጠበቀውን ኃላፊነት የምትወጡት እንዴት ነው?
3. በራስ ተነሳሽነት የሚከናወኑ ሥራዎችን ጥቀሱ።

## 6.5 የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርስ ምንነት፤



*ሥዕል 6.3 የጢስ ዐባይ ፏፏቴ*



*ሥዕል 6.4 የጢያ ትክል ድንጋይ*

- የጢስ ዐባይ ፏፏቴ ታዋቂነቱ በምንድነው?
- የጢያ የድንጋይ ሀውልቶች የሚገኙት የት ነው? ስለ ሀውልቱ የምታውቁትን ግለጹ፡፡
- ከሥዕሎች የትኛው የተፈጥሮ ሀብት፤ የትኛው ደግሞ ታሪካዊ ቅርስ እንደሆነ ለዩ፡፡

### የጫልቱ ሽልማት፤

***አቶ ደጀኔ፣*** ልጄ የምትፈልጊውን ነገር ልሸልምሽ አስቤያለሁ። ምን እንዳደርግልሽ ትወጃለሽ?

***ጫልቱ፣*** የምትሸልመኝ በምን ምክንያት ነው አባዬ?

***አቶ ደጀኔ፣*** ከክፍል አንደኛ በመሆንሽና ትምህርትሽን በአግባቡ በማጠናቀቅ ኃላፊነትሽን በመወጣትሽ ስለተደሰትኩ ልሸልምሽ አቅጃለሁ።

***ጫልቱ፣*** አመሰግናለሁ አባዬ፤ ሽልማቴ ሽርሽር ቢሆንልኝ እመርጣለሁ።

***አቶ ደጀኔ፣*** ጥሩ ሀሳብ ነው ጫልቱ። ወዴት ልውሰድሽ?

***ጫልቱ፣*** በተማርነው መሠረት በሀገራችን አስደናቂ የተፈጥሮ ሀብቶችና ልዩ ልዩ ታሪካዊ ቅርሶች መኖራቸውን አውቀናል። ከነዚያ አንዳንዶቹን ብታሳየኝ በጣም እደሰታለሁ።

***አቶ ደጀኔ፣*** ግሩም ሀሳብ ነው ጫልቱ። ለመሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው?

| | |
|---|---|
| ***ጫልቱ፣*** | የተፈጥሮ ሀብት ማለት በመሬት ላይና በመሬት ውስጥ እንዲሁም በውሀ ውስጥ በተፈጥሮ የሚገኙ ናቸው:: |
| ***አቶ ደጀኔ፣*** | ጥሩ ተገንዝበሻል ጫልቱ፣ ታሪካዊ ቅርስ የሚባለውስ ምንድነው? |
| ***ጫልቱ፣*** | ታሪካዊ ቅርሶች ደግሞ ሕዝቦች በረዥም ዘመናት ውስጥ የሠሯቸውና ለትውልድ የተላለፉ ቤተመንግሥቶች፣ ሀውልቶች፣ ስዕሎችና የመሳሰሉት ናቸው:: |
| ***አቶ ደጀኔ፣*** | መልካም ነው:: መሠረታዊውን ሀሳብ ጨብጠሻል:: በሚቀጥለው ክፍል ደግሞ በስፋት ትማሪያለሽ:: በተፈጥሮ ሀብትነትና ቅርስነት ከሚጠቀሱት መካከል በዚህ ዓመት ሁለቱን ላስጎበኝሽ እችላለሁ:: |
| ***ጫልቱ፣*** | በጣም ደስ ይለኛል አባዬ:: ስላየሁት ታሪካዊ ቦታና አካባቢ ዘገባ ጽፌ ለክፍል ጓደኞቼ ለማቅረብ እዘጋጃለሁ:: የት ልትወስደኝ አስበሃል አባዬ? |
| ***አቶ ደጀኔ፣*** | በዚህ ዓመት በጉራጌ ዞን ሶዶ አካባቢ የሚገኘውን የጢያ የድንጋይ ሀውልቶችና አምቦ አካባቢ የሚገኘውን የወንጪ ሐይቅን አስጎበኝሻለሁ:: ሀይቆችና በውስጣቸው የሚገኙ ነገሮች ሁሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው:: |
| ***ጫልቱ፣*** | አመሰግናለሁ አባዬ:: እኔም ዘገባዬን ለመጻፍ ማስታወሻ ደብተሮቼን አዘጋጃለሁ:: |

***መልመጃ 9***

***ከላይ የቀረበውን ውይይት መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የጫልቱ አባት የተደሰቱት ለምንድ ነው?
2. የምታውቋቸውን የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ምንነታቸውንና የት እንደሚገኙ ግለጹ::
3. የተፈጥሮ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው? ታሪካዊ ቅርስስ?

**የተፈጥሮ ሀብቶች** የሰው ልጆች በእውቀታቸውና በሥራ ልምዳቸው ሳያሻሽሏቸው በተፈጥሮ ያሉ ነገሮች ሁሉ የፈተጥሮ ሀብቶች ይባላሉ:: እነዚህም ከመሬት በላይ፣ ከመሬት ውስጥ፣ በባሕርና በሐይቆች ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ነገሮች ናቸው:: ለምሳሌ ከመሬት በላይ ደን፣ ልዩ ልዩ ዕፅዋት፣ አራዊት፣ አእዋፋት ወንዞች፣ ፏፏቴዎች፣ እንስሳት ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው:: ከመሬት ውስጥ ደግሞ፤ ፈሳሽና ጠጣር ማዕድናት፣ ማለትም ወርቅ፣ ነሀስ፣ ብረት፣ ጋዞች ሌሎችም ይካተታሉ::

እንዲሁም በውሀ ውስጥ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ፍጥረታት ሁሉ በተፈጥሮ ሀብትነት ይታወቃሉ:: በሀገራችን ከታወቁት የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል፣

- የጢስ ዐባይ ፏፏቴ፣ አዋሽ፣ ተከዜ፣ ገናሌ ወዘተ ወንዞቻችን፣
- ጫሞ፣ አዋሳ፣ ላንጋኖና ጣና ሌሎችም ሐይቆቻችን፣
- በአዋሽ፣ በባሌ፣ በነጭ ሣር፣ በሰሜን ተራሮች ውስጥ የሚገኙ አራዊትና አእዋፋት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው::

የተፈጥሮ ሀብቶችን ማልማት ለሰዎች ሕልውና ብዙ ጠቀሜታ አለው:: ለሕዝቦች የጋራ ዕድገትም ሰፊ አገልግሎት ይሰጣል:: እያንዳንዱ ዜጋ የተፈጥሮ ሀብቶችን ጠንቅቆ የማወቅ የማልማትና የመጠበቅ ግዴታ አለበት:: ይህም ኃላፊነትን የመወጣት አንዱ ገጽታ ነው:: ለምሳሌ ደንን መንከባከብ በቀላሉ ከእያንዳንዱ ሰው መኖሪያ አካባቢ ይጀምራል::

እናንተም በግቢያችሁ ውስጥ ዛፎችንና እጽዋትን በመትከል አካባቢን በልምላሜ እንዲሸፈን ብታደረጉ የአካባቢ አፈር በውሀ እንዳይሸረሸርና እጽዋት እንዳይወድሙ ይረዳል:: በዚሁ ሁኔታ ሁሉም የድርሻውን ቢሠራ በመውደም ላይ ያለው ደናችን ያንሠራራል:: የወንዞችም ሆነ የሐይቆች ውሀ በአግባቡ በጥቅም ላይ ከዋለ ለልማቱ እገዛ ያደርጋሉ:: ደንን መንከባከብ ለአራዊትና ለአእዋፋት መኖር ዋስትና ሲሆን ለእርሻ ሥራ እጅግ ጠቃሚ የሆነውን አፈርም ከመታጠብ ይድናል::

ታሪካዊ ቅርሶች የሚባሉት ሕዝቦች በኖሩባቸው ዘመናት የሠሯቸው የጥበብ ውጤቶች ናቸው:: እነዚህ ውጤቶች ለትውልድ በመተላለፍ በታሪክ ማስረጃነት ያገለግላሉ:: የሠሯቸው ሕዝቦች የነበራቸውን የሥልጣኔ ደረጃ ያስረዳሉ:: ታሪካዊ ቅርሶች ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቁሳቁሶች፣ ሀውልቶች፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ ቤተ መንግሥታት፣ መስጊዶች፣ ሥዕሎችና የመሳሰሉት ናቸው:: ቅርሶቹ እንክብካቤና ጥበቃ ካልተደረገላቸው ይወድማሉ:: የቅርስ ውድመት ደግሞ የታሪክ ውድመት ነው:: ታሪካዊ ቅርሶች የጋራ ንብረቶቻችን በመሆናቸው ሁላችንም ልንጠብቃቸው ይገባል::

ማንኛውም ሰው ረዘም ያለ ጊዜ ያስቆጠሩ በስጦታ ወይም በውርስ ያገኛቸውን ንብረቶች በቅርስነት መመልከትና መጠበቅ አለበት:: በመሆኑም የግልም ሆኑ የጋራ ታሪክና ጊዜን የሚጠቅሱ ቅርሶችን ለይተን ማወቅና መጠበቅ ግዴታችን ነው:: የማንነታችን መገለጫ የሆኑት ቅርሶች እንዳይወድሙ፣ እንዳይሰረቁና እንዳይሸጡ መንከባከብ ያስፈልጋል::

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. የተፈጥሮ ሀብት ካልተጠበቀ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድነው?
2. የሰዎችን ጥበብ ችሎታና የነበሩበትን የሥልጣኔ ደረጃ የሚጠቁመን ምን ይባላል?
3. በምንባቡ ውስጥ ከተገለጹት ታዋቂ ቦታዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች ወይም የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ በማጥናት ለክፍል ተማሪዎች ግለጹ::
4. የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ የእናንተ ድርሻ ምን መሆን አለበት?

## 6.6 ኤች አይ ቪ / ኤድስ

ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በዓለም ላይ እስከዛሬ መድኃኒት ያልተገኘለት ተላላፊ በሽታ ነው:: ሰውነትን በማዳከምና በሽታዎችን የመከላከል አቅም በማሳጣት ለሞት ያበቃል:: ይህ ተላላፊ በሽታ በመዛመት በዓለም ውስጥ ወደ የትኛውም ሀገርና አህጉር ተሠራጭቷል:: ሀገራችንም ከገጠር እስከ ከተማ በበሽታው መስፋፋት በመጠቃት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ሆናለች::

ይህ በሽታ እናትና አባትን በሚገልበት ጊዜ ቤተሰብ ይጐዳል:: ልጆች ያለሰብሳቢ ይቀራሉ:: ትምህርታቸውንም መቀጠል አይችሉም:: ከችግርም የተነሣ ለጐዳና ኑሮና ለእንግልት ይዳረጋሉ:: ይህ ሁኔታ ሀገር ተረካቢ የሆኑትን ልጆች እድገት ያሰናክላል:: ሀገራችንንም አምራችና የተማረ ዜጋ ያሳጣታል:: ስለዚህ ይህን አስከፊና አስቸጋሪ የሆነ በሽታ ከመስፋፋት ለማቆምና ለመከላከል የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ማወቅ አለብሽ/ አለብህ:: መተላለፊያ መንገዶቹን ካወቅሽ/ህ በኋላ ራስሽን/ ራስህን በበሽታው ከመያዝ በመከላከል ኃላፊነትታችሁን ልትወጡ ይገባል።

***ኤድስ የሚተላለፍባቸው መንገዶች***

- ኤድስ ወይም ቫይረሱ ያለበት ሰው በተወጋበት መርፌ ጤነኛው ሰው ሲወጋ፣
- የሕመምተኛው ሰው ደም ወደ ጤነኛው ሰው ደም ውስጥ ሲቀላቀል፣
- በኤድስ የተያዘ ሰው በተጠቀመባቸው ስለታም መሣሪያዎች፣ (ምላጭ፣ ጥፍር መቁረጫ ወዘተ) ጤነኛው ሲጠቀም፣
- ቫይረሱ ያለበት ሰው በተጠቀመበት የጥርስ ብሩሽ ወይም መፋቂያ ጤነኛው ሲጠቀም፣

**መልመጃ 11**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው::***

?

1. የኤድስ መከላከያ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?
2. የወላጆች በኤድስ መሞት ልጆችን የሚጐዳው እንዴት ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ማንኛውም ዜጋ የሀገሩ አለኝታ ነው፡፡ ሀገርን የሚረከብ ዜጋ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት መቻል አለበት:: በተሰጠው ወይም በፈቃደኝነት በጀመረው በማንኛውም ዓይነት ሥራ ላይ ውጤት ያመጣል፡፡ በታማኝነትና በቅንነት አንድን ሥራ ማከናወን ከቻለ ቃል ኪዳኑን የጠበቀና የታመነ ዜጋ ነው ፡፡

ኃላፊነትን መወጣት ከሚገለጹባቸው ሁኔታዎች አንደኛው የሀገር ቅርስና ሀብት የሆኑትን ንብረቶች በባለቤትነት መንከባከብና መጠበቅ ነው፡፡ የሀገር ሀብት በአግባቡ ስልማት ከዋለ ለሥልጣኔና ለብልጽግና መሠረት ስለሆነ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል። ለዚህ ዋነኛ ምሳሌ አድርገን የምንጠቅሰው የአፈራችን በከፍተኛ ፍጥነት እየታጠበ መሔድ ነው፡፡ ቅርሶቻችንም ቢሆኑ እንክብካቤና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፡፡

አስቀድሞ እንደተገለጸው ዜጐች ዋነኛ የሀገር ሀብቶች ናቸው፡፡ ራሳቸውን በትምህርትና በእውቀት በማነጽ አምራች ዜጐች እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለመማርም ሆነ አምራች ሆኖ ሀገርን ለመገንባት በቅድሚያ ጤናማ መሆን ወሳኝነት አለው፡፡ በከፍተኛ ፍጥነት በዓለም ላይ እየተዛመተ ያለውን ኤች.አይ.ቪ /ኤድስን መከላከል አለብን፡፡ መተላለፊያ መንገዶቹ የተጠቀሱ በመሆናቸው ከነዚህ ራስን በመጠበቅ ኤድስን መከላከል ሌላኛው ኃላፊነትን የመወጣት ገጽታ ነው፡፡ ምንም እንኳን ካለማወቅና ካለመጠንቀቅ ሰፊ ጥፋት በማድረስ ላይ ቢገኝም፣ ኤድስ ልናሸንፈው የምንችል ጠላታችን መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| ኃላፊነትን መውሰድ፣ | ተግባርን በአግባቡ ለመወጣት መወሰን:: |
| ቃል ኪዳን፣ | የቃል መተማመኛ ወይም ተስፋ:: |
| ቅንነት፣ | ደግነት የሚንፀባረቅበት ጥሩ ባህርይ:: |
| ታማኝነት፣ | ቃል ኪዳን አክባሪነት:: |
| ሀቀኝነት፣ | እውነተኛነት:: |
| የተፈጥሮ ሀብት፣ | በሰዎች ዕውቀት ያልተፈጠረ ሀብት (ውሀ፣ መሬት፣አየር):: |
| ታሪካዊ ቅርስ፣ | ያለፉ ዘመናትን ታሪክና ሥልጣኔ ማስረዳት የሚችል ከትውልድ የተላለፈ ሀብት:: |
| ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ፣ | መድኃኒት ያልተገኘለት ተላላፊና ገዳይ በሽታ:: |
| ስለታም መሣሪያ፣ | በቀላሉ ቆዳን መቁረጥ የሚችል መሣሪያ (ምላጭ፣ ስለታም ነገር፣ ወዘተ):: |
| ጉህ ሲቀድ፣ | ሲነጋጋ፣ ንጋት ሲጀምር። |
| ቃለ አባይ፣ | ዋሾ። |

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::***

### I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ቃል መግባት ለእምነት መተማመኛ መስጠት ነው::
2. ተፈጥሮን መንከባከብ የአዋቂዎች እንጂ የወጣቶች ኃላፊነት አይደለም::
3. ቅርስን መጠበቅ ኃላፊነትን መወጣት ነው::
4. ሀቀኝነት ሌላው የእውነተኛነት መጠሪያ ነው::
5. ኤድስን መዋጋት ከኃላፊነት ጋር ግንኙነት የለውም::

### II. በ “ለ” ሥር የተዘረዘሩትን በ“ሀ” ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አርአያነት፣ | ሀ/ ተስፋና የመተማመኛ ቃላት። |
| 2. ቅርስ፣ | ለ/ በሰዎች ጥበብ ያልተሠራ። |
| 3. ኃላፊነትን መወጣት፣ | ሐ/ ተላላፊ በሽታ። |
| 4. የተፈጥሮ ሀብት፣ | መ/ ምሳሌነት። |
| 5. ታማኝነት፣ | ሠ/ የታሪክ ማስረጃ። |
| 6. ኤድስ፣ | ረ/ የሥራ ውጤት ማሳየት። |
| 7. ቃልኪዳን፣ | ሰ/ አለመዋሸት። |
| | ሸ/ ግዴለሽነት። |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ኃላፊነት መወጣት የሚገለጽበት፤
   ሀ. ትምህርትን በአግባቡ መማርና ጥሩ ውጤት ማምጣት፣
   ለ. የጥናት ጊዜ እንዳያንስ በቤት ውስጥ ሥራ አለመሳተፍ፣
   ሐ. የአካባቢ ልማትና ጽዳት የቀበሌ ተግባር ብቻ ነው ማለት፣
   መ.በአቧራ ላለመቆሸሽ መማሪያ ክፍልን አለማጽዳት።
2. ቅርስን መንከባከብ የማን ኃላፊነት ነው?
   ሀ. የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ሐ. ዜጎች፣
   ለ. የመንግሥት ባለስልጣናት፣ መ. ሁሉም መልስ ይሆናል::
3. ኒያላ፣ ዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ፤
   ሀ. የአገር ቅርስ ናቸው፣
   ለ. የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፣
   ሐ. በየትኛውም ክፍለ ዓለም የሚገኙ የአራዊት ዝርያ ናቸው፣
   መ. ሀ እና ለ መለሶች ናቸው::
4. ለሀገር ሥልጣኔና ዕድገት ጠቃሚው፤
   ሀ. የዜጎች መማር ነው፣
   ለ. ዘመኑ በፈጠራቸው የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች መጠቀም ነው፣
   ሐ. በእውቀት የተደገፈ ሥራን በአጥጋቢ ውጤት ማከናወን ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው::

5. ራስን ከኤች. አይ.ቪ/ኤድስ አለመጠበቅ፣
   ሀ. ግዴታን መወጣት ነው፣
   ለ. ለሕይወት ዋጋ አለመስጠትና ኃላፊነትን አለመወጣት ነው፣
   ሐ. ቅድሚያ ለትምህርትና ለጥናት ትኩረት መስጠት ነው፣
   መ. ቃልኪዳንን አክብሮ መገኘት ነው፡፡

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ዘመንና ታሪክን ባህልና ወግን የሚገልጹ ነባር ሀብቶች____________ይባላሉ ፡፡
2. በዓለም ላይ በአሁኑ ጊዜ መድሐኒት ያልተገኘለት በሽታ____________ነው፡፡
3. በቴክኖሎጂና በሳይንስ ጥበብ ያልተሠራ ሀብት ____________ተብሎ ይጠራል፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው እንዴት ነው ?
2. ቃልኪዳንና ታማኝነት ምን ማለት ነው? እንዴት ይገለጻሉ? በምሳሌ አስረዱ፡፡
3. ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት እንዴት መንከባከብ አለባቸው?

# ምዕራፍ ሰባት

# ጠንካራ የሥራ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ ስታጠናቅቂ፤***

- የጠንካራ የሥራ ባህልን ምንነት ትረዳለህ/ ትረጃለሽ፤
- የሙያ ሥነ ምግባር ምንነትን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፤
- የሥራ ክቡርነትን ትረዳለህ/ትረጃለሽ።

## 7.1 ሥራን መፍጠር

### 7.1.1 ሥራን መፍጠር ማለት ምን ማለት ነው?



*ሥዕል 7.1 በተለያዩ ሙያዎች የተሰማሩ ሰዎች በሥራ ላይ*

- ከላይ ከቀረቡት ሥዕሎች የተረዳችሁትን ግልፁ።
- በሥዕሎቹ ላይ የምታዩዋቸውን ዓይ ነት ተግባራት ስለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

ሥራ መፍጠር ማለት ችሎታን ተጠቅሞ ምርት ወይም ገቢ ለማስገኘት የሚያስችል አዲስ የሥራ ዓይነት ፈጥሮ መሥራት ማለት ነው፡፡

**ትንሿ የብረታ ብረት መሥሪያ ግቢ**

ድምቡ የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ሁልጊዜ የሰጡትን የቤት ሥራ በሚገባ ስለሚሠራ መምህሩ ጎበዝ እያሉ ያበረታቱታል፡፡ ግን አልፎ አልፎ ልብሱ ቆሻሻ ይነካበት ስለነበር ምክንያቱን ይጠይቁታል፡፡ ድምቡም አቅሙ በፈቀደ መጠን በግቢያቸው ውስጥ ባለው የብረታ ብረት ሥራ ውስጥ አባቱን በሥራ የሚያግዝ መሆኑን ይገልፅላቸው ነበር፡፡ መምህሩና ተማሪዎች በነድምቡ ግቢ በአካል ተገኝተው ስለዚህ ሁኔታ ለማየት ፍላጎት አደረባቸው።

አንድ ቀን ድምቡ መምህሩንና ጓደኞቹን ለጉብኝት ወደቤቱ ለመወሰድ ጥያቄ አቀረበ፡፡ መምህሩና ጓደኞቹም ግብዣውን በደስታ ተቀብለው ወደ ነድምቡ ቤት ሄዱ፡፡ እዚያ እንደደረሱ በእነ ድምቡ ግቢ ውስጥ አንድ አነስተኛ የብረታ ብረት መሥሪያና መገጣጠሚያ ማሽኖችን አዩ፡፡

በዚያ ሥፍራ የድምቡን አባት ጨምሮ አምስት የሚሆኑ የጠቋቆረ ቱታ የለበሱ ሠራተኞች ነበሩ፡፡ ሠራተኞቹ በተለያየ መሣሪያ ብረት ሲቆርጡ፣ ሲያግሉና ሲቀጠቅጡ ተመለከቱ፡፡ በዚያ ሥፍራ አንዱ ሲሠራ ሌላው ቆሞ ሳይመለከት በትጋት ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡

የድምቡ መምህርና የክፍል ጓደኞቹ ባዩት ነገር በጣም ተደሰቱ:: ሠራተኞቹ በጣም ፈጣኖችና ሥራቸውን የሚያከብሩ መሆናቸውን ከሚያደርጉት የሥራ እንቅስቃሴ ተገነዘቡ። በግቢው ውስጥ ብዙ የሚሠሩ ዕቃዎችንና የበር መዝጊያም ሆነ መስኮት የሚያሠሩ ደበንኞችን ተመለከቱ::

ባለፈው ሳምንት የተማሩትን ማለትም "ጠንካራ የሥራ ባህል" የሚለውን የትምህርት ርዕስ አስታወሱ:: መምህራቸው በክፍል ውስጥ ያስተማሯቸውን በዚህ ትንሽ ብረታ ብረት መሥሪያ ቦታ በተግባር ተመለከቱ:: መምህሩና ተማሪዎቹ ድምቡ ከትምህርት ቤት መልስ መሣሪያ በማቀበልና በመላላክ እንደሚያገለግል ከድምቡ አባት ሲሰሙ ይበልጥ አደነቁት::

## መልመጃ 1

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. ከታሪኩ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::
2. ከነድምቡ ሠራተኞች ምን ትማራላችሁ?
3. ከድምቡ ተግባር ምን ተረዳችሁ?

### ታጠቁ ለሥራ

ማጣት ድንቁርና - ድህነት በሽታ፣
በተባበረ ክንድ - በሥራ እንዲረታ::
ሁላችሁ ተነሱ - ለሥራ ዝመቱ፣
ሀገር ማደጊያዋ - ዛሬ ነው ጊዜያቱ::
እንደጉንዳን ሕብረት - እንደንብ ታታሪ፣
ጥበብን ፈላጊ - ዕውቀትን መርማሪ፣
የነገ ትልቅ ሰው - የዛሬ ተማሪ::
ጥገኝነት ፀያፍ - መሆኑን አውቃችሁ፣
ሳይሠሩ መብላትን - ሥንፍናን ንቃችሁ፣
ትንሽ ትልቅ ቀርቶ - ሥራን አክብራችሁ፣
በርትታችሁ ሥሩ - በአንድነት ሆናችሁ::

## መልመጃ 2

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት መልሱ::***

?

1. ግጥሙን ካነበባችሁ በኋላ የተረዳችሁትን ሀሳብ በአጭሩ ገልፃችሁ ፃፉ::
2. በግጥሙ 5ኛ፣ 6ኛና 7ኛ መስመር የተገለፀውን ሀሳብ ለመምህራችሁ አብራሩላቸው::
3. በግጥሙ ውስጥ «ጥገኝነት ፀያፍ መሆኑን አውቃችሁ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

### ሰናይት

ሰናይት ፈቀደ ልጅ ሳለች ከዕለታት ባንደኛው ቀን እናትና አባቷ ስለጀመሩት የግል ሥራ ሲወያዩ ትሰማ ነበር:: ወዲያው የራሷን ሥራ ለመፍጠር አንድ ሃሳብ ይፈልቅላታል:: ይህም ሰዎች ተጠቅመው የሚጥሏቸውን የተለያዩ ብልጭልጭ ወረቀቶችን በመልቀም መሸጥ ነበር::

ሰናይት በምትኖርበት አካባቢ ባህላዊ ስፌት እየሰፉ በማስጌጥ የሚተዳደሩ ባለሙያዎች ነበሩ:: እነዚህ ሰዎች ብልጭልጭ ወረቀቶችን ለስፌት ማስጌጫ ስለሚፈልጓቸው ሰናይት የሰበሰበቻቸውን ወረቀቶች የሚገዙ ብዙ ደንበኞች አፈራች::

እንዲህ እያለች ባጭር ጊዜ ውስጥ ሌላ ንግድ ለመጀመር የሚያስችላት ወረት አጠራቀመች:: ከዚያም የትራስ ልብስ ጠልፎ በመሸጥ ሥራ ላይ ተሰማራች:: ቀጥሎም የገንዘብ አቅሟን በማዳበር ወደ ሌላ ስራ ተረማመደች::

ቀስ በቀስም እያደገች ስትሄድ በልብስ ስፌት በመሠልጠን የራሷን የልብስ ዲዛይንና የስፌት ሱቅ ከፈተች:: እንዲሁም ልዩ ልዩ የሙሽራ ልብሶችን በማከራየት የገቢ ምንጯን አዳበረች::

የፈጠራ ሥራዋን ለማሻሻል የሚያስችሏትን የልብስ ስፌት መኪኖችና ዘመናዊ የልብስ ቅድ መሣሪያዎችን ገዛች:: ሠናይት በአሁኑ ወቅት በአካባቢዋ የታወቀች የልብስ ስፌት ባለሙያ ለመሆን በቅታለች::

**መልመጃ 3**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በታሪኩ ውስጥ ሰናይት ሥራ ስመፍ ጠር ያሰበችው በምን ምክንያት ነው?
2. ከሰናይት ምን ምን ነገሮችን ስመማር ቻላችሁ?
3. እናንተስ ወደፊት ምን ዓይነት ሥራ ስመሥራት ታስባላችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

ሁሉም ሰው የፈለገውን የሥራ ዓይነት በመፍ ጠርና በማሻሻል ወደ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ ይችላል፡፡ አንድ ሰው ሥራን ፈጥሮ ለመኖር በቅድሚያ የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. *የሥራን ክቡርነት መረዳት፣* ሥራን ትንሽ ትልቅ ነው ብሎ ሳያማርጡ በሥራ ክቡርነት በማመን ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት መዘጋጀት፤
2. የራስ ተነሳሽነት፣ አንድ ሰው ሥራ መፍ ጠርና መሥራት አለብኝ ብሎ ራሱን ለሥራ ማዘጋጀትና መንቀሳቀስ፤
3. ጥረትን ማዳበር፣ ሥራን ለመፍጠርና የሥራ ፈጠራን በየጊዜው ለማሻሻልና ለማዳበር ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ።

የሰው ልጅ የራሱን ኑሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻ ሻለና እየለወጠ የመጣው በሥራ አማካይነት ነው፡፡ ሰው ሥራን ጠንክሮ በመሥራቱ ጥንት ከነበረበት ኋላቀር የአኗኗር ዘዴ ወደተሻለና ወደ ዘመናዊ የኑሮ ደረጃ ሊደርስ ችሏል፡፡

ዛሬ የምናያቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሁሉ የሰው ልጅ የሥራ ውጤቶች ናቸው፡፡ የአንድ ሕዝብ ጠንካራ የሥራ ባህል ሲዳብር ሀገሩንና ወገኑን ወደ እድገት ደረጃ ሊያሸጋግርና በዚህም ራሱንና ቤተሰቡን ሊረዳ ይችላል፡፡

ሥራን ትንሽ ወይም ትልቅ ብሎ መምረጥ ተገቢ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ልማትና ዕድገት ሊመጣ አይችልም፡፡ የሥራ ትንሽ ወይም ትልቅ የሚባል ምርጫ መኖር የለበትም፡፡ ማንኛውም ሥራ ክቡር ነው፡፡ ለምሳሌ እናንተ ሥራ ለመ ፍጠር ታስቡ ይሆናል፡፡ ይህ ታላቅ ነገር ነው፡፡ ማሰቡ ብቻ ሳይሆን ለመፍጠር የምታስቡትን ሥራ ሳትዘገዩ ወደተግባር መለወጥ ይገባችኋል፡፡

**ማንኛውም ሥራ ክቡር ነው።**

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ስመሆኑ ሥራን ፈጥሮ እየሰሩ ስመኖር በእናንተ በኩል ምን ምን ያስፈልጋ ችኋል? በደብተራችሁ ላይ ዘርዝሩና ስመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡
2. ጠንካራ የስራ ባህል ስሀገር ልማት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ግለፁ፡፡
3. ሰዎች ስለ ሥራ ክቡርነት ሲናገሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በደብተራችሁ ላይ ዘርዝሩና ስመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡

## 7.2 ሳይሰሩ መብላት

### 7.2.1 ሳይሰሩ መብላት ምን ማለት ነው?

- ልጆች እናንተ ከትምህርት ቤት መልስ የምትሰሩት ሥራ አለ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡
- ሳይሠሩ መብላት መጥፎ መሆኑን የሚገልጽ አንድ ምሳሌ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

ሳይሠሩ መብላት ማለት ሌሎች ሰዎች በለፉበትና በደከሙበት ውጤት መጠቀም ማለት ነው፡፡ ሰዎች ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ለማገዝ በሥራ መሳተፍ አለባቸው። ማንም ሰው በቤተሰብም ይሁን በሕብረተሰብ አባልነቱ ሥራ ካልሠራ የሌሎች ሸክም ሆነ ማለት ነው፡፡

ሳይሠሩ መብላት ደግሞ በሰዎች ዘንድ አስነ ዋሪና የሚነቀፍ ድርጊት ነው:: ሠራተኛ ሰው ለራሱም ሆነ ለሀገር የሚጠቅም ተግባር የሚያ ከናውን ስለሆነ በሰዎች ዘንድ የሚወደድና የሚከበር ነው::

**መልመጃ 5**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

1. ሳይሠሩ መብላት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሥራ መሥራት ያለብን ለምንድን ነው?
3. ሳይሠሩ መብላት የሚጐዳው ማንን ነው?

### 7.2.2 ሳይሠሩ መብላት የሚያስከትላቸው ችግሮች

- በእናንተ አቅም መሠራት አለባቸው የምት ሏቸውን ሥራዎች ዘርዝሩ::

ሥራ የሰው ልጆች የመኖር ዋስትና ነው:: አንድ ሰው ካልሥራ ጤናማና የተሟላ ኑሮ ለመኖር አይችልም፡፡ ሰው ለመኖር ቢያንስ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ያስፈልገዋል:: እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ደግሞ ሥራ መሥራት ይኖርበታል::

ሥራ መሥራት እየቻለ የማይሠራ ሰው በማ ንም ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ሥራ ሣይሠሩና ሳይደ ክሙ መኖር ይፈልጋሉ:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች እነሱ ሳይሠሩና ሳይደክሙ ሌሎች የሠሩትን የሚበሉ ናቸው:: ይህ ተገቢ አይደለም:: እነሱ ሳይሠሩ ሌሎች የሠሩትን የድካም ፍሬ ስለ ሚካፈሉ የሠራተኞች ድርሻ ትንሽ ይሆናል:: በዚህ ምክንያት ሁሉም ሰው በአቅምና በችሎ ታው ለመሥራት ካልተጣጣረ የሰዎች የኑሮ ሁኔታ ሊሻሻል አይችልም:: የሀገር ዕድገትም አይኖርም:: ሰዎች ሥራ ሳይሠሩ መኖር የሚፈ ልጉ ከሆነ ጥገኝነት ይስፋፋል:: ጥገኝነት ማለት የሌሎችን እጅ በመጠበቅ ባልደከሙበት ሀብት መኖር ማለት ነው:: ስለዚህ ሌሎች በለፉበት ተቀ ምጦ የመብላት ልምድ መቅረት ይኖርበታል::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ሳይሰሩ መብላት ምን ችግር ያስከትላል?
2. ጥገኝነት ከሚመጣባቸው ምክንያቶች ሁለቱን ግለጹ::
3. ሥራ የሰው ልጆች ዋስትና ነው የሚባለው በምን ምክንያት ነው?

### 7.2.3 ሳይሠሩ መብላትን መፀየፍ

- ሳይሠሩ መብላት አፀያፊ ነው የሚባለው ለምንድነው?

ሣይሰሩ መብላት ነውርና አፀያፊ ተግባር ነው:: በቤተሰብና በሀገር ደረጃም ቢሆን የልማት እና የእድገት እንቅፋት ከሚሆኑት ችግሮች አንዱ ነው:: ስለዚህ ሳይሰሩ መብላትን በመ ፀየፍ እና ሳይሰሩ ለመኖር የሚፈልጉ ሰዎችን በማስተማር ሁሉም ሠርቶ እንዲኖር ማበረ ታታት ያስፈልጋል::

**የነመገርቱ ግቢ**

መገርቱና ኡቻንጋ ጓደኛሞች ናቸው:: ሁለቱ ጓደኛሞች አንድ ቀን የቤት ሥራቸውን እነ መገርቱ ቤት እየሠሩ ሳለ ኡቻንጋ በግቢው ውስጥ የተተከሉትን አበቦችና የጓሮ አትክል ቶች ተመልክቶ በልምላሚያቸው ተገረመ፤ መገ ርቱንም እንዲህ በማለት ጠየቃት:: "የግቢ ያችሁ ተክሎች ያምራሉ፣ በሚገባም በቅለዋል፣ ማነው የሚንከባከባቸው?"

መገርቱም ችግኞችን ከሌላ ቦታ በማምጣት የተ ከሉት አባቷ መሆናቸውን እሷና ታናሽ ወን ድሟ ደግሞ በማረምና ውሃ በማጠጣት በየተራ እንደሚሠሩ ነገረችው::

ኡቻንጋ ከዚያ በፊት በቤቱ ውስጥ ሥራ ሠርቶ ስለማያውቅ በጣም ተገርሞ "ትንንሽ ልጆች ሥራ ይሠራሉ እንዴ?" ሲል ጠየቃት::

መገርቱም በመገረም እየተመለከተችው "በርግጥ ትንንሽ ልጆች እንደ ትልቅ ሰው ከባድ ሥራ ዎችን አይሠሩም፣ ይሁን እንጂ ቀላል ሥራ ዎችን መሥራት መልመድ አለባቸው:: በእ ቅምና በችሎታቸው ሥራን መሥራት አስፈ ላጊ መሆኑን ከልጅነታቸው ጀምሮ ማመንና መለማመድ ይኖርባቸዋል" አለችው::

ኡቻንጋ እስከአሁን በቤተሰቡ ውስጥ በሚችለው ሥራ ባለመሳተፉ ተፀፀተ፣ ሌሎች የደከሙበትን ሲበላ በመቆየቱም አዘነ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ኡቻንጋ በሱ አቅም ሊሠሩ የሚችሉ ሥራዎችን በመሥራት ቤተሰቡን ማገዝ ጀመረ::

**መልመጃ 7**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ከመገርቱና ከኡቻንጋ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. ህፃናት በሚችሉት ሥራ መሳተፋቸው የሚጠቅመው ማንን ነው? ተወያዩበት
3. የኡቻንጋ የመጨረሻ ውሣኔ ምን ነበር?

ራሳቸውንና አካባቢያቸውን በሚጠቅም ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሥራ መሥራትን የሚ ወዱ ናቸው:: ይህን የመሰለ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎችም ሳይሠሩ መብላትን እንዲፀየፉና ሠርተው እንዲ ያገኙ የሚያነቃቁ ናቸው::

ሰው መኖር ያለበት አቅምና ችሎታው በሚፈቅ ደው ሥራ ላይ ተሰማርቶ በሚያገኘው ውጤት መሆን ይገባዋል፡፡ በሥራ ውጤታቸው ራሳቸ ውንም ሆነ ሀገራቸውን ማልማት የሚፈልጉ ሰዎች ሣይሠሩ መብላትን ይፀየፋሉ:: ሆኖም አን ዳንድ ሰዎች ሌላው የደከመበትን ተቀምጦ መብ ላት ይፈልጋሉ:: ይህ ግን በግለሰብ፣ በቤተሰብና በሀገር ደረጃ ጉዳት የሚያመጣ ስለሆነ በጥ ብቅ መወገዝ አለበት፡፡ በሌላ በኩል ሳይሠሩ መብላትን የሚፀየፉ ሰዎች ለሌሎች ሰዎችም መልካም ምሣሌዎች ናቸው::

**መልመጃ 8**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ሌሎች የለፉበትን ሳለመብላት እናንተ ወደፊት ምን ማድረግ አለባችሁ?
2. በቤት ውስጥ ሥራ የእናንተ ድርሻ ምንድን ነው?
3. አንድ ሰው የሌላው ሰው ጥገኛ ነው የሚባለው መቼና ምን ሲሆን ነው?

## 7.3. ሕገ መንግስታዊ የሥራ መብቶች

- ዜጎች ሊሠሩ የሚችሉትንና የማይች ሉትን ሥራ ማን ይመርጥላቸዋል?

ሥራ እየሠሩ መኖር የሁሉም ዜጎች መብት ነው:: ማንኛውም ሰው ለመኖር መሥራት አለ በት:: ሕፃናት በሚችሉት የሥራ ዓይነት መሳ ተፋቸው ጥሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዕድሜና ከአቅማቸው በላይ የሆነና የጉልበት ብዝበዛን የሚያስከትል ሥራ መሥራት አይገባቸውም:: ስለሆነም ማንም ሰው የመኖር ሕገመንግሥታዊ መብት እንዳለው ሁሉ ሠርቶ ማደር የሚች ልበት ሕገ መንግሥታዊ መብትም አለው::

የመሥራት መብት የተነፈገው ሰው የመኖር መብቱንም ተገፏል ማለት ነው:: ምክንያቱም የሰው ልጅ ኑሮና ሥራ የማይነጣጠሉ በመሆ ናቸው ነው::


**መልመጃ 9**

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ።***

?

1. የጉልበት ብዝበዛን የሚያስከትል ሥራ ስንል ምን ማለታችን ይመስላችኋል?

### 7.3.1 የፈለጉትን ሥራ በፈለጉት ቦታ የመሥራት መብት







*ሥዕል 7.2 በተለያዩ ሙያዎች የተሰማሩ ሰዎች*

- ሥዕሉ ላይ የምታይዋቸው ሰዎች በምን ዓይነት የሥራ መስክ የተሰማሩ ይመስላችኋል?
- እናንተ ወደፊት ምን ሠርታችሁ ለመኖር ትፈልጋላችሁ?

ለሁሉም ዜጐች የተፈቀደውና በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠው የመሥራት መብት ሕገ መንግሥታዊ የመሥራት መብት በመባል ይታወቃል:: እነዚህ ሕገ መንግሥታዊ የመሥራት መብቶች የሚከተሉት ናቸው::

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈለገውንና የመረጠውን ዓይነት ሥራ የመሥራት መብት አለው:: ሁሉም ሰው ተመሳሳይ የሥራ ፍላጎት አይኖረውም አንዱ ገበሬ፣ ሌላው መምህር፣ አንዱ ሐኪም፣ ወዘተ በሚል የሙያ መጠሪያ የተሰማራበት የሥራ መስክ እንደየ ፍላጎቱ ይለያያል:: ይሁን እንጂ ማንም ሰው በዜግነቱ በመረጠው የሥራ ዓይነት መሠማራት በሕግ የተሰጠው መብት ነው::

2. ማንኛውም ሰው ሙያውን የመምረጥና ወደ ፈለገው ቦታ ሔዶ የመሥራት መብት አለው:: ይህ ማለት ማንኛውም ዜጋ የመረጠውን የሙያ መስክ ወደየትኛውም የሀገሪቱ ክልሎች ሄዶ የመሥራት መብቱ በሕግ ተረጋግጦለታል ማለት ነው:: አንዳንድ የሙያ ዓይነቶችን ለማከናወንና ለማምረት ከቦታ ቦታ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ አንድ ሸክላ ሠሪ ከነበረበት ቦታ የሸክላ አፈር በብዛት ወደሚገኝበት ቦታ በመዛወር ሥራውን ሊቀጥል ይችላል::

3. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት የማፍራትና የባለቤትነት መብት አለው:: ይህም አንድ ዜጋ በመረጠው ሙያና በፈለገው አካባቢ ተሠማርቶ የመሥራት፣ የግል ንብረት የማፍራትና የባለቤትነቱን መብት የማስጠበቅ ሕገ መንግሥታዊ መብት አለው::

ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ የመሥራት ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ለሁሉም ዜጐች በእኩል የተሰጡ ነፃነቶች በመሆናቸው ሁሉም ዜጋ ሠርቶ እንዲያድር ሙሉ መብት የሚያጐናጽፉ ናቸው:: ሰው እነዚህን መብቶች ተጠቅሞ ሥራ በሠራ ቁጥር ሕይወቱ ይለወጣል፣ የቤተሰቡ ኑሮ ይሻሻላል፣ የቤተሰብ ማደግ ደግሞ የአካባቢና የሀገር እድገትና ልማትን ያመጣል:: የአንድ ሀገር ዜጐች የመሥራት መብቶቻቸውን ተጠቅመውና ተባብረው ከሠሩ ሀገር ትለ ማለች፣ የሕዝብ ኑሮ ደረጃም ይሻሻላል::

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ሕገ መንግሥታዊ የሥራ መብት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሰው የራሱና የቤተሰቡ ህይወት ተለ ውጦ ለማየት ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

### 7.3.2 የግል ንብረት የማፍራት መብት

- የግል ንብረት ሲባል ምን ማለት ነው?

የግል ንብረት ሲባል አንድ ሰው በግሉ የሚኖረው የራሱ ሀብት ሲሆን ይህም ለምሣሌ ያህል የመኖሪያ ቤትን፣ የቤት እንስሳትን፣ የእርሻ መኪናን፣ የእርሻ መሣሪያዎችን ወዘተ የሚያካትት ነው:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ቦታና አካባቢ የመረጠውን ሥራ ሠርቶ መኖር ይችላል:: በሚሠራው የሥራ ውጤትም የመጠቀም መብት አለው:: ከዚህም በላይ ሠርቶ ከሚያገኘው ውጤት ንብረት የማፍራትና በንብረቱም የማዘዝ መብት አለው::

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. አንድ ሰው የግሉ የሆነ ንብረት ለማፍራት የሚችለው እንዴት ነው?
2. የቤተሰባችሁ የግል ንብረት የሆኑትን ጥቀሱ?

## 7.4 ሙያና የሙያ ሥነ ምግባር ምንነት

- ሙያ ሲባል ምን ምንን ያጠቃልላል?
- የሙያ ሥነ ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?

ሙያ የራሱ የሆነ ልዩ ዕውቀትንና ችሎታን የሚጠይቅ የሥራ ዓይነት ነው:: ለምሳሌም ያህል ግብርና፣ ጋዜጠኝነት፣ መምህርነት ዳኝነት፣ የመሳሰሉት የሙያ ዓይነቶች ናቸው።

የሙያ ችሎታ ማለት በአንድ ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችልና ስለዚያ ሙያ ሊኖረን የሚገባው ዕውቀትና ችሎታ መኖር ማለት ነው::

የሙያ ሥነምግባር ማለት ደግሞ አንድ ሙያ በተግባር ላይ ሲውል ባለሙያው ሊያከብረው የሚገባው የሙያው ደንብና የአሠራር ሥነሥርዓት ነው:: ሁሉም የሙያ ዓይነቶች የራሳቸው የሆኑና የተለያዩ የሙያ ሥነምግባሮች አሏቸው::

ይሁን እንጅ በሁሉም ሙያዎች የምናገኛቸው የጋራ የሆኑ የሙያ ሥነምግባሮች አሉ:: እነዚህ የሙያ ሥነምግባሮች በሁሉም ባለሙያ ዘንድ መከበር የሚገባቸው ናቸው:: እነዚህም ሥራን ማክበር፣ በቅንነት ማገልገል፣ ለደንበኛ ታማኝ መሆን፣ ሀቀኝነት፣ የሙያ ግዴታን መወጣት፣ በሙያው ተጠቅሞ ሌሎችን አለመጉዳት፣ በተገልጋዩ ላይ አድሎ አለመፈፀም የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ማንኛውም ተገልጋይ ትክክለኛ አገልግሎት የሚሰጠውንና የማይሰጠውን ባለሙያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማወቅ ይችላል:: ጥሩ አገልግሎት የሰጠውን ባለሙያ ያከብራል፣ የዘወትር ደንበኛው ለመሆንም ይጥራል:: በሌላ በኩል የሙያ ሥነምግባሩን ያልተወጣን ግለሰብም ሆነ ድርጅት ያወግዛል፣ ከዚህም አልፎ መብቱ እንዲከበርለት በአደባባይ ሊጠይቅ ይችላል:: ይህ እየተደጋገመ ከሔደ ድርጅቱ ኪሳራ ላይ ይወድቃል ማለት ነው::

**መልመጃ 12**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. በሁሉም ባለሙያ ዘንድ መከበር ያለባቸው የሙያ ሥነምግባሮችን ዘርዝሩ።
2. ጥሩ አገልግሎት መስጠት የሚጠቀመው ማንን ነው?

### 7.4.1 ለሙያው ደንብና የሥራ መርሆዎች መገዛት

- *ለሙያ ደንብና መርሆዎች መገዛት ማለት ምን ማለት ነው?*

እያንዳንዱ ሙያ የራሱ የሆነ ውጤት አለው:: አንድ ባለሙያ የሚሠራው ሥራ ውጤታማ ይሆን ዘንድ አስቀድሞ የዚያን ሙያ የሥራ ሥነሥርዓቶች በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል:: ለምሣሌ አንድ ገበሬ ጥሩ ምርት እንዲያገኝ በወቅቱ መሬቱን ማለስለስ፣ ከዚያም እህሉን መዝራትና እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅበታል::

ይህን የአሠራር ሥርዓት ከተከተለ ራሱንና ቤተሰቡን ለመመገብ እንዲሁም ሸጦ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ነገሮች ለመግዛት ይችላል ማለት ነው:: ነገር ግን እነዚህን ሥርዓቶች ካልተከተለ የሚፈለገውን ውጤት አያገኝም::

እንዲሁም አንድ መምህር ተማሪዎቹን አስተምሮና በዕውቀት ገንብቶ ነገ የተሻሉ ዜጐች ለማድረግ አስቀድሞ የሥራ ፍቅር፣ ሰዓት የማክበር፣ ተማሪዎቹን የመውደድና አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ ሊኖረው ይገባል:: ይህ ካልሆነ ግን ተማሪዎቹን በሚፈልገው ዕውቀት ገንብቶ መልካም ዜጎች ሊያደርጋቸው አይችልም::

**መልመጃ 13**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?

1. አንድ ባለሙያ በሚሠራው ሥራ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?
2. በትምህርታችሁ ውጤታማ እንድትሆኑ ከእናንተስ ምን ይጠበቃል?

### 7.4.2 የሙያ ችሎታን ማዳበር



*ሥዕል 7.3 የሙያ ሥልጠና*

- *በሥዕሉ ላይ ያሉት ሰዎች በመሰልጠናቸው ምን ጥቅም ያገኛሉ? ሀገሪቱስ?*

አንድ ሥራ ጥሩ ውጤት የሚኖረው ባለሙያው ራሱንና ሙያውን ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት ነው:: የሥራን ውጤታማነት ለማሳደግ የሙያ ችሎታን ማዳበር ያስፈልጋል::

በየጊዜው ችሎታን ለማዳበር የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን መውሰድ የሥራ ውጤትን ከፍ ያደርጋል:: ከዚህም ሌላ ስለሙያው የተሻለ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች በመጠየቅ መረዳት ያስፈልጋል:: የሙያ ችሎታ ለማዳበር የሚጣጣር ሰው ጥንካራ ባለሙያ ይሆናል። የምርት ውጤቱ ከፍ ያለና ጥራቱም የተሟላ ይሆናል። ጥራት ያለው ምርት የሚያመርት ባለሙያ በተጠቃሚዎቹ ዘንድ ዕምነት ያተርፋል። ስለዚህ ማንኛውም ሠራተኛ በሚሠማራበት የሙያ ዘርፍ ጥሩ ውጤት ለማግኘትና ለሕብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ይችል ዘንድ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ማክበር ይጠበቅበታል::

ይህ በተግባር በሚተረጐምበት ጊዜ ባለሙያው፣ ቤተሰቡና አካባቢው ይጠቀማል ማለት ነው። ይህ ሕዝቡን በቅንነት በታማኝነትና በመልካም ሙያዊ ሥነ ምግባር ማገልገል ደግሞ ሀገርን ወደ ልማትና እድገት ያሸጋግራል::

**መልመጃ 14**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. ከሥልጠና ሌላ ሙያ በምን በምን ሁኔታ ሊዳብር ይችላል?
2. ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት ምን ጥቅም የሚያስገኝ ይመስላችኋል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ማንኛውም ሰው ለመኖር ቢያንስ ምግብ፣ መጠለያና ልብስ ያስፈልገዋል፡፡ ይህንን ፍላጐት ለማሟላት ደግሞ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ሰው ምንጊዜም ሥራን ሳይንቅ ከሠራ ከራሱ አልፎ ለአካባቢውና ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ሊያከናውን ይችላል፡፡ ዛሬ አነስተኛ የሚመስል ሥራ በዕውቀትና በሙያ ሥነምግባር ከታገዘ ትልቅ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል፡፡

ሥራ እንደማንኛውም ነገር ሊፈጠር የሚችል ነው፡፡ ሆኖም ሥራን ለመፍጠር በቅድሚያ የሥራ ፍላጐት፣ ተነሳሽነትና የግል ጥረት በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነዚህ የሥራ ስሜቶች ካሉ አንድን ቀላል ሥራ በመፍጠር ሙያን በትምህርት በማዳበርና የሙያ ሥነምግባሮችን በመላበስ ወደ ከፍተኛ የሥራ ዓይነት ለመሸጋገር ይቻላል፡፡ ሥራን ሠርቶ መኖር የሁሉም ዜጋ መብት የመሆኑን ያህል ሣይሠሩ መብላት ደግሞ ነውርና አሳፋሪ ነው፡፡

የአንድ ሀገር ዜጐች በተሰማሩበት ሙያ ጠንክረው ሲሠሩ ውጤታቸው ከፍ ይላል፡፡ በዚህ ሒደትም ሀገር በልማት ጐዳና ትጓዛለች ማለት ነው፡፡ የሀገር ልማትና እድገት መፋጠን ደግሞ ቀስ በቀስ ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማስወገድ ይረዳል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሀገር ትበለጽጋለች፣ ህዝቦቿም ጤናማና የተመቻቸ መልካም ሕይወት ሊመሩ ይችላሉ፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ጥገኛ፣** | በሌሎች ድካምና ልፋት የሚኖር በሌሎች ሰዎች ገቢ የሚተዳደር:: |
| **ነውር፣** | ተገቢ ያልሆነ ተግባር፣ ሰዎች የማይቀበሉት አፀያፊ ባሕሪ:: |
| **ለፍቶ መና፣** | ውጤት የማይታይበት ሥራ፣ የድካም ዋጋ የማያስገኝ:: |
| **ሙያ፣** | ስለ አንድ ሥራ የሚኖር ዕውቀትና ችሎታ:: |
| **ልምድ፣** | አንድን ሙያ አዘውትሮ ከመሥራት የሚገኝ ችሎታ:: |
| **መርህ፣** | አንድን ተግባር ለመፈፀም ሰዎች የሚከተሉት የሥራ አቅጣጫ፣ መተዳደሪያ። |
| **ማውገዝ፣** | መርገም፣ በመጥፎ ስም ማንሳት:: |
| **የሙያ ሥነ ምግባር፣** | አንድን ሥራ ለመሥራት ከአንድ ባለሙያ የሚጠበቅ ባህሪ። |
| **ወረት፣** | ገንዘብ፣ ንብረት ሀብት። |

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

### I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ሥራ የሰው ልጅ የሕይወት መሠረት ነው::
2. አንድ ሰው እየሠራ ካለው ውጪ ሌላ ሥራ መፍጠር አያስፈልገውም::
3. ራስን ችሎ መኖር ጥቅሙ ለራስ ብቻ ነው::
4. ሳይሠሩ ሌሎች የደከሙበትን መብላት ነውር አይደለም::
5. የፈለጉትን ሥራ መሥራትና የግል ንብረት ማፍራት የዜጎች ሁሉ መብት ነው::

### II . በ “ለ”ሥር የተዘረዘሩትን በ“ሀ” ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሙያ፣ | ሀ. የዜጐች ሠርቶ የመኖር መብት። |
| 2. የሙያ ችሎታ፣ | ለ. ሰዎች በጋራ የሚያከናውኑት ተግባር። |
| 3. የሥራ መብት፣ | ሐ. አንድ ባለሙያ ለሙያው የሚሰጠው ክበሬታ። |
| 4. የግል ንብረት | መ. ራሱን የቻለ ዕውቀት የሚፈልግ የሥራ ዓይነት። |
| 5. የሙያ ሥነምግባር፣ | ሠ. አንድ ዜጋ በሙያው ሠርቶ የሚያፈራው ሀብት። |
| 6. የቡድን ሥራ፣ | ረ. በሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችልና ስለ ሥራው የሚኖር ዕውቀት። |
| | ሰ. ተገልጋዩን ህብረተሰብ ማሳተፍ፡፡ |
| | ሸ. ህብረተሰብ የማይቀበለው አስነዋሪ ተግባር። |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. አንድ ባለሙያ ጥሩ አገልግሎት ለመስጠት ማዳበር ያለበት የትኛውን ነው?
   - ሀ. የሙያ ሥነ ምግባርን፣
   - ለ. የሙያ ችሎታን፣
   - ሐ. አዳዲስ ሥራ መፍጠርን፣
   - መ. ሁሉም አስፈላጊዎች ናቸው።
2. ከሚከተሉት ውስጥ ነውርና አሳፋሪ የሚባለው የቱ ነው?
   - ሀ. ተጨማሪ ሥራ መሥራት፣
   - ለ. በራስ ጥረት ሥራ መፍጠር፣
   - ሐ. መሥራት እየቻሉ ሌላው የደከመበትን መብላት፣
   - መ. የሙያ ችሎታን ማዳበር።
3. ሥራን ለመፍጠር አስፈላጊው ነገር የቱ ነው?
   - ሀ. ራስን በራስ ለሥራ ማነሳሳት፣
   - ለ. የሌሎችን እርዳታ መሻት፣
   - ሐ. ገንዘብ እስኪገኝ መጠበቅ፣
   - መ. ሙያ ለመማር ዝግጁ አለመሆን።

4. ሥራ የማይሠራ ሰው በመጨረሻ ምን ይሆናል?
   ሀ. ለቤተሰብና ለሀገር ሸክም ይሆናል፣
   ለ. ወደ ከፍተኛ ውጤት ይደርሳል፣
   ሐ. የሙያ ሥነምግባር ያለው ይሆናል፣
   መ. ሥራን ይፈጥራል።
5. ሰው ሥራ መሥራት ያለበት ለምንድን ነው?
   ሀ. ለመኖርና ተጨማሪ ፍላጐቶቹን ለማሟላት፣
   ለ. አካባቢውንና ሀገሩን በሙያው ለማገዝ፣
   ሐ. ራሱንና ቤተሰቡን ለመርዳት፣
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ሀገር የምትለማው መሥራት የሚችሉ ዜጐች የ ----------------ባህልን ሲያዳብሩ ነው
2. ሥራን ፈጥሮ መሥራት አስፈላጊ የሚሆነው ከ-----------እና -------- ለመላቀቅ ነው፡፡
3. አንድ ሙያ በሥራ ላይ ሲውል ባለሙያው ሊያከብረው የሚገባው የሙያው ደንብና አሠራር መመሪያ ---------------- ይባላል፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. የሥራ ውጤታማነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. አንድ ሙያተኛ የሙያ ሥነምግባር የለውም የምንለው ምን ሲሆን ነው?

# ምዕራፍ ስምንት

# ራስን መቻል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- ራስን የመቻል ምንነት ትረጂያለሽ/ትረዳለህ፤
- በራስ የመተማማን ጠቀሜታን ትረጂያለሽ/ ትረዳለህ፤
- ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን ለምን እንደሚጠቅም ታውቂያለሽ /ታውቃለህ፡፡



*ሥዕል 8.1 ጥገኝነት*



*8.2 ሥዕል 8.2 ራስን መቻል*

## 8.1 ራስን የመቻል ምንነት

- ከሁለቱ ሥዕሎች ራስ መቻልን የሚያ ሳየው የትኛው ነው?
- ራስን ለመቻል በትምህርት ቤትና በቤታ ችሁ ውስጥ የምትሰሯቸውን ሥራዎች በየተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞ ቻችሁ ግለጹ፡፡

### ጉበዝ ተማሪዎች

ጉበዝ ተማሪዎች የትም ቦታ ያሉ፣
ቀስቃሽ አይፈልጉም በጧት ይነቃሉ፡፡
በፍጥነት ተነስተው ይለባብሱና፣
ፊታቸውን ታጥበው ቁርስም ይበሉና፣
ወደ ትምህርት ቤት ፈጥነው ይሄዳሉ፡፡
ባንዲራ ሲወጣ በጋራ ዘምረው፣
ይገባሉ ክፍል ስርዓትን አክብረው፡፡
መምህራን ሲያስረዱም በጽሞና አዳምጠው፣
መልስም ይሰጣሉ ሲጠየቁ ተግተው፡፡
ዕውቀታቸው እንዲያድግ መጽሐፍ ያነባሉ፣
ይኼ ነው ጉብዝና ልጆች ልብ በሉ፡፡

ምንጭ፣ «ይቅርታ» የልጆች መፅሐፍ፣ 2000 /የዝና ወርቁ/

**መልመጃ 1**

***ግጥሙን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ራስን የመቻል መገለጫ የሆኑትን ተግባራት የሚገልጹ ሀረጎችን እየለያችሁ አውጡ፡፡
2. አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡ ከዚያም ራስን መቻል ስለሚሰጠው ጥቅም ተወያዩ፡፡

ራስን መቻል ማለት የራስን ጉልበት፣ ዕውቀት እና አቅም ጠንቅቆ በማወቅ በዚያው መጠን የሚቻለውን ነገር ሁሉ በራስ ተነሳሽነት ጠንክሮ መሥራት ነው፡፡ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይንም ከመንግሥት እርዳታን ሳይጠብቁ በራስ ገንዘብ፣ እውቀት እና ጉልበት ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወን ራስን የመቻል ዋና መገለጫ ነው፡፡ ለምሳሌ ልጆች፣

- ትምህርታቸውን በትጋት ከተከታተሉ እና በፈተና ወቅት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ሳይኮርጁ ከሠሩ፣
- መምህራን የሚሰጧቸውን የቤት ሥራ ዎች ያለቤተሰብ ጉትጎታ ራሳቸው አስበው ከሰሩ፣

- በቤታቸው ውስጥ የትምህርት መሣሪያ ዎቻቸውን በአግባቡ እና በጥንቃቄ የሚ ያስቀምጡ ከሆነ፣
- የትምህርት ቤት መግቢያና መውጫ ሰዓቶችን አክብረው የሚገቡ እና የሚ ወጡ ከሆነ፣

ባጠቃላይ ለራሳቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮ ችን ራሳቸው የሚያከናውኑ ከሆነ «ራሳቸውን ችለዋል» ማለት ይቻላል፡፡

በሥዕል 8.1 ላይ ሌሎች ሲሠሩ ቆሞ የሚመ ለከተው እራሱን ለመቻል የሚያደርገው ጥረት እንደሌለ የሚያመላክት ነው። በአንጻሩ በሥ ዕል 8.2 ላይ አልጋውን የሚያነጥፈው ልጅ ራሱን ለመቻል ከፍተኛ ጥረት እያደረገ የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህ ከልጅነት ጀምሮ ራስን የመቻል ስሜትን ማዳበር የወደፊት ሕይወ ትን የተቃና ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል ስናስተውለው ማንኛውም ሰው ቢሆን የራሱ አመለካከት ኖሮት የራሱን አቋም ለመያዝና ለመፈፀም እንዲችል በቅ ድሚያ ራሱን መቻል ይኖርበታል፡፡ በሌላ ሰው ላይ ጥገኛ ሆነው እየኖሩ የራስን አመ ለካከት መከተል እና የግል አቋም መያዝ አስቸጋሪ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥይቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. አንድ ተማሪ ራሱን ለመቻል ምን ምን ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅበታል?
2. እናንተ በቤታችሁ ውስጥ ራሳችሁን ችላችሁ የምታከናውኗቸውን ሥራዎች ግለጹ፡፡

## 8.2. በራስ መተማመን

- በራስ መተማመን ማለት ምን ማለት ነው?

### አሸብርና እናቱ

ወ/ሮ አየለች- ልጃቸውን አሸብርን ጠሩትና፣ «ልጄ አሸብር! ዛሬ በጣም አሞኛል:: ለነገ ትም ህርት ቤት የምትለብሰው ዩኒፎርምህ አልታ ጠበም:: እንዲያው ምን ይሻለኛል? እስኪ ከጐ ረቤት የሚያጥብ ሰው ልለምን» አሉት::

«እማዬ ለምንድነው ሰው የምትለምኝ?» አላ ቸው- አሸብር::

«ታዲያ ምን ላድርግ:: ካልታጠበልህ እኮ ነገ ከትምህርት ቤት መቅረትህ ነው» አሉት:: በዚህ ጊዜ አሸብር በጣም ተገረመና:-
«እኔ ራሴ ለምን አላጥበውም?» አላቸው::

«አይይ ልጄ! አንተማ አትችልም?» አሉት::

«አይ እማዬ ለካስ ሞኝ ነሽ:: እኔ እኮ አንቺ ሁልጊዜ ስታጥቢ እያየሁ ልብስ እንዴት እንደ ሚታጠብ አውቀያለሁ:: አክስቴን ደግሞ አስተ ምሪኝ እያልኳት አስተምራኛለች:: ስለዚህ እኔ አጥበዋለሁ» አላቸው::

እናቱ ግን ስላላመኑት «አይሆንም» አሉት::

አሸብር ግን ልብስ ማጠብ እንደሚችል እርግጠኛ ስለሆነ፣

«ግዴለሽም እማዬ፤ ካላመንሽኝ ካጠገብሽ አቀራ ርቤ ልጠብ» አላቸው:: በዚህ ስለተስማሙ እናቱ እያዩት ልብሶቹን ማጠብ ጀመረ::

«ጐሽ የኔ ልጅ አደግልኝ:: በል እስኪ እኔም ራሴን እንዲሻለኝ ትንሽ ልተኛ» አሉት::

**መልመጃ 3**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ከላይ ባነበባችሁት ታሪክ መሠረት በራስ መተማማን የሚለውን ሀረግ ግለጹ::
2. አሸብር ልብስ ማጠብ እችላለሁ ብሎ በራሱ ለመተማመን ያበቃው ምንድን ነው?
3. በራስ ለመተማመን ምን ያስፈልጋል?

በራስ መተማመን ማለት የራስን አቅም ጠንቅቆ በማወቅ በሚሠሩት ሥራ ላይ እርግጠኛ መሆን መቻል ነው። በራስ መተማመን ስለ ራስ ትክክለኛ ግንዛቤ ከመያዝ የሚመነጭና ለሥራ የሚያነሳሳ ስሜት ነው። ለምሳሌ አንድ ተማሪ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ በሚገባ ከተከታተለ፣ መምህራን የሚሰጡትን የቤት ሥራ ከሠራና ዕቅድ እያወጣ ካጠና በፈተና ጊዜ በራሱ ተማምኖ መሥራት ይችላል።

በራስ ለመተማመን ጠንክሮ መሥራትና እውቀትን ማዳበር መሠረታዊ ነገሮች ናቸው። ከላይ በቀረበው ታሪክ ላይ አሸብር እናቱ እና አክስቱ ልብስ ሲያጥቡ እያስተዋለ በመማሩ ራሱ ልብሱን ማጠብ እንደሚችል እርግጠኛ ሆነ። በራሱ ተማመነ ማለት ነው። በራሱ ተማምኖ በመሥራቱም ጐረቤቶችን ከመለመን ዳነ። በራሳችን እየተማመን በማንነታችን እንድንኮራ ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል።

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. በራስ ለመተማመን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
2. በራስ ተማምኖ መሥራት ምን ጥቅም አለው?

## 8.3 በአቋም መጽናት



*ሥዕል 8.3 የራስን ሃሳብ ለሌሎች ማሳመን*

- ከላይ የቀረበው ምሥል ምንን ያሳያል?

### ዘኪ እና የክፍል ጓደኞቹ

ዘካርያስ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው። መምህሩ ሲያስተምሩ አይከታተልም። የሚሰጠውን የቤት ሥራም ራሱ አይሠራም።

በዚህ ምክንያት ክፍል ውስጥ ጓደኞቹን እየለመነና ከቤቱ ዳቦ፣ ከረሜላ ብስኩት እያመጣ እየሰጣቸው የሠሩትን እየገለበጠ ያሳርም ነበር። በፈተና ጊዜም እንዲያስኮርጁት ቃል አስገብቷቸዋል።

በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያው የዓመቱ አጋማሽ ፈተና ደረሰ። ዘካርያስም እንደሚያስኮርጁት ቃል ከገቡለት ተማሪዎች አጠገብ ለመኮረጃ እንደሚመቸው ሆኖ ተቀመጠ። ፈታኙ ወደ ፈተና ክፍሉ ሲገቡ ግን የተማሪዎቹን አቀማመጥ ቀየሩት። ዘካርያስም ሊያስኮርጁት ቃል ከገቡለት ልጆች ተለይቶ የመጀመሪያው ረድፍ ላይ ተቀመጠ።

የፈተና ውጤታቸው ሲሰጥ ዘካርያስ በጣም ዝቅተኛ ውጤት ስላገኘ አዘነ። «መውደቄ ነው» እያለም አለቀሰ። ጓደኛው ባጫ ደግሞ የዘካርያስን አገጭ በጁ ደግፎ «ለመኮረጅ ከምትዘጋጅ ይልቅ ፈተናውን ራስህን ችለህ ለመሥራት ትምህርትህን በትኩረት መከታተል ነበረብህ» አለው። አልማዝ ደግሞ «ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ» ብላ ቀለደችበት።

ዘካርያስም በጣም ተፀፀተ። «ከዚህ በኋላ በክፍል ውስጥ ትምህርቴን በትኩረት እከታተላለሁ። የቤት ሥራዎቼንም ራሴ እሠራለሁ። በትጋት አጠናለሁ። ይህንን በማድረግ ከፍተኛ ውጤት አምጥቼ ወደ ስድስተኛ ክፍል እዛወራለሁ» ብሎ ወሰነ።

በያዘው አቋም ፀንቶ በትኩረት መማር፣ ማጥናት እና ራሱን ችሎ የቤት ሥራዎቹን መሥራት ቀጠለ። ጓደኞቹ ብስኩትና ከረሜላ ስለቀረባቸው፣ «የሰራነውን ወስደህ ገልብጥ» ቢሉትም፤ «አይሆንም እኔ የናንተ ጥገኛ አይደለሁም። ራሴን ችዬ በትጋት ከሠራሁ ጥሩ ውጤት ማምጣት እችላለሁ» አላቸው። ዘካርያስ በአቋሙ በመጽናት ፈተናውን በልበ ሙሉነት ብቃውን እየተቀመጠ ተፈተነ። ከፍተኛ ውጤትም አመጣ።

ጓደኞቹ ግን ስለበለጣቸው ተናደዱና፣ "አንተ እኮ ሰነፍ ተማሪ ነበርክ" አሉት:: እሱም "በድሮ በሬ ያረሰ የለም" ብሎ በተራው ቀለደባቸው::

**መልመጃ 5**

*ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. ዘካሪያስ ዝቅተኛ ውጤት እንዴት ማምጣት እንደቻለ ግለፁ::
2. ዘካሪያስ አመዛዝኖ ነው የወሰነው ወይስ አይደለም? ከነምክንያታችሁ ግለፁ።

ማንኛውም ሰው አንድን ጉዳይ ለመፈፀም ቆርጦ መነሳቱን ሲገልጽ «አቋም ይዟል» ይባ ላል:: ይህንን አቋሙን ያለማወላወል ሲፈጽ መው ደግሞ በአቋሙ የመጽናቱ መገለጫ ይሆናል:: አቋም መያዝ እና መጽናትን በተ መለከተ:-

- በጉዳዩ ላይ በቅድሚያ ጊዜ ወስዶ ማሰብ፣
- ለመያዝ የተፈለገውን አቋም ከራስ፣ ከቤ ተሰብ እና ከሀገር ደህንነት እና ጥቅም ጋር ማገናዘብ፣
- የራስን ነጻ አቋም መያዝና ያመኑበትን ሀሳብና አመለካከት በነጻነት ማራመድ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው::

ማንኛውም ሰው በማንኛው ጉዳይ አቋም ሊኖ ረው እና በዚያው ሊፀና ይገባል:: ለምሳሌ ከዘኪ እና ጓደኞቹ ምንባብ እንደተረዳችሁት ዘካርያስ የሌሎች ጥገኛ ላለመሆን ወሰነና አቋም ያዘ:: በዚህ መሠረት ትምህርቱን በሚ ገባ በመከታተሉ ራሱን ችሎ ከፍተኛ ውጤት አመጣ::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. አንድ የክፍሳችሁ ተማሪ ትምህርት ለማ ቋረጥ ቢያስብ/ብታስብ በዚህ ሀሳብ ላይ አቋም ለመያዝ በቅድሚያ ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
2. ወደፊት መሆን የምትፈልጉትን ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለባችሁ የሚገልፅ ፅሁፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ::

## 8.4 ለለራሳችን የሚኖረን የተሳሳተ ግንዛቤ የሚገለጹባቸው ባህሪያት

### 8.4.1 የበላይነት ስሜት

- የበላይነት ስሜት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የምታውቁትን ግለጹ::

**እሾህ**

ቀኑ ቅዳሜ ስለሆነ ሀይሉና አለሚቱ ትምህርት ቤት አይሄዱም:: እናታቸው ወ/ሮ ወሰኔና አባታቸው አቶ ለሜሳ ደግሞ ወደ እድር ስብሰባ የሚሄዱበት ቀን ነው:: አባትና እናት ልጆቻ ቸው ሥራ እንዲለምዱና ለወደፊቱ ራሳቸውን እንዲችሉ በማሰብ በጋራ ቤቱን እንዲጠርጉና አልጋዎችን እንዲያነጥፉ ነግረዋቸው ወደ እድር ስብሰባ ሄደዋል::

ወላጆቻቸው ከእድር ተመልሰው ወደ ቤት ሲገቡ ሃይሉና አለሚቱ ይጨቃጨቃሉ:: ቤቱ አልተጠ ረገም፣ አልጋዎች አልተነጠፉም:: «ምንድነው የሚያጨቃጭቃችሁ?» አሉ ወላጆቻቸው - ወደ ቤት እየገቡ::

*አለሚቱ፣* «እሱ የኔን ያህል ቤት መጥረግም ሆነ አልጋ ማንጠፍ አይችልም:: ስለዚህ እኔ ቆንጆ አድርጌ የሠራሁትን ያበላሽብ ኛል:: ከሱ ጋር መሥራት አልፈልግም» አለች::

*ሀይሉ፣* «እኔ ጉበዝ ስለሆንኩ ካንተ ጋር አብሬ አልሠራም ብላ እምቢ አለችኝ» - አለ ሀይሉ እየተበሳጨ::

እናታቸው በጣም ስለተበሳጩ፣
«አለሚቱ ትክክል አይደለሽም::

ሁልጊዜም ሁሉን ነገር እኔ ብቻነኝ የማው ቀው እያልሽ ስለምትጨቃጨቂ አብሮሽ ከሚ ሠራ ሰው ጋር አትጣጣሚም:: ይኼው ዛሬም ምንም ሳትሠሩ ቆያችሁን» አሉ::

አባቷ ደግሞ፣

"ሁሉን ነገር አውቃለሁ ብለሽ ስለምታስቢ ለመማር ዝግጁ አይደለሽም:: ለምትሠሪው ሥራም ትኩረት አትሰጪም:: ባለፈው ቀን የበሩን እጀታ የሰበርሽው ትኩረት ሰጥተሽ እንዴት እንደሚሠራ ባለመጠየቅሽ ነው:: ይኼንን ባህሪይሽን ማሻሻል ይኖርብሻል" አሏት::

**መልመጃ 7**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥይቄዎች መልሱ።*

1. በዚህ ታሪክ ውስጥ የበላይነት ስሜት ያንፀባረቀውን ሰው ገለፁ? አልተንፀባረቀም የምትሉ ደግሞ ምክንያታችሁን አስረዱ::
2. የበላይነት ስሜት የሚያጠቃው ሰው የሚፈጥረውን ችግር እየዘረዘራችሁ በቡድን ተወያዩ::

የበላይነት ስሜት እራስን ብቻ ከፍ አድርጐ ሌሎችን ዝቅ አድርጐ ከመመልከት የሚመነጭ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ተምሬአለሁ በሚል ስሜት አልተማሩም የሚሏቸውን ሰዎች ዝቅ አድርገው ይመለከታሉ:: ይህም የበላይ ነት ስሜት መገለጫ ነው::

በሌላ በኩል አንዳንድ ሰው ሀብት ስላለው ብቻ በሀብት ከሱ ያነሱ ሰዎችን ዝቅ አድርጐ ይመለከታል:: ይህም ሀብት አለኝ በሚለው ሰው ላይ የበላይነት ስሜት ሊፈጠር ይች ላል:: በአጠቃላይ የበላይነት ስሜት አብዛኛውን ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለመግባባት፣ ላለመጣጣምና ለግጭት መንስዔ ይሆናል::

**መልመጃ 8**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. የበላይነት ስሜት በምን ይገለፃል?
2. የበላይነት ስሜት ምን ጉዳት ያስከትላል?

## 8.4.2 የበታችነት ስሜት

- ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ የበታችነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርጓቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።

**ፍቅርተ**

ፍቅርተ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት:: ጨዋታ ከመጠን በላይ ትወዳለች:: ስለዚህ ብዙ ጊዜ እየተደበቀች ከትምህርት ቤት ትቀራለች:: መምህራን የሚሰጧትን የቤት ሥራም ብዙ ጊዜ አትሰራም:: የፈተና ውጤቷም ሁልጊዜ ከጓደኞቿ ያነሰ ስለሆነ የበታችነት ስሜት ይሰማታል:: «እኔ ትምህርት አይገባኝም፣ ደካማ ተማሪ ነኝ» ብላ ታስባለች:: በዚህ ምክንያት በራሷ አትተማመንም:: ክፍል ውስጥ አስተማሪ ጥያቄ ሲጠይቅ እሳሳታለሁ ብላ ስለምትፈራ የምታውቀው ጥያቄ እንኳ ቢሆን መልሱን አትናገርም::

**መልመጃ 9**

*ከላይ ያለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. "እኔ ትምህርት አይገባኝም:: ደካማ ተማሪ ነኝ" የሚለው የምን ስሜት መገለጫ ነው?
2. የፍቅርተ ዓይነት የበታችነት ስሜት እንዳያጠቃችሁ ምን ማድረግ እንደሚኖርባችሁ ገለጹ::

የበታችነት ስሜት የሚመነጨው እራስን ዝቅ አድርጐ ከመመልከት ነው:: አንድ ሰው እራሱን ዝቅ አድርጐ ሲመለከት የሚያውቀውን ነገር የማያውቅ ይመስለዋል:: መሥራት የሚችለውንም መሥራት የማይችል ይመስለዋል::

የበታችነት ስሜት በራስ የመተማመን ስሜት እንዳይዳብር እንቅፋት የሚሆን ነው::

በራስ መተማመን ከሌለ ደግሞ ትምህርትን በውጤታማነት ለመማርም ሆነ ሌሎች ሥራ ዎችን በአግባቡ ለመሥራት እንዳንችል ያደ ርገናል፡፡ ለምሳሌ ፍቅርተ ለትምህርቷ ትኩ ረት ባለመስጠቷ በራሷ እንዳትተማመን እና የበታችነት ስሜት እንዲሰማት ምክንያት ሆኗል፡፡

**መልመጃ 10**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የበታችነት ስሜት በምን ይገለፃል?
2. በራስ መተማመን በምን ይገለፃል?

## 8.5 የራስን ችሎታ በማወቅ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የመሆን ጠቀሜታ

- እርስ በርስ መማማር ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ ተግባር ለማከናወን ከሚያስፈልጉን ነገ ሮች ውስጥ አንዱ ችሎታ ነው፡፡ ችሎታ አለን ብለን ማሰብ ሳይሆን በእርግጥ ችሎታው ሊኖ ረን ይገባል፡፡ ችሎታ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይበለጽጋል፡፡

እኛም ለሥራው የሚያስፈልገው ዕውቀት እን ዳለን ልናውቅና በራሳችን ልንተማመን ይገ ባል፡፡ ያለን ዕውቀት የበለጠ ሊያድግ ከሚች ልባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ዕውቀት ካላ ቸው ከሌሎች ሰዎች በመማር ነው፡፡

**መልመጃ 11**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የራሳችንን ችሎታ ለማወቅ ምን ማድ ረግ አለብን?
2. በሁለት ቡድን በመሆን አንደኛው ቡድን ከክፍል ጓደኛች ሊማር የሚችላቸውን ይግለጽ፡፡ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ከቤተ ሰብ የሚማራቸውን ይግለጽ፡፡

### 8.5.1 ለሀገር ዕድገትና ብልፅግና መሥራት

- የሀገር ዕድገትና ብልጽግና ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ ሰው ሁሉም ዓይነት ዕውቀት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለዚህ ብቻውን በተናጠል ሠርቶ አጥጋቢ ውጤት ሊያስመዘግብ አይችልም፡፡ የሚጠቅም ውጤት ለማምጣት ሁልጊዜ በጋራ መሥራት አማራጭ የለውም፡፡ ለምሳሌ አንድን ቤት ለመሥራት የተለያዩ ባለሙያዎች ያስፈል ጋሉ፡፡ መሀንዲስ፣ ግምበኛ፣ ቀለም ቀቢ፣ አናጺ፣ ኤሌክትሪሽያን፣ ቆፋሪ፣ ተሸካሚ ወዘተ ያስፈ ልጋሉ፡፡

እነዚህ ባለሙያዎች ተባብረውና አንዱ የሌላ ውን ሙያ አክብሮ ሲሠሩ ብቻ ነው ጥሩ ቤት መሥራት የሚቻለው፡፡ አንድ የታመመን ሰው ለማከም ደግሞ ሀኪም፣ ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን፣ ነርስ፣ ጤና ረዳት፣ የጽዳት ሰራተኛ ወዘተ ያስ ፈልጋሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ተባብረውና ተጋግዘው ሲሠሩ ብቻ ነው ውጤታማ ሥራ መሥራት የሚቻለው፡፡

ስለዚህ ለጋራ ብልጽግና በጋራ መሥራት ጠቃሚ ነው፡፡ ሀገራችንንም ማሳደግ እና ማበልፀግ የምን ችለው በልማት ሥራዎች ላይ ሁሉ ተጋግዘን በአንድ መንፈስ ስንሠራ ብቻ ነው፡፡ «ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ» የሚለውን ማስተዋል ተገቢ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 12**

*በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ።*

በአቅራቢያችሁ የሚገኝ አንድ የሥራ ማሕበር ሥራ አመራሮችን በመምህራችሁ አማካይነት ጋብዙና በጋራ መሥራት እና መማማርን በተመለከተ ጥያቄዎችን አዘጋጅታችሁ ተወያዩ፡፡

## 8.5.2 የሀገርን እድገትና ብልጽግና የሚጐዱ ተግባራት

- ኮንትሮባንድ ንግድ ምንድነው? በኮንትሮ ባንድ ከሚገቡ ዕቃዎች እስኪ የምታዉቁትን ግለጹ::



*ሥዕል 8.4 ኮንትሮባንድ ሀገርን የሚጎዳ ተግባር ነው::*

### መድኃኒቱ

ወ/ሮ አማረች «ኡኡ...» ብለው ጮሁ:: ጐረቤቶቻቸው እየተሯሯጡ ሲገቡ ትንሿ ልጃቸው ፋጤ ተዝለፍልፋ አልጋው ላይ ተኝታለች::

«ኧረ መኪና በቶሎ ጥሩ፣ ቶሎ ፍጠኑ» አሉ አንድ አዛውንት በድንጋጤ እየተርበተበቱ:: ወዲያው መኪና ተጠራና ትንሿ ልጅ ወደ ሀኪም ቤት ተወሰደች ::

ሀኪም ቤት እንደደረሱ ወ/ሮ አማረች እያለቀሱ በእጃቸው የያዙትን መድሀኒት ለዶክተሯ ሰጡ:: ዶክተሯም መድሀኒቱን አገላብጠው አዩና በድንጋጤ፣

«ይኼ መድሀኒት ጊዜው ያለፈበት እና የተበላሸ ነው:: ከየት ነው የገዛችሁት?» አሉ::

«ኧረ እኔ ከመድሀኒት ቤት ነው የገዛሁት» አሉ - ወ/ሮ አማረች ልጃቸው አደገኛ ሁኔታ ላይ መሆኗን ስለተገነዘቡ እያለቀሱ:: ወዲያው ዶክተሯ ፋጤን ወደ ከፍተኛ ህክምና ላኳትና ለፖሊስ ደውለው ሁኔታውን አስታወቁ::

ፖሊስ ባካሄደው ምርመራም መድሀኒቱ በሕገወጥ መንገድ በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር መግባቱ ታወቀ:: መድሀኒቱን በሕገወጥ መንገድ ያስገቡትና የመድሀኒት ቤቱ ሠራተኞች በሙሉ ፍርድ ቤት ቀርበው የእስር ቅጣት ተበየነባቸው::

**መልመጃ 13**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. ከቀረበው ምንባብ ስለኮንትሮባንድ ምን ተረዳችሁ? እስኪ አወያይና ፀሀፊ ምረጡና ተወያዩ::
2. ፋጤ የወሰደችው መድሃኒት ችግሩ ምንድነው?

ኮንትሮባንድ ከሁለት የጣሊያንኛ ቃላት የተመሠረተ ነው:: «ኮንትራ» ማለት መቃወም፣ መፃረር እና ተቃራኒ መሆን ማለት ሲሆን «ባንድ» ማለት አዋጅ፣ ሕግንና መመሪያን ያጠቃልላል:: በዚህ መሠረት የኮንትሮባንድ ንግድ ማለት ሕግን ደንብን እና መመሪያን በመተላለፍና በመቃወም የሚደረግ የንግድ እንቅስቃሴ ነው በማለት ኮንሳይስ ኦክስፎርድ ኤሌክትሮኒክስ ዲክሽነሪ ይተረጉመዋል::

***ድርጊቱም፣***

1. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ሊፈጽሙት የሚገባውን ሕጋዊ ሥነ ሥርዓት ሳይከተሉ በድብቅ ድንበር ጥሶ ማስገባት ነው::
2. ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ዕቃዎች ሊፈጽሙት የሚገባውን ሕጋዊ ሥነ ሥርዓት ሳይከተሉ በድብቅ ድንበር ጥሶ ከሀገር ማስወጣት ነው::

በዚህ ሕገወጥ ሁኔታ ከሀገር የሚወጡ እና ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በዜጎች ሕይወት፣ ኢኮኖሚ እንዲሁም ማኀበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ናቸው፡፡

በኮንትሮባንድ አማካኝነት ተገቢ ደረጃቸውን ስለመጠበቃቸው በሚመለከተው አካል ምርመራ ያልተደረገባቸው መድሀኒቶች እና የተመረዙ ምግቦች ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ በዜጎች ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ በፋጤ ላይ የደረሰው ችግር አንድ ምሳሌ ነው፡፡

ዕቃዎች በኮንትሮባንድ ወደ ውጭ ሀገር ሲወጡም መንግሥትን ከግብር እና ቀረጥ ሊያገኘው የሚገባውን ገቢ በማሳጣት የሀገርን ኢኮኖሚ ያዳክማሉ፡፡ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ ሁኔታው እጅግ አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

በአጠቃላይ ኮንትሮባንድ በአሁኑ ጊዜ ድርጊቱም፤

- ለሽብርተኝነት የገንዘብ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣
- የመንግሥት ገቢን ያሳጣል፣
- ጥራትና ደረጃቸው ያልተጠበቀ ሸቀጦች እና ያልተፈቀዱ የጦር መሣሪያዎች ወደ አገር እንዲገቡ በማድረግ የሀገርን ሰላም እና ኢኮኖሚ፣ የህዝብና ማህበራዊ ህይወትን እና ጤናን በማቃወስ ላይ የሚገኝ ከባድ ወንጀል ነው፡፡

**መልመጃ 14**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. ኮንትሮባንድ ምንድነው?
2. ኮንትሮባንድ ምን ጉዳት ያመጣል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ራስን ለመቻል በየጊዜው እውቀትን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ በዕውቀት ለመበልፀግ ደግሞ በቤት ውስጥ ታላላቆች የሚሠሩትን ማስተዋል፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር መወያየት፣ ያስተዋልነውን ነገር በተቻለን አቅም በተሻለ ሁኔታ መሥራት ጠቃሚ ነው፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ የትምህርት ቤቱን ሥነሥርዓት ማወቅ፣ መምህራን ሲያስተምሩ በጽሞና ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ ጥያቄዎችን መሥራት፣ ከክፍልና ከግል ጓደኞች ጋር መወያየትና የተሻለውን ሃሳብ መቀበል እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

እነዚህ ነገሮች ራሳችንን እንድንችል ያበቁናል፡፡ ራሳቸውን የቻሉ ሰዎች ደግሞ የሌሎች ሰዎች ተገዥ አይሆኑም፡፡ የሚያምኑበትን ለመወሰን ይችላሉ፡፡

በሌላም በኩል ኮንትሮባንድ የሀገርን ገቢ በማሳጣት አዳክሞ ራሷን እንዳትችል የሚያደርግ ጉጂ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ መድሀኒቶችና ምግቦችን በድብቅ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት የጤና ቀውስን ያስከትላል፡፡ ሁሉም ሰው ራሱን ለመቻል ጥረት ካደረገ እና ሕገ ወጥ ተግባራትን ከተከላከለ ሀገር ትበለጽጋለች፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**መጐትጐት፣** መቀስቀስ፣ ማነሳሳት።

**ማንቋሸሽ፣** ዝቅ አድርጐ ማየት፣ መናቅ።

**በጽሞና፣** በርጋታ እና በትኩረት።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. የራስን አቅም ጠንቅቆ ማወቅ በራስ ለመተማመን ይጠቅማል::
2. በውይይት ጊዜ ለሌላ ሰው ሀሳብ ግምት ሳይሰጡ በራስ ፍላጐት ብቻ መከራከር ጠቃሚ ነው::
3. የሚረዳን ሰው ካለን ራሳችንን ለመቻል መሥራት ምንም አይጠቅመንም::
4. የማናውቀውን ነገር ከሌላ ሰው መጠየቅ የበታችነት ምልክት ነው::
5. እየተማማሩ ተረዳድቶ መሥራት ለሀገርና ለራስ ጠቃሚ ነው ::

## II. ከተራ ቁ. 1-6 «የተከናወኑ ሥራዎች» በሚለው ርዕስ ሥር የተዘረዘሩ ተግባራት «ጥገኝነት» ወይም «ራስን መቻል» መሆናቸውን በማስተዋል በተሰጠው ቦታ ላይ የ «√» ምልክት በማድረግ አዛምዱ::

| ተ.ቁ | የተከናወኑ ሥራዎች | ጥገኝነት | ራስን መቻል |
|---|---|---|---|
| 1 | ደብተሮቼን የት እንዳስቀመጥኳቸው ጠፉብኝና ወንድሜ ፈልጐ ከቦርሳዬ ውስጥ ከተታቸውና ሰጠኝ፣ | | |
| 2 | ልብሶቼን ራሴ ለበስኩ፣ | | |
| 3 | የተመገብኩባቸውን ዕቃዎች እህቴ እንድትሰበስባቸው ጠረጴዛው ላይ ተውኳቸው፣ | | |
| 4 | ትምህርት ቤት እንዳይረፍድብኝ በጠዋት ከእንቅልፌ ነቃሁ፣ | | |
| 5 | ኮንትሮባንድ ንግድ፣ | | |
| 6 | መኝታዬን አነጠፍኩ፣ | | |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. ራሱን የቻለ ሰው፣
   ሀ. ለራሱ ብቻ ማሰብ አለበት፣
   ለ. ከሌላው ሰው የበላይ ነኝ ብሎ ማሰብ አለበት፣
   ሐ. በዝቅተኝነት ስሜት ይሸማቀቃል፣
   መ. ከተረጂነት ነጻ ነው::
2. ከሚከተሉት ውስጥ በራሱ የሚተማመን ተማሪ ተግባር የቱ ነው?
   ሀ. ጥያቄ ለመመለስ እጁን ያወጣል፣
   ለ. ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ይወያያል፣
   ሐ. የመሰለውን ሀሳብ ይገልጻል፣
   መ. ሁሉም ትክክል ነው::

3. በአቋም መጽናት ጠቃሚ የሚሆነው፤
   ሀ. የኔ ሀሳብ ብቻ ነው ትክክል ብሎ ድርቅ በማለት፣
   ለ. ስለ አንድ ጉዳይ በማንበብ፣ በመወያየት፣ በመሞከር፣ ግንዛቤን አዳብሮ በመወሰን እና በመፈጸም፣
   ሐ. የሌሎች ሰዎችን ሀሳብ ብቻ ተከትሎ ሳያገናዝቡ መወሰን እና መፈፀም፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።

4. የጋራ ብልፅግናን ማምጣት የሚቻለው፤
   ሀ. ለብቻ ሠርቶ በመክበር፣
   ለ. በጋራ ሠርቶ በጋራ ተጠቃሚ በመሆን፣
   ሐ. በመማማርና እውቀትን በማሳደግ፣
   መ. ከ ሀ በስተቀር ሁሉም መልሶች ናቸው።

5. ኮንትሮባንድ ንግድ፤
   ሀ. በሕገ ወጥ መንገድ እቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ነው፣
   ለ. በሕገ ወጥ መንገድ እቃዎችን ከሀገር ማስወጣት ነው፣
   ሐ. ሀገርና ሕዝብን የሚጐዳ ተግባር ነው፣
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. መምህራን የሰጡትን የቤት ሥራ ሳይሠሩ ከሌላ ሰው መገልበጥ---------------- ነው፡፡
2. በፈተና ጊዜ ከጓደኛ ሳይኮርጁ መሥራት--------------------- ነው፡፡
3. --------------- ማለት ነገሮችን አመዛዝኖ የተሻለውን ሃሳብ መያዝ እና ያለማወላወል መፈፀም ነው፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ራስን መቻል ማለት ምን ማለት ነው?
2. በአቋም ለመጽናት ምን ያስፈልጋል?
3. የበላይነት ስሜት እና የበታችነት ስሜት የሚገለፁባቸውን ባህሪያት ግለፁ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የቁጠባ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የቁጠባን ምንነት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፤
- የቁጠባን ባህል ማዳበር እራስን ለመቻል እንደሚያገለግል ትረዳለህ/ትረጃለሽ፤
- በአከባቢያችሁ የቁጠባ ባህልን ማዳበር ለምን እንደሚያስፈልግ ትገነዘባለህ /ትገነዘቢያለሽ።

## 9.1 ቁጠባ

### 9.1.1 የቁጠባ ምንነት



*ሥዕል 9.1 ቁጠባን አለማወቅ*



*ሥዕል 9.2 የክፍል ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎችን በአግባቡ አለመጠቀም ቁጠባን ይፃረራል*

- *ሁለቱ ፎቶግራፎች የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው?*

*ቁጠባ ማለት ከሚገኝ ገቢ በአግባቡ ለሚያስፈልግ ወጪ ተጠቅሞ የተወሰነውን ለወደፊት ጠቀሜታ እንዲሆን ጥሪት ማስቀመጥ ማለት ነው:: ይህም ቁጠባ አላስፈላጊ ከሆኑ ወጪዎች መታቀብን ያመለክታል:: ቁጠባ ማለት ዛሬን እየተቸገሩ ለነገ ማሰብ አይደለም:: ቁጠባ ከምናገኘው ገቢ የሚያስፈልገንን ተጠቅመን የተወሰነውን ደግሞ ማስቀመጥ ማለት ነው::*

*ቁጠባ ሌላም ገጽታ አለው:: የምንገለገልባቸው ቁሳቁሶች እንዳይጐዱ በአግባቡ መያዝና ለረጅም ጊዜ ግልጋሎት መጠቀም ማለት ነው:: ለምሳሌ የመማሪያ መጻሕፍቶቻችንን በአግባቡ መጠቀምና በንጽህና መያዝ፣ የመማሪያ ክፍሎቻችን፣ ወንበሮቻችንና ጠረጴዛዎቻችንን ጉዳት እንዳይደርስባቸው በጥንቃቄ መያዝና መጠቀም ይኖርብናል::*

*የቁጠባ መጠን በየሰው አቅም ይወሰናል:: ለምሳሌ አንድ ጫማ አሳማሪ እቁብ ቢጥል በሳምንት የሚጠበቅበት ክፍያ አስር ብር ብቻ ሊሆን ይችላል:: በአንጻሩም አንድ ባለታክሲ በሳምንት አንድ መቶ ብር ሊጥል ይችላል:: የቁጠባ መጠን ከሚገኝ የገቢ መጠን ጋር የተያያዘ ነው::*

***መልመጃ 1***

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

?

1. ቁጠባ ማለት ምን ማለት ነው
2. የሚቆጠብ ገንዘብ ለምን ለምን እንደሚጠቅም በአካባቢያችሁ ከሚኖሩ ሰዎች ወይም ከቤተሰቦቻችሁ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
3. አንድን ተማሪና አንድን ገበሬ በመውሰድ ሁለቱ እንዴት ቆጣቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተወያዩ::

## 9.1.2 የቁጠባ ዓላማዎች

### 9.1.2.1 የሌሎች ጥገኛ አለመሆን

- ጥገኝነት ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ ? ምን ማለት ይመስላችኋል?

### አቶ ሳሙኤል እና ወ/ሮ ብርቱካን፤

አቶ ሳሙኤል ሳዴቦ የተወለደው በደቡብ ኢትዮጵያ አረካ ከተማ ነው:: በልጅነቱ በወገቡ ላይ በደረሰበት አደጋ ምክንያት አካል ጉዳተኛ ሆኗል:: ይሁን እንጂ ወላጆቹ ትምህርት ቤት አስገብተው አስተምረውታል:: አስር ዓመት ሲያልፈው ችግረኛ ወላጆቹን ለማገዝ በትርፍ ሰዓቱ የሊስትሮ ሥራ መሥራት ጀመረ:: ከዚያ ተነስቶ በጥቃቅን ሸቀጦች ንግድ ሥራ ተሰማራ:: ሃያ ዓመት ሲያልፈው ከወ/ሮ ብርቱካን ጋር ተጋቡና ሁለት ልጆችን ወለዱ:: በአንድ ወቅት አቶ ሳሙኤል ይሰራ የነበረው የኮንትሮባንድ ንግድ ኪሳራ አደረሰበትና ድህነት ላይ ወደቁ::

በዚህ ጊዜ አቶ ሳሙዔልና ባለቤቱ ወ/ሮ ብርቱካን የነበሯቸውን የጣት ቀለበቶች ሸጡና እንደገና በሙዝ ንግድ ተሰማሩ:: አቶ ሳሙኤል አንድ ሳጥን ሙዝ እየገዛ ሲቸረችር ቀስ በቀስ የሚሸጠው የሙዝ ሣጥን ቁጥር ጨመረ::

አቶ ሳሙዔልና ወ/ሮ ብርቱካን ዛሬ ባላቸው የኑሮ ደረጃ ልጆቻቸውን ጥሩ ትምህርት ቤት ያስተምራሉ:: ደህና መኖሪያ ቤት ተከራይተው ይኖራሉ:: ከዚህ ባሻገር ከሚሠሩት ሥራ ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ከሚጠቀሙበት በተጨማሪ እቁብም ይጥላሉ::

ድህነትን በሥራ ወዳድነታቸው ያሸነፉት አቶ ሳሙኤልና ወ/ሮ ብርቱካን ስለወደፊቱ ሲያስቡ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ወ/ሮ ብርቱካን ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ አቅደዋል:: ንግዳቸውንም የበለጠ ለማስፋፋት እየጣሩ ነው::

*(ምንጭ ለዚህ መጽሀፍ እንዲስማማ ተደርጎ በአጭሩ ከጦማር ጋዜጣ ሰኔ 1996 እትም ከገጽ 10 የተወሰደ)*



*ሥዕል 9.3 አቶ ሣሙኤልና ቤተሰቡ*

**መልመጃ 2**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ከአቶ ሳሙዔልና ከባለቤቱ ከወ/ሮ ብርቱካን ሕይወት ምን ተማራችሁ?
2. በአካባቢያችሁ ከትንሽ ደረጃ ተነስተው ሀብታም የሆኑ ሰዎችን ታሪክ በአጭሩ በመጻፍ በክፍል ውስጥ በንባብ አሰሙ::
3. ያገኛችሁትን ታሪክ በክፍል ውስጥ ካቀረባችሁ በኋላ ያላችሁን አስተያየት በመያዝ ሌሎች ተማሪዎች ካቀረቧቸው ባለታሪኮች የእናንተ ባለ ታሪክ በምን እንደሚለይ በጽሁፍ አቅርቡ::

ቁጠባ ራሳችንን መቻል አቅቶን የሌሎች ጥገኛ እንዳንሆን ያስችለናል:: በአቅማችን ልክ እየኖርን ያለንን በቁጠባ በመጠቀም ለወደፊት ኑሯችን ካላሰብን በቀር ራሳችንን ችለን መኖር ስለሚያቅተን የሌሎች ጥገኛ እንሆናለን:: ስለዚህ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለን ብንሆን እንኳን የአቅማችንን ያህል መቆጠብን መልመድ ያስፈልገናል፡፡

### 9.1.2.2 ወደፊት ሲመጣ የሚችልን ችግር ስመቋቋም፣



*ሥዕል 9.4 ልጄን በምን ላሳክም?*



*ሥዕል 9.5 በቆጠብነው ገንዘብ ምን እንግዛ?*

- ከዚህ በላይ ካሉት ሥዕሎች የተገነዘባችሁትን ግለጹ፡፡

## ኋላ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

አቶ ሙላቱና ወ/ሮ ሂሩት ከመምህርነት ሙያ ቸው ጡረታ በወጡበት ዓመት በተለይ ኮሌጅ የሚማሩት ሁለቱ ልጆቻቸው ዳንኤልና ብሌን ትልቅ ሥጋት ላይ ወድቀው ነበር፡፡ ምክንያቱም ወላጆቻቸው ጡረታ ከወጡ የሚያገኙት የወር ገቢ ስለሚቀንስ በትምህርታቸው ላይ ችግር የሚ ፈጠር መስሏቸው ነበር፡፡

ይልቁንም ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ "ገንዘብ የምታገኙበትን መንገድ መፈለግ ይኖርባችኋል" የሚባሉ መስሏቸው በርካታ ሰዓቶችን በመነጋገር አሳልፈዋል፡፡

አቶ ሙላቱና ወ/ሮ ሂሩት ግን የልጆቻቸውን ሥጋት በመረዳታቸው ውይይት ለማድረግ ጊዜው አሁን መሆን እንዳለበት ወሰኑ፡፡ ሁለቱም ለረጅም ዘመን ጠብቀው ስላቆዩት ቁምነገር ለልጆቻቸው ለመግልጽና የቤታቸው የኑሮ ልምድ በነበረበት ሁኔታ እንደሚቀጥል መንገር እንዳለባቸው ተስማሙ፡፡

አንድ እሁድ ቀን ከሰዓት በኋላ የቤተሰቡ አባላት በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባሰቡ፡፡ አቶ ሙላቱና ወ/ሮ ሂሩት ሁለት የተለያዩ የባንክ የቁጠባ ደብተሮች ይዘው ቀረቡ፡፡ ደብተሮቹ የተለያየ የገንዘብ መጠን ይገልጹ ነበር፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ሁለቱ ታታሪ ወላጆች በየጊዜው ቤተ ሰባቸውን ከሚያስተዳድሩበት ገቢ እየቆጠቡ መጥፎ አጋጣሚ ቢፈጠር፣ በቤተሰቡ ላይ አደጋ ቢደርስ፣ ችግር ላይ እንዳይወድቁ እንዲሁም የልጆቻቸውን ትምህርት ዳር ለማድረስ እንዲያ ስችላቸው ነው ያጠራቀሙት፡፡

ይህንኑ ለልጆቻቸው እንደዚህ በማለት አስረዷ ቸው፡፡ «ያማራችሁን ሁሉ ስትጠይቁን፣ ሌሎች ልጆች የተደረገላቸውን ሁሉ እንድናደርግላችሁ ስትጠይቁን ሳንፈጽምላችሁ የኖርነው፣ ሰው እን ደቤቱ እንደሚኖር ልናስተምራችሁ፣ እኛ ጡረታ ስንወጣም ችግር ላይ እንዳትወድቁ ስላሰብን ነው፡፡ አሁን ሁላችንም ሳንሳቀቅ እንደተለመደው ኑሯችንን እንቀጥላለን፡፡ በጡረታ ላይ ስላለን የምናገኘው ደመወዝ ቀድሞ ከምናገኘው ያነሰ መሆኑን ሁላችሁም መረዳት አለባችሁ፡፡ ነገር ግን ከነበረን ላይ ቆጥበን ያስቀመጥነው ገንዘብ በዚህ ጊዜ ይጠቅመናል፡፡ እና ንተም ትምህርታ ችሁን ጨርሳችሁ እራሳችሁን ስትችሉ ፈጽሞ ከችግር ሀሳብ ነጻ እንሆናለን፡፡»

ዳንኤልና ብሌን እርስ በርሳቸው በመተያ የት ተነስተው የወላጆቻቸውን አንገት አቅፈው ሳሟቸው፡፡ ሁለቱን ታናናሾቻቸውንም ስለቁጠባ ጠቀሜታ እነርሱም እንደሚያስተምሯቸው ነግ ረው እለቱን የደስታ እለት አድርገውት አመሹ፡፡

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መለሱ።***

1. ብሴን እና ዳንኤል ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?
2. ሁለቱ ወላጆች ከዚህ በኋላ ስለቁጠባ ማሰብ ይኖርባቸዋል ወይስ አይኖርባቸውም? በቡድን ተወያዩ፡፡

ቁጠባ ወደፊት ሳይታሰብ ሊያጋጥም የሚችልን ችግር ለመቋቋም እንዲቻል መጠባበቂያ ገንዘብ ወይም ንብረት ማስቀመጥ ማለት መሆኑን ቀደም ሲል ተረድታችኋል፡፡ ያልታሰቡ የወደፊት አጋጣሚዎች ህመምና አደጋ ናቸው፡፡ በአንድ ሰው ላይ እነዚህ አጋጣሚዎች ሲደርሱ ለህክምና የሚሆን ወጪ የሚወሰደው ቀደም ሲል ከተጠራቀመ ገንዘብ ነው፡፡

የቁጠባ አስፈላጊነት ለችግር ጊዜ ብቻ አይደለም፡፡ ሰዎች ሁሉ በወደፊት ሕይወታቸው ሊያሳኩዋቸው የሚሹዋቸው ግቦች ይኖሯቸዋል፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ለመማር፣ ሥልጠና ለማግኘት፣ ልጆችን በአግባቡ ለማስተማር፣ ሠርግ፣ ልደት፣ ማህበር፣ የትምህርት ምረቃ ለማዘጋጀት የሚሆን ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ነገር ግን እነዚህ የተጠቀሱት ግላዊና ማሕበራዊ እቅዶች ከአቅም በላይ ሊሆኑና ሊቀሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ልደትን ያለድግስ ከጓደኞችና ከቤተሰብ ጋር አስቦ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሠርግ ለመደገስ ገንዘብ ከሌለ ሥርዓቱን ብቻ ፈጽሞ ጋብቻን ማክበር ይቻላል፡፡ አደጋና ህመም ግን በማንኛውም ሰው ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ በመሆናቸው ሁልጊዜ ዝግጁ ሆኖ መቀመጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም በየትኛውም መንገድ ቢሆን የቁጠባ ባህል ማዳበር ተገቢ ነው፡፡

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ሰዎች ያላቸውን ገቢ እየቆጠቡ ማስቀመጣቸው ለምን ይረዳቸዋል?
2. በቤተሰባችሁ ውስጥ የሚከበሩ በዓላትና የሚደረጉ ዝግጅቶች በዓመት ውስጥ ምን ያህል ናቸው? መልሱን ከቤተሰብ ኃላፊዎች ጠይቃችሁ ተረዱ፡፡

3. በተራ ቁጥር 2 ስተጠቀሰው ጥያቄ ለምታገኙት መልስ የሚወጡ ወጪዎች ምን ያህል እንደሆኑ በመመዝገብ ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## 9.2 በእቅድና በአቅም ልክ መመራት፤

### 9.2.1 በዕቅድና በአቅም ልክ የመመራት ምንነት፣

“ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርም!”

- ከዚህ አባባል የተረዳችሁትን ግለጹ፡፡

**ሠርግና ምላሽ፤**

አቶ ፋሲል ታሪክነህ የስድስት ልጆች አባት ናቸው፡፡ የሚኖሩት ከአዲስ አበባ 80 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኝ መንደር ነው፡፡ ሰሞኑን ከመጀመሪያ ልጃቸው ጋር የከረረ ፀብ የፈጠሩበት አጋጣሚ የተከሰተው ልክ የዛሬ ዓመት ነበር፡፡ አዲስ አበባ የሚኖረውና ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀው ልጃቸው ዳዊት ሥራ ከያዘ ሦሥት ዓመት ሆኖታል፡፡

ይሁን እንጂ ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎትና ዓላማ ከአላት ሶስና ጋር ጋብቻውን የፈፀመው ባለፈው ግንቦት ወር ላይ ነው፡፡ ሁለቱም ወጣቶች ለወላጆቻቸው ይህንኑ እቅዳቸውን ባሳወቁ ጊዜ የሠርጋቸውን ድግስ በሚመለከት ብዙ ክር ክር ገጥሟቸዋል፡፡

ሆኖም በሠርጋቸው እለት ዘመዶቻቸውና የሚወዷቸው ጓደኞቻቸው ብቻ በሚገኙበት ለማክበር ወስነው ዝግጅታቸው ተጠናቋል፡፡ በእቅዳቸው መሠረት ጋብቻቸውን ፈጽመዋል፡፡

በዚህም አቶ ፋሲል ቅር ቢሰኙም ልጃቸው ራሱን ችሎ የሚኖርና ከአጠገባቸው ስለራቀ ሊያስገድዱት ስላልቻሉ ዝም ብለውታል፡፡ ነገር ግን በራሳቸው በኩል መልስ ሊጠሩትና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን በመልስ ሰበብ ደግሰው ሊያበሉ ወገባቸውን ታጥቀው ተነሱ፡፡

በዚህ ጊዜ ለድግስ ወጪ ተጨማሪ ገንዘብ ቢጠይቁት ልጃቸው ዳዊት ይህን ማድረግ ከአቅሙ ጋር ስለማይሄድ ሀሳባቸውን እንደማይ ቀበለው ይቅርታ በመጠየቅ ጭምር አስረድቷቸዋል:: ለአቶ ፋሲል ይህ ሁለተኛ ጥፋት ነው:: ስለ ሆነም እርሱ ያላቸውን ቸል በማለት ለድግሳቸው ቆርጠው ተነሱ::

ከአንድ ጎረቤታቸው ተማጽነው ገንዘብ ተበደሩ:: ይህም በቂ አልመሰላቸውም:: የሰፈራቸው እድር ገንዘብ ሰብሳቢ ከሆኑት ከአቶ በድሩ ደግሞ እንደምንም አግባብተውና በሁለት ወር ውስጥ ሊመልሱ ቃል ገብተው ተጨማሪ ገንዘብ ተበደሩ:: ለክረምት መውጫ ተብሎና ለዘር ከተቀመጠው የጎተራ እህል ደግሞ አራት ኩንታል አውጥተው ተጠቀሙበት:



ሥዕል 9.6. የተንዛዛ ድግስ የቁጠባ ባህልን ይጎዳል

ዝግጅቱ ተጠናቆ ሲያበቃ በሐምሌ ወር ላይ ድል ያለድግስ ደግሰው ልጃቸውን ከአዲስ አበባ መልስ ጠሩ:: የሚኮሩበት ልጃቸው ከፈለገ 50 ያህል እንግዶችን ይዞ እንዲመጣ አሳሰቡት:: ለእርሳቸው ደግሞ ብዙ ዓመታት ከኖሩበት መንደር በርካታ ክፉና በጎ አብረዋቸው ያሳለፉ ሰዎች ጠርተው ግብዣው ተከናወነ::

ዳዊት በአባቱ ድርጊት ሥጋት ገብቶታል:: ብዙ ጥሪት ሳያባክኑ እዳ ውስጥም ሳይዘፈቁ መደገስ እንደሚገባቸው ቢነግራቸውም አንድ ጊዜ የወሰኑትና ከእርሱ ወግ የበለጠ የሚመኙት እንደሌለ መለሱለት:: አባቱን ሀሳባቸውን ለማስቀየር አልቻለም:: ነገር ግን አንድ ጊዜ ወጪ አውጥተው ስለደገሱ ቢቀር የሚሰማቸውን ሀዘን በማሰብ ስድስት ሚዜዎቻቸውን ብቻ አስከትለው ከሶስና ጋር ተገኙ::

አባቱ በዚህ በጣም አዘኑ:: እርሱና ሶስና በአዲስ ዓመት ያቀዱት የራሳቸው እቅድ ደግሞ ነበራቸው:: ለዚህም በአቅም ልክ መኖርን መልመድና ቅድሚያ ለኑሯቸው መሠረት መጣል እንዳለባቸው ተስማምተዋል:: ይሁን እንጂ የዳዊት ዕቅድና የአባቱ ድርጊት ያልተጣጣሙ በመሆናቸው ለግጭት ዳርጓቸዋል:: በአዲሱ ዓመት ለታናናሾቹ የትምህርት ቤት ክፍያ ለሠርጋቸው ድግስ ወጪ የገቡትን ዕዳ ለመክፈል እንዲሁም ለዘር መግዣ ገንዘብ እንዲሰጣቸው በጠየቁት ጊዜ ሊረዳቸው አልቻለምና የፀባቸው መነሻም ይሔው ነው::

**መልመጃ 5**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. አቶ ፋሲል የልጃቸውን መልስ የደገሱበትን ወጪ ያገኙት ከየት ነው?
2. ዳዊት በአባቱ ድርጊት ያልተደሰተው ለምንድነው?
3. አቶ ፋሲል በአቅም ልክ እንዳይኖሩ እንዳያስቡ ያደረጋቸው ምንድነው?

የሰዎች የኑሮና የሀብት ደረጃ የተለያየ ነው:: ስለሆነም ሁሉም ሰው በአቅሙ ልክ መመራት አለበት:: በአቅም ልክ መመራት ማለት አንድ ሰው በራሱ የኑሮ ደረጃ ወይም የሀብት መጠን ማድረግ የማይችለውንና የማይገባውን ነገር አለማድረግ ማለት ነው::

ሰዎች በአቅማቸው ልክ መመራት ካልቻሉ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ:: ስለሆነም ለማንም ሰው የዚህ ዓይነት ችግር እንዳይገጥመው በዕቅድና በአቅም ልክ መመራት ይገባል::

የቁጠባ ባህል ሲኖረን ግን አቅማችንን አይተን ወጪዎቻችንን ባለን አቅም ልክ መጥነን እና ወጣለን:: የቁጠባ ባህል ሲኖረን ኑሯችንን የምንመራውና ወጪ የምናወጣው ራሳችንን

ከሌሎች ጋር በማወዳደር ሳይሆን በራሳችን አቅም ልክ ይሆናል፡፡

በአቅማችን ስንኖር ዛሬ ኖረን ነገ እንዳንቸገር ያደርገናል፡፡ በአቅም ልክ የመመራት ምስጢሩ ያለው በእቅድ መመራት ላይ ነው፡፡ እቅድ የምንፈልገውን ዓላማ ለማሳካት ወሳኝ ነው፡፡

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

?

1. በአቅም ልክ የመመራት ምን ጠቀሜታ አለው?
2. በአካባቢያችሁ ኑራቸውን በዕቅድ የሚመሩ ሰዎች ካሉ በኑራቸው ላይ ምን ለውጥ እንዳሳዩ በመጠየቅ በፅሑፍ አቅረባችሁ ተወያዩበት።

## 9.2.2 በእቅድና በአቅም ልክ መኖር

- በእቅድና በአቅም ልክ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?

### አበበና ሂሩት

አበበና ሂሩት በአንድ ክፍል ውስጥ ይማራሉ፡፡ በዓመቱ መጨረሻ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የወላጆች ቀን ይከበራል፡፡ ለዚህ በዓል የትምህርት ቤታቸው ተማሪዎች ዝግጅት እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ ይህ ጥያቄ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተማሪዎች እንዲመለከቱት ተለጥፎላቸዋል፡፡

አበበ ማስታወቂያውን ተመልክቶ ወደ ጓደኞቹ ተቀላቀለ፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ጉዳይ አንዳቸውም አንስተው አልተነጋገሩም፡፡ ሂሩት ደግሞ ማስታወቂያውን አንብባ የተረዳችውን እያብሰለሰለች ወደቤቷ ሄደች፡፡ የወላጆች በዓል የሚከበረው ከአንድ ወር በኋላ እሁድ ቀን ነው፡፡ ሂሩት የሥነጽሁፍ ዝጅግት ላይ ለመወዳደር ፈልጋለች፡፡

የወላጆች ቀን በተከበረ በሳምንቱ የሴሚስተር አጋማሽ ፈተና ይሰጣል፡፡ ዘወትር ቅዳሜ አያቷ ቤት እየሄደች አያቷን ትጠይቃለች፡፡ ስለዚህ ከወዲሁ ጊዜዋን በአግባቡ ተጠቅማ ዓላማዋን ለማሳከት ማቀድ ያስፈልጋታል፡፡ ግጥም ለመጻፍ ጊዜ ያስፈልጋታል፡፡ በእርሷ እድሜ የሚገኙ ልጆች የጻፏቸውን ወይም የአዋቂዎችን ግጥሞች ማንበብ ይኖርባታል፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው ቅዳሜ አያቷ ቤት ስትሄድ አጎቷን መጻህፍት እንዲፈልግላት ተጠይቀዋለች፡፡

ቤተመጻህፍት ገብታ ጋዜጦችን ማንበብ አስባለች፡፡ ለዚህም ቀድማ ትምህርት ቤት መድረስና ዘግይታ መውጣት ይኖርባታል፡፡ ይህንኑ ሃሳቧን ለወላጆቿ አስረዳቻቸው፡፡ እነርሱም አበረታቷት፡፡ ጊዜዋን በአግባቡ እንደምትጠቀም ስለሚያውቁ አበበ ያለምክንያት ወደ ትምህርት ቤት እንደምትሄድ የነገራቸውን አልተቀበሉትም፡፡

ሂሩት በትምህርትና ከዚህ ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎች ከአበበ እንደምትበልጥ ያውቃሉ፡፡ ለዚህም ማስረጃው የሁለት ዓመት ታላቋ የሆነው አበበ ሁለት ጊዜ ፈተና ወድቆ በክፍል ደረጃ እርሷ መብለጧ ነው፡፡ አባቷ ከምታነባቸው መጻሕፍት ፍሬ ሃሳቦች የምትይዝበት የተለየ የማስታወሻ ደብተር እንደሚያስፈልጋትና ይህንንም እንደሚያሟሉላት ነግረዋታል፡፡

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ሂሩት እቅድ ማውጣት ያስፈለጋት ለምንድነው? ምን ምን ተግባራት ይጠበቁባታል?
2. አበበ በትምህርት ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ስተለጠፈው መልእክት ትኩረት አለመስጠቱ ምንን ያመለክታል?

እቅድ ጊዜን ቅድሚያ ማግኘት የሚገባቸውን ተግባራት በቅድሚያ ለመፈጸም፣ ገንዘብን ደግሞ አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮቻችን በአግባቡ ማዋል የሚያስችለን መንገድ ነው፡፡ እቅድ በገንዘብ አወጣጥም ሆነ በጊዜ አጠቃቀም ቅድሚያ የሚሰጠውን ቅድሚያ ከማይሰጠው ለመለየት ይረዳል፡፡ በእቅድ መኖር ከችግር እንዲሁም ከውጥረት ለመውጣት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

**መልመጃ 8**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. እቅድ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በአቅም ልክ መኖር ማለትና ከአቅም በላይ መኖር ልዩነታቸው ምን እንደሆነ በአካባቢያችሁ ከሚኖሩ አርአያ ከሆኑ ሰው በመጠየቅ ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## 9.3 በቤተሰብ ውስጥ ቁጠባን የሚጻረሩ ተግባራት፤

- ስለቁጠባ ባገኛችሁት ግንዛቤ መሠረት በቤተሰባችሁ ውስጥ ቁጠባን የሚጻረሩ ተግባራት ምን ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡

የቁጠባ ባህላችንን የሚያናጉ በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ አንደኛው ባህላዊ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ግላዊ ነው፡፡

ባህላዊ የሚባለው በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የተለመዱ ከሰዎች አክብሮትንና ዝናን ለማግኘት ሲባል የሚደረጉ መስተንግዶዎች ናቸው፡፡ የተንዛዛ የተዝካር፣ የሰደቃ፣ የማህበራት እና የምርቃት ድግስ እንዲሁም ከልክ ያለፈ የበዓል አከባበር ሰዎችን በይሉኝታ ጥሪታቸውን እንዲያሚጥጡ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ በየባህሉ የአንድ ቤተሰብ አባል በሞት ሲለይ ቋሚዎቹ ቤተሰቦች የዚያን ሰው አርባ፣ ሰማንያ፣ ስድስት ወር፣ ሙት ዓመት በየጊዜው ሥርዓቱ ከሚያዘው ከመጠን በላይ እየደገሱ ሲያበሉ የሚታይበት ባህል አለ፡፡ አንድ የቤተሰብ ኃላፊ ወይም አባወራ ሲሞት በጓሮ የተተከሉ የእንሰት ተክሎች የሚነቀሉበት ባህልም አለ፡፡ እነዚህ ተግባራት በጣም ጎጂ ናቸው፡፡

ግላዊ የቁጠባ ባህል እንዳይኖር የሚያደርጉትን ደግሞ እንመልከት፡፡ የመጀመሪያው አቅምን አለማወቅ ነው፡፡ አቅምን አለማወቅ ማለት የገቢ መጠንንና ፍላጎትን አለማመጣጠን ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው ሰዎችን ለማስደሰት ሲባል የሚደረግ አቅምን ያላመዛዘነ ወጪ ነው፡፡ በርካታ ሰዎች ራሳቸውን ጎድተው ሰዎችን ማስደሰት የሕይወት ግብ ይመስላቸዋል፡፡ ከራሳቸው ደህንነት በፊት ለሰዎች መኖርን ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ የቤታቸውን ችግር ደብቀው ደግ ለመባል ብቻ እና የሰዎችን ምስጋና ለመቀበል ሲሉ የችግር መውጫቸውን አውጥተው ለሰዎች የሚጋብዙ፣ ስጦታዎችን በውድ ዋጋ ገዝተው የሚያበረክቱ አሉ፡፡ ሌላም ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዝቅተኛም ሆነ በከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች ለተማሪዎች የመመረቂያ ድግሥ በማዘጋጀት ከሁለት አቅጣጫዎች ችግሮችን የሚፈጥሩም አሉ፡፡

በአንድ በኩል የራሳቸውን ኑሮ ማቃወስ ሲሆን ሌላው ደግሞ ተጋባዦችን ለስጦታ መግዣ እንዲያወጡ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተግባራቸው በተቸገሩ ጊዜ ዋስትና አይሆኗቸውም፡፡

ሌላው ግላዊ የሆነው ቁጠባን የሚጻረር ችግር ደባል ሱስ ነው፡፡ ደባል ***ሱስ*** ማለት የአንድ መጥፎ ድርጊት ወይም ልማድ ተገዢ መሆን ማለት ነው፡፡ ሱስና ***ልማድ*** የሚመሳሰሉ ቢሆንም ልዩነት አላቸው፡፡

የመጠጥ ሱስ አልኮል መጠጥ ካልቀመሱ ተረጋግቶ ሥራን መሥራት አለመቻል ነው፡፡ የቁማር ሱስ ያለጊዜና ያለእቅድ በልዩ ልዩ የቁማር ጨዋታዎች መጠመድና ገንዘብን፣ ጊዜንና አካልን አላግባብ ማባከን ማለት ነው፡፡ እነዚህም ነጥቦች ደባል ሱሶች ይባላሉ፡፡ የመጠጥ፣ የአደገኛ እጾችና የቁማር ሱሰኛ መሆን ኑሮን በእቅድ እንዳይመሩ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ የሰዎች ጥገኛ መሆንና በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ሠላም ማጣትን ያስከትላል፡፡

**መልመጃ 9**

?

*ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ የተጠቀሱትን ተግባራት አንብባችሁ ሱስ የሚያስከትሉ መሆን አለመሆናቸውን ከጎን ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት መልሱ፡፡*

| ተግባራት | መልስ |
|---|---|
| ምግብ መመገብ | ሱስ ያልሆነ |
| ጊዜ ሳይወስኑ ካርታ መጫወት | ሱስ የሚያስከትል |
| አደንዛዥ እጽ መጠቀም | |
| አዘውትሮ አልኮል መጠጣት | |
| ቴምብር መሰብሰብ | |
| ሲጋራ ማጤስ | |
| ቁማር መጫወት | |
| እስፖርትን ማዘውተር | |

በሠንጠረዡ መሠረት ለሰጣችኋቸው መልሶች ምክንያቶቻችሁን በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ቁጠባ ማለት ከሚኖረን ገቢ ለወቅታዊ ፍጆታ የሚሆነን ተጠቅመን ለወደፊት የሚሆነንን ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ጥሩ የቁጠባ ባህልን በአቅም ልክ በመኖር ማዳበር ይቻላል፡፡ ቁጠባ ጥሩ ተግባር ሲሆን ተግባራዊ እንዳይሆን የሚጻረሩ ማህበራዊና ግላዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሠርግና ሌሎች አጋጣሚዎች ከአቅም በላይ በሆነ ወጪ ሲደገሱ በወደፊት ኑሯችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ገቢያችንን በአግባቡ ለሚያስፈልጉን ነገሮች በማከፋፈል መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ከሚያስፈልጉን ነገሮች መካከልም ለወደፊት የሚሆን ተቀማጭ መካተት ይኖርበታል፡፡

የቁጠባ ዓላማዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሊያጋጥም የሚችልን ችግር ለመቋቋም፣ የሌሎች ጥገኛ ላለመሆን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የቁጠባ ዓላማዎች ናቸው፡፡ ጥሩ የቁጠባ ባህል ማዳበር የሚቻለው በእቅድና በአቅም ልክ መኖር ሲቻል ነው፡፡

በአቅም ልክ መኖር ማለት አንድ ሰው በራሱ የኑሮ ደረጃ ወይም የሀብት መጠን ማድረግ የማይገባውን ነገር አለማድረግ ማለት ነው፡፡ በአቅም ልክ ለመኖር በእቅድ መመራት ወሳኝ ነው፡፡ እቅድ ማለት በጊዜና በገንዘብ አጠቃቀም ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ለይቶ በቅደም ተከተል ማከናወን ማለት ነው፡፡

አቅምን ከማወቅ ባሻገር በቤተሰብም ውስጥ የቁጠባ ባህልን የሚጻረሩ ግላዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ግላዊ የሚባሉት ብኩንነት፣ የአደገኛ እጽ እና የመጠጥ ሱሰኝነት ጥቂቱ ሲሆኑ ባህላዊ የሆኑት ቁጠባን የሚጻረሩ ሁኔታዎች ደግሞ ከልክ በላይ ድግስ፣ ተደጋጋሚ ማህበር እና ከመጠን ያለፈ የክብረ በዓላት ድግስ ናቸው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ልማድ፣** አንድ ሰው በተደጋጋሚ የሚፈጽመው ተግባር።

**ሱስ፣** አስተሳሰብን፣ የሥራ ባህልንና ኑሮን ለሚያናጉ አደገኛ እጾችና ልማዶች ተገዢ መሆን።

**እቁብ፡** የተወሰኑ ሰዎች የተወሰነ የገንዘብ መጠን በወር ወይም በሳምንት በማዋጣት እጣ ለሚወጣለት ተረኛ ለመስጠት የሚመሠርቱት ሕብረት።

**ጥሪት፣** ለወደፊት ሕይወት መኖሪያ የሚሆን ንብረት።

**ጥገኛ፣** አንድ ሰው ሰርቶ መኖር በሚችልበት የአካልና የአእምሮ ብቃት ላይ ሆኖ ራሱን ችሎ መኖር ሳይችል ሲቀር።

**ድል ያለ ድግስ፣** በከፍተኛ ደረጃ የተዘጋጀ፣ ሰፊ ድግሥ፣ ምግብና መጠጡ፣ እንዲሁም ተጋባዡ ከመጠን ያለፈ ብዛት ያለው።

**መጥነን፣** ወስነን፣ በልክ አድርገን፣ እንዳይበዛም እንዳያንስም አድርገን።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።***

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።

1. *መቆጠብ የሚችሉ ሀብታሞች ብቻ ናቸው።*
2. *ቁጠባ ማለት ከሚያስፈልግ አለታዊ ወጪ ላይ ቀንሶ ለመጪው ጊዜ ማስቀመጥ ማለት ነው።*
3. *ቁጠባ የአንድን ወር ገቢ ለአንድ ወር ኑሮ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ጊዜም እንዲሆን ማብቃቃት ነው።*
4. *ቁጠባ ሊታሰብ የሚችለው ከእለት ጠቀሜታችን ወይም ፍጆታችን ሲተርፈን ብቻ ነው።*
5. *አንድ ቤተሰብ ያለውን በማብቃቃት የሚቆጥበው ለወደፊት ልጆች በማሰብ ብቻ ነው።*

## II. በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉትጋር አዛምዱ።

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ድህነት፣ | ሀ. የቁጠባ አይነተኛ መርህ። |
| 2. በአቅም መኖር፣ | ለ. የተንዛዛ ወይም ከአቅም በላይ መደገስ። |
| 3. ለብክነት የሚዳርግ ባህል፣ | መ. መሰረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት አለመቻል። |
| 4. እቅድ፣ | ሠ. ጎጂ የዘወትር ተግባር። |
| 5. ሱስ፣ | ረ. ቅድሚያ ያለውን ከሌለው መለየት። |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።

1. *በአቅም ልክ መኖር ማለት፣*
   - ሀ. ፍላጎትን በሚያገኙት ገቢ መጠን መወሰን ነው፣
   - ለ. ወደፊት እንደሚያገኙ በመተማመን ተበድሮም ቢሆን የፈለጉትን ማድረግ ነው፣
   - ሐ. ስለነገ አለማሰብ ነው፣
   - መ. ሁሉም መልስ ነው።

2. *የቁጠባ ተጻራሪ የሆነው የቱ ነው?*
   - ሀ. ያገኙትን ሁሉ ለሌሎች ማካፈል፣
   - ለ. ከሌሎች አገኛለሁ በማለት ያለን መስጠት፣
   - ሐ. ተበድሮ ድል ያለ ድግስ መደገስ፣
   - መ. ሁሉም መልስ ነው።

3. ሱሰኛ መሆን ማለት፤
   ሀ. አንድን ሙያ አጥብቆ መያዝ፣
   ለ. በደባል ሱሶች ቁጥጥር ሥር መዋል፣
   ሐ. ልማዳዊ የሆነ በጎ አሰራርን ማጎልበት፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም።
4. ጥገኝነት፤
   ሀ. አብሮ መብላትና መጠጣት፣
   ለ. መተጋገዝ፣
   ሐ. የሌሎችን ምክርና ሐሳብ ማግኘት፣
   መ. የራስን አቅም ሳይጠቀሙ በሌሎች ተጠቃሚ መሆን።
5. እቅድ፤
   ሀ. የቁጠባ መሠረት ነው፣
   ለ. የጉብዝና መሠረት ነው፣
   ሐ. ጊዜ እንዳይባክን ያደርጋል፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. ሱስን ከሚያስከትሉ ልምዶች መካከል __________ እና________ ይጠቀሳሉ።
2. ለብክነት ከሚዳርጉ ኋላ ቀር ጎጂ ተግባራት መካከል__________-እና ________ይጠቀሳሉ።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።

1. በአካባቢያችሁ ስንት የድግስ ዓይነቶች አሉ? ሁለቱን ብቻ ጥቀሱ።
2. ቁጠባ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በእቅድ መመራት ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል ሁለቱን ጥቀሱ።

# ምዕራፍ አሥር

# ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምንነትን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፤
- ሕዝባዊ ተሳትፎ ለዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፤
- በትምህርት ቤትና በአካባቢ የዲስፕሊን፣ የጽዳትና የልማት ተግባራት ላይ የመሣተፍን አስፈላጊነት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፣

## 10.1 የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምንነት



*ሥዕል 10.1 አካባቢያችንን በጋራ እናጽዳ*

- ከላይ ከቀረበው ሥዕል ምን ተረዳችሁ?
- በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባር ላይ የተሰማሩት ለምንና እንዴት እንደሆነ ግለጹ፡፡

### የአምስተኛ «ለ» ክፍል ችግር

አብዛኞቹ የአምስተኛ «ለ» ክፍል ተማሪዎች በክፍላቸው ሁኔታ ደስተኞች አልነበሩም፡፡ ባለፈው ሳምንት መምህር ያልገባበት ክፍለ ጊዜ ስለአገኙ ይህንኑ ለስብሰባ ሊጠቀሙበት ተስማሙ፡፡ ገና ውይይቱ ሲጀመር ቁም ነገር የማይሆንላትና ጨዋታ ወዳዷ አዘነጋሽ አመመኝ ብላ ውሽቷን እያቃሰተች ወጣች፡፡ ሥራዋን ያወቀው ወንድሟ ስለሺም እህቱን እንደ መደገፍ ብሎ አብሯት ወደ ጨዋታ ሄደ፡፡

በውይይቱ መጀመሪያ የተናገሩት ከማልና ሐዋ ነበሩ፡፡ እነሱም ላለፉት አራት ሳምንታት ሌሎቹ የክፍል ጓደኞቻቸው አርአያነታቸውን ተከትለው አብረዋቸው እንደሚሆኑ ተስፋ በማድረግ ክፍላቸውን ሲያፀዱ ሰንብተው እንደነበር አስታወሱ፡፡ ሆኖም አንድም ሰው እነሱን ተከትሎ አብሯቸው ባለማፅዳቱ ማዘናቸውን ገለፁ፡፡

ሌሎቹም ተራ በተራ ስለክፍላቸው በጣም መቆሸሽ በተለይም ከማልና ሐዋ ካቋረጡ ወዲህ ችግሩ መባባሱን አብራሩ፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የነከማልን አርአያ ባለመከተላቸው ራሳቸውን ወቀሱ፡፡ በዚህ አኳኋን በቂ ውይይት ከተካሄደ በኋላ በጉዳዩ ሁሉም ስላመኑበት በዚሁ ዕለት ክፍሉን ለማጠብና ለማስዋብ ወሰኑ፡፡

ገመቹ ልብሴና ጫማዬ ይበላሻል በሚል ሰበብ እንደዓለሚቱ ከዳር ቆሞ በርቱ እያለ ያጨበጭባል፡፡ በውይይቱ ወቅት "እንነሳ፤ አሁኑኑ እናጽዳ፤" እያለ ገንቢ አስተያየቶችን ያቀረበ ቢሆንም በመጨረሻ በፈፀመው ተግባር ብዙዎቹ ቅር ተሰኙበት፡፡

ጫማቸውን አውልቀው በትጋት ከሚሠሩት ጓደኞቿ ከኤቢሴ፣ ከመስከረምና ከአብረኸት የተለየችው ዓለሚቱም ጫማዬ አልተመቸኝም ብላ ከዳር በመቆም ታበረታታቸዋለች፡፡

በውይይቱም እያንዳንዳቸው ሲያፈልቁ በነበሩበት ገንቢ አስተያየቶች ዳብሮና ውሳኔ አግኝቶ የተከናወነው የፅዳት ሥራ በጣም አርኪ ሆኖ ተጠናቀቀ፡፡ ክፍሉም ፅዱና በተገቢዎቹ የትምህርት መርጃዎች ያሸበረቀ ሆነ፡፡ ሥራው እንደተጠናቀቀ የአስር ደቂቃ ስብሰባ ተደርጎ ውጤቱ ተገመገመ፡፡

ከፍተኛ ትጋት ላሳዩት ተማሪዎችና ቀደም ሲል ልዩ ጥረት ላደረጉት ለከማልና ለሐዋ የአድናቆት ጭብጨባ ተደረገላቸው፡፡ በመጨረሻም ከሂደቱ ሁሉም ጠቃሚ ትምህርት እንደቀሰሙ ለማረጋገጥ ተቻለ፡፡

## የቡድን ሥራ፣

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሥራት በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡***

1. የአምስተኛ «ለ» ክፍል ተማሪዎች ያከናወኗቸው ተግባራት ተገቢ ናቸውን? ለምን?
2. የአምስተኛ «ለ» ክፍል ተማሪዎች በፈፀሟቸው ተግባራት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ያደረጉና ያላደረጉ አባላት ነበሩ? ልዩነታቸው ምን ይመስላል?
3. የከማልና የሐዋ የመጀመሪያ ጥረት ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አኳያ እንዴት ይመዘናል?

ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩ ተማሪዎች ያከናወኗቸው ልዩ ልዩ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ተግባራት እንደ የሁኔታቸው በሁለት ምድብ ክፈሉ፡፡ አንዱ ምድብ «በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የተከናወኑ» የሚል ሌላው ምድብ ደግሞ «በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ያልተከናወኑ» በሚል ይቅረብ፡፡ ለመልሶቹም ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡

1. የክፍላችን አለቃ ሁሉንም ችግር በጉልበት ብቻ ለመፍታት የሚሞክር ነበር፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ተሰብስበን በመወያየት በድምፅ ብልጫ አዲስ አለቃ መረጥን፡፡
2. ትምህርት ቤታችን የችግኝ ተከላ ዘመቻ መጥራቱን ተከትሎ ከክፍላችን ብዙ ተማሪዎች በሥፍራው ተገኝተው ተክለዋል፡፡
3. የክፍላችን አለቃ ክፍላችን የሚተዳደርበትን ደንብ አዘጋጅቶ በመምጣት በንባብ ከአሰማን በኋላ በጭብጨባ እንድናፀድቀው አስደረገ፡፡

***ከሚከተሉት መልመጃዎች መካከል አንዱን በመውሰድ በቡድን አነስተኛ ጥናት አከናውኑ፡፡ ውጤቱንም በቀጣይ ክፍለ ጊዜ በመምህራችሁ አማካኝነት ለክፍል አቅርባችሁ ተወያዩበት፡፡***

1. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ጥሩ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሁለት ክበባት ምረጡ፡፡ ከዚያም ስለአመሠራረታቸው፣ ስለዓላማቸው፣ ስለመተዳደሪያ ደንባቸው፣ ስለአደረጃጀታቸው፣ ስለሥራ እቅዶቻቸውና ስለአከናወኗቸው ዋናዋና ተግባራት ግለጹ፡፡ በማያያዝም አባሎቻቸው ስለሚያደርጉት የተሳትፎ ዓይነትና ደረጃ አቅርቡ፡፡ የሁለቱን ክበባት ልዩነትም አነፃፅሩ፡፡ የቱ ይሻላል? ለምን?
2. በመኖሪያችሁ አካባቢ በጥሩ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ሁለት ማህበራዊ ድርጅቶችን ምረጡ፡፡ ከዚያም ስለሁለቱም አመሠራረት፣ ዓላማ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ አደረጃጀት፣ የሥራ እቅዶችና የአከናወኗቸውን ዋና ዋና ተግባራት ግለጹ፡፡ በማያያዝም አባሎቻቸው ስለሚያደርጉት የተሳትፎ ዓይነትና ደረጃ ሰፋ አድርጋችሁ አቅርቡ፡፡ የሁለቱን ድርጅቶች ልዩነትም አነፃፅሩ፡፡ የቱ ይሻላል? ለምን?

በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ምን ጊዜም ራሳችሁን ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ዝግጁ ልታደርጉ ይገባል፡፡ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሰዎች አንድ ውጤት ሊያመጣ በሚችል ተጨባጭ ተግባር ላይ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን መነሻ ያደርጋል፡፡ ለዚህም የራስ ተነሳሽነትና ትጋት ያስፈልጋል፡፡

ይህ ዓይነቱ ተሳትፎ ይበልጥ ውጤታማ ይሆን ዘንድ መከናወን ያለበት በግል ብቻ ሳይሆን በጋራ ነው፡፡ በመሆኑም ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የራስ ተነሳሽነት ያለበትና በጋራ የተሰማሩበት ውጤታማ የሆነ ተጨባጭ ድርጊት ነዉ፡፡

## 10.2 የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት



*ሥዕል 10.2 ተማሪዎች በችግኝ ተከላ ተሳትፎ*

- ከላይ በቀረበው ሥዕል መሠረት የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነትን ግለጹ፡፡

### ተፎካካሪዎቹ

ነስሮና ወላይቴ የክፍል ጓደኛሞች ናቸው። ሁለቱም በክፍል ውስጥ በጨዋነታቸውና በትጋታቸው እንዲሁም በትምህርት አቀባበል ከሁሉ በመላቃቸው ይታወቃሉ፡፡ አንዳንዴ በትምህርት ጉዳዩች ላይ ሲከራከሩ የሚጣሉ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን ከክርክራቸው በኋላ እንደቀድሟቸው በሠላም ሲነጋገሩ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ተከራክረው ከአንድ ስምምነት ላይ ለመድረስ ሊያቅታቸው የማን ሐሳብ ትክክል እንደሆነ ለማረጋገጥ ተያይዘው ወደ ሚመለከተው መምህር በመሄድ አንዳቸው በድል ይመለሳሉ፡፡

አንድ ቀን እንደልማዳቸው ሲከራከሩ ከማይስማሙበት ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡ ነስሮ «በአንድ ክበብ ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በማድረጋችን ልንጠቀምም ላንጠቀምም እንችላለን» ይላል፡፡ ወላይቴ ደግሞ ምን ጊዜም ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የጋራም ሆነ የግል ጠቀሜታ እንደሚገኝ ታስረዳዋለች፡፡ ነስሮ ግን በዚህ አልተስማማም፡፡ ለምሳሌ በትምህርት ቤታቸው የአካባቢ ጥበቃ ክበብ ውስጥ በችግኝ ተከላ ፕሮግራም በመሳተፋቸው እሱና እሷ በየግል ያገኙት ምንም ነገር እንዳልነበረ ይገልጻል፡፡

ወላይቴም በሰጠችው ምላሽ ከችግኝ ተከላው የመንፈስ እርካታ፣ ልምድና እውቀት እንዳገኙና ወደፊትም ደኑ ባይኖር ሊደርስ ከሚችል ጉዳት እንደሚጠብቁ አስረዳችው፡፡ በዚህ ጊዜ በድንገት ከፊት ለፊት የተደፋ ቁሻሻ ይመለከታሉ፡፡ ነስሮም ይህንኑ በአስረጅነት በመውሰድ በክበባቸው ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በማድረግ እንዲህ የተዝረከረከውን ቆሻሻ እንዳላነሱ አስረዳ፡፡

አያይዞም ባለማንሳታቸው በሁለቱም ላይ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰ፣ ወይም ቢያነሱ ኖሮ ምንም የግል ጥቅም እንዳላገኙ ያብራራ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ በድንገት ሳያይ በአንድ የሙዝ ልጣጭ ላይ ስለቆመ አንሸራቶት ክፉኛ ወደቀ፡፡ ወላይቴ ጮሃ ልታቀናው ስትታገል ሌሎች ተማሪዎች ደረሱላትና ተረዳድተው አነሱት።

«አሁን ተረጋግጧል፣ በክበባችን በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የጽዳት ሥራ አከናውነን ቢሆን ኖሮ ሁላችንም ለግቢያችን ንጽህና ተቆርቋሪዎችና ባለቤቶች በሆንን ነበር፡፡ እኔንም በግሌ በጠቀመኝና ከዚህ ከደረሰብኝ ጉዳትም በጠበቀኝ ነበር፡፡ አሳምነሽኛል፡፡ ተረትቻለሁ፡፡ አንቺ ትክክል ስለሆንሽ ወደ መምህሩ ዘንድ መሄድ አያስፈልገንም» ብሏት ተያይዘው ተመለሱ፡፡

**መልመጃ 1**

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ነስሮ ያገኘው ትምህርት ምንድነው?
2. ነስሮና ወላይቴ በትምህርት ቤታቸው የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት ናቸው። በችግኝ ተከላም ሆነ በግቢ ጽዳት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ቢያደርጉ ኖሮ ሊያገኙ ይችሉ ከነበሩት ጥቅሞች መካከል ሦስቱን ዘርዝሩ፡፡

3. እስኪ እናንተ ደግሞ በራሳችሁ ትምህርት ቤት ልታከናውኑ የምትችሉትን ጠቃሚ ተግባር አቅርቡ፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥም ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ባታደርጉ ልታጡ የምትችሉትን ሦስት ነገሮች ዘርዝሩ።

እስከአሁን እንደተማራችሁት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተመልክታችኋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ተሳትፎ በጋራ ከሚያስገኘው ውጤት ባሻገር እያንዳንዱ አባልም በተናጠል የሚያገኘው ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በክፍል የአለቃ ምርጫ፣ በትምህርት ቤት የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ማፅደቅ፣ የክፍልን ችግር ለመፍታት የሚካሄድ ስብሰባ፣ ክፍልን ለማፅዳትና ለማስዋብ የሚደረግ እንቅስቃሴ፣ የትምህርት ቤትን ሀብትና ንብረት የመንከባከብ ተግባር፣ ወዘተ ተማሪዎች በትጋትና በተነሳሽነት በጋራ ሊሳተፉባቸው ይገባል፡፡

ይህንን ማድረግም ለየግለሰቡ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ ለምሳሌ ጉልበተኛ ጥቃት አያደርስባቸውም። ጥሩ የሆነ የትምህርት ሥርዓት ይሰፍንላቸዋል፡፡ ጤናን የማይጎዳና መንፈስን የሚያረካ መማሪያ ክፍል ይኖራቸዋል፡፡ እንዲሁም ትምህርትን በጥሞና ለመከታተል የሚያስችል ተስማሚ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

**መልመጃ 2**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. በትምህርት ቤታችሁ ከሚገኙ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብቶች መካከል ተገቢ እንክብካቤ ያላገኙ ደናሪሉ? ከኖሩ ዘርዝሯቸው፡፡
2. ተገቢውን እንክብካቤ ያላገኙት ንብረቶች ምን ሲደረግላቸው ይገባል?
3. ሲደረግላቸው የሚገባው እንክብካቤ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ያስፈልገዋል? እንዴት?

## 10.3 የሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶች



*ሥዕል 10.3 ትምህርት ቤታችንን እናስውብ*



*ሥዕል 10.4 አካባቢያችንን እናልማ*

- ከላይ የቀረቡት ፎቶግራፎች ምንን ያሳያሉ?
- በሁለቱ ፎቶግራፎች መካከል ያለው መመሳሰል ምንድነው? ልዩነታቸውስ?

እስከአሁን ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምን እንደ ሆነና ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ለመገንዘብ ችላችኋል። አሁን ደግሞ የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶችን ትመለከታላችሁ፡፡

ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ አንደኛው በትምህርት ቤት የሚካሄድ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በመኖሪያ ወይም በሥራ አካባቢ የሚካሄድ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው፡፡

**መልመጃ 3**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡***

1. በትምህርት ቤታችሁ የሚንቀሳቀሱትን ክበባት ስም ዘርዝሩ፡፡ ክበባት ከሌሉ እንዴት ያሉ ክበባት ሊቋቋሙ እንደሚገባቸው አስረዱ፡፡
2. በመኖሪያችሁ አካባቢ (በቀበሌዎቻችሁ) የሚገኙትን ማህበራዊ ድርጅቶች ስም ዘርዝሩ፡፡ ድርጅቶች ከሌሉ እንዴት ያሉ ማህበራዊ ድርጅቶች ሊቋቋሙ እንደሚገባቸው አስረዱ፡፡
3. በትምህርት ቤት ያሉት ወይም ሊቋቋሙ የሚገባቸው ክበባትና በቀበሌ ያችሁ ያሉት ወይም ሊቋቋሙ የሚገባቸው ማህበራዊ ድርጅቶች በምን በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ?

| በትምህርት ቤት የሚካሄድ | በመኖሪያ አካባቢ የሚካሄድ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |


**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ሕዝባዊ ተሳትፎዎች በሁለት ዓይነቶች በመመደብ መልሳችሁን ከታች ያለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡***

?

1. በተማሪዎች ካውንስል/ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት በብቃት መሥራት።
2. የትምህርት ቤቱ የስካውት ክበብ የቡድን መሪ በመሆን ኃላፊነትን በሚገባ መወጣት።
3. ለኤች አይቪ ታማሚዎች እንክብካቤ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት መሰማራት።
4. በትምህርት ቤቱ የቀይ መስቀልና የቀይ ጨረቃ ክበብ አባል በመሆን የተሟላ እንቅስቃሴ ማድረግ፡፡
5. የተማሪዎች የበጎ አድራጎት ክበብ አባል በመሆን የሥራ ድርሻን በአጥጋቢ አኳኋን መፈፀም።
6. በገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ጠንካራ የማህበር አባል ሆኖ መንቀሳቀስ፡፡

## 10.4 የሲቪክ ማህበራት



*ሥዕል 10.5 የቀይ መስቀል/ጨረቃ ማሕበር*



*ሥዕል 10.6 የመምህራን ማሕበር ጉባዔ*

- ከላይ ያሉት ፎቶግራፎች ምንን ይገልፃሉ።
- ሁለቱን ፎቶግራፎች የሚያመሳስላቸው ምንድነው? የሚያለያያቸውስ?

የሲቪክ ማሕበር ማለት የንግድ ያልሆነ፣ ከፖለቲካና ከመንግሥት ነፃ የሆነ ድርጅት ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ፍላጎቶቹን በራሱ ግላዊ ጥረት ብቻ ለማሟላት አይችልም፡፡ የጋራ ጥረቶች ብዙ ነገሮችን ያሳካሉ፡፡ ማንኛውም ሕዝብ ሕይወቱን ለማሻሻል ከፈለገ የተለያዩ ማሕበራዊ ልማቶችን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የልማት ሥራዎቹ በጋራ መከናወን ይገባቸዋል፡፡

በጋራ ለመሥራት ደግሞ መደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች የተለያዩ ዓይነት ድርጅቶችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም አንዱ የሆነውና ከሌላው በባሕርይ የሚለየው የሲቪክ ማህበር ነው፡፡ ከሲቪክ ማሕበራት ባህርያት መካከል አንደኛው በመንግሥት የሚመሩ ባለመሆናቸው ነፃ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ዓላማቸው ትርፍ ማስገኘት ሳይሆን ማሕበራዊ አገልግሎት ማበርከት ብቻ ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ገቢያቸውን የሚያገኙት ከአባሎቻቸው መዋጮና ከሌሎች ለጋሾች በመሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻም የፖለቲካ ወገንተኝነት የላቸውም፡፡ ሰዎች በሲቪክ ማህበራት ውስጥ ተሰማርተው የሚያገለግሉት በበጎ ፈቃድ አሊያም በማሕበሩ በመቀጠር ነው፡፡

የሲቪክ ማህበራት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማደግ፣ ለጋራ ሠላምና ለልማት መፋጠን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ማሕበራዊ ተቋማት ናቸው፡፡

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የሚከተሉትን ባህሪያት የሚያሟሉትንና የማያሟሉትን ድርጅቶች ቀጥሎ ከቀረበው ዝርዝር ለዩ፡፡ መልሱን ከሥር ያለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ስጡ፡፡

**ባህርያት - የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለው**
- በመንግሥት የማይመራ (ከመንግሥት ነጻ የሆነ)
- በአባላቱ በጎ ፈቃድ የሚንቀሳቀስ
- ለአትራፊነት ያልተደራጀ
- ገቢውን ከአባላቱ መዋጮና ከለጋሾች የሚያገኝ

- የወረዳ የልማት ማህበር
- የሴቶች ማህበር
- የንግድ ማህበር
- የመንግሥት መሥሪያ ቤት
- የፖለቲካ ድርጅት
- የወጣቶች ማህበር
- የሙያ ማህበር
- የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች እድር
- መንግሥታዊ ያልሆነ የረድኤት ድርጅት
- የሰራተኞች ማህበር

2. ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት የሚያሟሉ ድርጅቶች በጋራ ምን ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ?

| ባህርያቱን የሚያሟሉ | ባህሪያቱን የማያሟሉ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

3. እስካሁን በሠራችሁት ላይ በመመሥረት አሁን ደግሞ እስኪ ስለሲቪክ ማህበር ምንነት አጭር ማብራሪያ በማቅረብ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አንድ ሰው በተነሳሽነት ከሌሎች ጋር በጋራ የሚያከናውነው ተጨባጭ ተግባር ነው፡፡ በትምህርት ቤት በሚከናወኑ ሥራዎች ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማድረግ ከማንኛውም ትጉህ ተማሪ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ተጨማሪ ልምድና እውቀት ለማግኘትና ከውጤቱም ለመጠቀም ያስችላል፡፡

ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የጋራ እንቅስቃሴን ይሻል። ገንዘብን፣ ጉልበትንና እውቀትን አዋህዶ በጋራ መሥራት በላቀ ሁኔታ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ በጋራ ለመሥራት ከሚደራጁት አካላት መካከል የሲቪክ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ተቋማት የሚካሄድ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለዴሞክራሲ ማደግ፣ ለሠላም መረጋገጥና ለልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ሲቪክ፣** | ፖለቲካዊና ወታደራዊ ያልሆነ። |
| **ተጨባጭ ተግባር፣** | የይስሙላ ሳይሆን ውጤታማ የሆነ ሥራ። |
| **ተነሳሽነት፣** | በጉትጎታ ሳይሆን በራስ ውስጣዊ ግፊት አንድን ተግባር ማከናወን። |
| **መደራጀት፣** | ስጋራ ውጤት ቡድን ወይም ማህበር ማቋቋም። |
| **የልማት ሥራ፣** | የህብረተሰቡን እድገት ለማምጣት የሚረዳ ውጤታማ ተግባር። |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::

1. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ተጨባጭ የሆነ የተግባር እንቅስቃሴ ይሻል፡፡
2. ሁለቱ የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶች የሲቪክ ማሕበራትና ማሕበራዊ ድርጅቶች ናቸው፡፡
3. ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አባላት በግል ሊያገኙ የሚችሉት ጠቀሜታ አይኖርም፡፡
4. የንግድ ድርጅት  የሲቪክ ማሕበራት አንዱ ምሳሌ ነው፡፡
5. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መኖሩን ከሚያረጋግጡት ነገሮች መካከል አንዱ እንቅስቃሴው በጋራ የሚካሄድ መሆኑ ነው፡፡

## II. በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉትጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የፖለቲካ ወገንተኝነት አለመኖር፣ | ሀ. በትምህርት ቤት የተቋቋመ የሲቪክ ማሕበር። |
| 2. የመረዳጃ እድር፣ | ለ. የሲቪክ ማሕበራት የሚያስከትሉት ጉዳት። |
| 3. ተጨባጭ ተግባር ማከናወን፣ | ሐ. በመኖሪያ አካባቢ የሚገኝ የሲቪክ ማህበር። |
| 4. የተማሪዎች የፀረ ኤች.አይቪ. ክበብ፣ | መ. የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ግላዊ ጠቀሜታ። |
| 5. የልምድ መዳበር፣ | ሠ. ከሲቪክ ማሕበር ባህሪያት አንዱ። |
| | ረ. የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ብያኔ። |
| | ሰ. የንቁ  ሕዝባዊ ተሳትፎ አንዱ ባህርይ:: |

## III. ለሚከተሉት ፐያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ____________ የሚታይበት እንቅስቃሴ ነው፤
   ሀ. በጋራ መሥራት፣ ሐ. ተነሳሽነት፣
   ለ. ተጨባጭ ተግባር፣ መ. ሁሉም ትክክል ናቸው፡፡
2. የሲቪክ ማሕበራት መለያ ባህርይ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ.ለአትራፊነት የሚሠሩ አይደለም፣ ሐ. የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊሆኑ ይችላል፣
   ለ. ከመንግሥት ነፃ ናቸው፣ መ. ገቢውን ከአባላቱ ያገኛል፡፡

3. የትጉህ ተማሪ መለያዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ________ ነው፤
   ሀ. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማድረግ፣ ለ. የክፍል አለቃ መሆን፣
   ሐ. በአስተማሪዎቹ መወደድ፣ መ. ሁሉም ትክክል ናቸው፡፡
4. የሲቪክ ማሕበራት ከሆኑት መካከል አንዱ ___________ ነው፤
   ሀ. የወረዳ አስተዳደር ማሕበራዊ ዘርፍ፣ ለ. የሙያ ማህበር፣
   ሐ. የመንግሥታት ሕብረት፣ መ. መልሱ አልተሰጠም።
5. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለግለሰብ የሚያስገኘው ጥቅም _________፤
   ሀ. እውቀትና ልምድ ነው፣ ለ. ምንም አይኖርም፣
   ሐ. የሀብትና ብልፅግና ነው፣ መ. መልሱ አልተሰጠም፡፡
6. በጋራ መሥራት ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚያመጣው ጥቅም_______፤
   ሀ. ይበልጥ ውጤታማ ማድረጉ፣
   ለ. እውቀት ሀብትና ችሎታን ለማቀናጀት፣
   ሐ. ሀ እና ለ ትክክል ናቸው፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም።

## IV. የሚከተሉት ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሐረግ ሙሉ::

1. ሁለቱ የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶች ____________ እና ____________ ናቸው፡፡
2. ለዴሞክራሲ ሥርዓት መዳበር፣ ለጋራ ሠላምና ለልማት መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መንግሥታዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ያልሆነ ድርጅት ____________ ነው፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::

1. ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አጭር ትርጉም ስጡ፡፡
2. የሲቪክ ማሕበርን ምንነት የሚያሳዩ አምስት መለያ ባህርያቱን ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አንድ
# ዕውቀትን መሻት


**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፣***

- ዕውቀትን መሻት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፤
- የዕውቀት ባለቤት መሆን ለራስ ኑሮ መሻሻልም ሆነ ለሕብረተሰብ ዕድገት ያለውን አስተዋፅኦ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፤
- ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን የዕውቀትና የማስረጃን አስፈላጊነት ትረዳለህ/ትረጃለሽ::

## 11.1. የዕውቀት ምንነትና ጥቅም፤



*ሥዕል 11.1*



*ሥዕል 11.2*



*ሥዕል 11.3*

- ከላይ የቀረቡትን ሥዕሎች ምንነትና ለሰዎች የሚኖራቸውን ጥቅም ግለጹ::
- ስለነዚህ ነገሮች እንዴት ልታውቁቻላችሁ?
- ለሁለቱ ጥያቄዎች ከሰጣችኋቸው መልሶች አንጻር ስትመለከቱት፣ አንድን ነገር ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው?

### የተማሪዎቹ ውይይት

ዘይነባ፣ ሙሐባ፣ ለማና ጉተማ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ከዕለታት አንድ ቀን የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መምህርታቸው ወ/ሮ ኪሮስ የቤት ሥራ ሰጧቸው:: የቤት ሥራውም «የተለያዩ መረጃዎችን ተጠቅማችሁ የዕውቀትን ምንነት አብራሩ» የሚል ነበር:: ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ዙሪያ በማንበብ፣ በመከራከርና በመወያየት መሳተፍ ያረካቸው ነበር:: በመሆኑም የቤት ሥራው ሲሰጣቸው በጣም ተደሰቱ::

ተማሪዎቹ የቤት ሥራውን ከተቀበሉ በኋላ በየበኩላቸው የተለያዩ መረጃዎችን ፍለጋ ተሰማሩ:: መጻሕፍትን አነበቡ፣ ሰዎችን አነጋገሩ:: ከዚያም እያንዳንዳቸው ያገኟቸውን መልሶች ይዘው ለጋራ ውይይት ተገናኙ:: በጉዳዩ ላይም ብዙ ተከራከሩ:: ያቀረቧቸውም መልሶች ባጭሩ የሚከተለውን ዓይነት ነበሩ::

***ዘይነባ፣*** "ዕውቀት ማለት በቅርባችን ያሉ ነገሮችን፣ ቦታዎችንና ሰዎችን በተመለከተ የሚኖረን ግንዛቤ ነው" በማለት ተናገረች::

***ሙሐባ፣*** "ዕውቀት የሚባለው የነገሮችን ጠቃሚነትና ጎጂነት የምንረዳበት የአእምሮ መሣሪያ ነው"። በማለት መልሱን አቀረበ::

***ለማ፣*** ዕውቀት ስለእንስሳት፣ ስለመሬት፣ ስለ አየር ሁኔታ፣ ስለቴክኖሎጂ የምንገነዘበው ነው::

***ጉተማ፣*** ዕውቀት የምንለው ከመምህራን፣ ከመጽሐፍ፣ አካባቢን ከማጤንና ከማጥናት የምናገኘው ግንዛቤ ነው::

ከዚያም የየራሳቸውን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው አቀረቡ:: ተማሪዎቹም በትኩረት ያዳምጧቸው ነበር:: መምህርቷም በተማሪዎቻቸው ጥረት በጣም ደስ ተሰኙ::

መገናኛ ብዙኃንን በመከታተል እንዲሁም በጉብኝት የምናገኘው ቁምነገር ዕውቀት ይባላል:: ስለ ዚህ ከላይ የተጠቀሱት አራቱም ተማሪዎች የዕውቀትን ምንነት በትክክል ገልፀዋል ማለት ይቻላል::

እውቀት ከተለያዩ ተጽዕኖዎች ነጻ እንድንሆን የሚያግዘን መሣሪያ ነው:: ለምሳሌ ጥራት ያለው ቤት ሠርተን በመኖር ብርድ፣ ዝናብና ፀሐይ የመሳሰሉ የተፈጥሮ ጉዳቶችን እንከላከላለን:: ይህ ታዲያ የቤት አሠራር ዕውቀትን ይጠይቃል::

በሽታ እንዳያጠቃን የሚያደርጉ ነገሮችንም በዕውቀት እንደርስባቸዋለን:: ስናውቃቸውም እንዳያጠቁን የሚያስችል የመከላከያ ዘዴ እንቀይሳለን፤ ካጠቁንም ለመዳን የሚያስችል መድኃኒት እንድናገኝ ዕውቀት በጣም ያስፈልገናል:: ስለዚህ ዕውቀት እየተሻሻለ በሄደ ቁጥር ኑሮም በጣም ይሻሻላል::

እናንተም በትምህርት ቤት የተሻለ ዕውቀት በገበያችሁ ቁጥር የበለጠ ጎበዝና ተመራማሪ ተማሪዎች ትሆናላችሁ:: ይህም በተራው የላቀ ዕውቀት እንዲኖራችሁ ያግዛችኋል::

## መልመጃ 1

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ተወያዩባቸው::***

?

1. ከአራቱ ተማሪዎች መልሶች መካከል ስለዕውቀት ምንነት ስሕተት የሆነ መልስ አስተውላችኋል? እንዴት?
2. እናንተስ «ዕውቀት ምንድነው» ስሚለው ጥያቄ አሁን ምን መልስ አላችሁ?

ዕውቀት አካባቢንና ዓለምን የመረዳት ሂደት ነው:: ሰው አካባቢውን በመመልከት አስተሳሰቡን ያሰፋል:: ከሰዎችም መረጃዎችን በማግኘት አእምሮአችንን እናሰፋለን:: ትምህርት ቤትም ገብተን ከመምህራንና ከመጻሕፍት ብዙ ቁምነገር እንቀስማለን፣ ይህም ዕውቀት ምን እንደሆነ ያሳየናል::

## መልመጃ 2

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው::***

?

1. ዕውቀት አንዴ የምንማረው ነገር እንጂ እየተሻሻለና እየዳበረ የሚሔድ አይደለም ቢባል ትክክል ነው ትላላችሁ? ለምን?
2. የተሻለ መጠለያ ለመገንባት ከዕውቀትና ከገንዘብ ቀድሞ የሚያስፈልገን የትኛው ነው?
3. ከፍ ያለ ዕውቀት ካለውና ዝቅ ያለ ዕውቀት ካለው ሰው ሀገሩን የበለጠ የሚጠቅመው የትኛው ነው? እንዴት?

## 11.2 መረጃ የሚገኝባቸው ዘዴዎች







*ሥዕል 11.4 የተለያዩ የመረጃ ምንጮች*

- ከላይ የምትመለከቱት ሥዕል ስለመረጃ ማግኛ ዘዴ ምን ፍንጭ ይሰጣችኋል?
- መረጃዎችን ከምን ከምን የምናገኝ ይመስላችኋል?
- አዘውትሮ መረጃን ማግኘት ምን ጥቅም አለው?

### ራስ ስሞሽ

"ራስ ስሞሽ" የሚባለው የሥራ መረዳዳት ልማድ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን አርሶ አደሮች ዘንድ የተለመደ ነው:: በራስ ስሞሽ አማች ለአማቾቹ ሥራ የሚያግዙ ሰዎችን ቡድን ይዞ ይመጣል:: የሥራ ቡድኑን የማምጣቱ ፍላጎት የሚመነጨው ከሚስት ቤተሰቦች ወይም ከራሱ ከአማችየው ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ሁለቱም መንገዶች ግባቸው በአብዛኛው የአጨዳ ሥራን ተረዳድቶ መሥራት ነው:: በዚያውም በተጋቢዎች ቤተሰቦች መካከል ያለውን የመ ረዳዳት ባሕልን ያዳብራል። የሥራ ቡድኑ ብዙ የሰው ኃይል የሚያቅፍ ሆኖ ለየት ባለ መንፈስ ሥራን የማከናውን አደራ ይጣልበታል::

ይህ በርከት ያለ የሰው ኃይል የአማቾችንም የመስተንግዶ ብቃት የሚያስገመግም ነው:: በተ ለይ የራስ ስሞሹ ጠያቂዎች አማቾች ከሆኑ በእነሱ በኩል ከፍተኛ ድግስ ይደገሳል:: ጠላው፣ አረቄው፣ ዳቦው፣ እንጀራና ወጡ በልዩ ጥንቃቄ ይሰናዳል:: የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት ከሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ለሥራው የተለመኑትን ሰ ዎች በመስተንግዶ ደስ አሰኝቶ መመለስ ለአ ማት ቤተሰብ ትልቅ ክብርና ዝና ያስገኛል፡

ታዲያ የድግሱ ወጪ አማችየውንም ሊመለ ከት ይችላል:: ምክንያቱም እንደሁኔታው የተ ወሰኑ ነገሮችን ለመስተንግዶ ማገዣ እንዲያ ቀርብ ሊጠበቅበት ይችላል::

በተለይ ደግሞ ይህን የሥራ ቡድን የማዘጋጀቱ ሐሳብ የአማችየው ከሆነ፣ ድግስ የማዘጋጀት ኃላፊነት የራሱ በአማችየው ይሆናል:: ራሱ አስ ደግሶ በአህያ ጭኖ ይመጣል:: ያም ሆኖ ታዲያ አማቾችም ቢሆኑ ቢያንስ አንድ ሙክት ማረድ አይቀርላቸውም::

ከዚህም አልፎ የሥራ ቡድኑ ሲሠራ ውሎ ከቦታ ርቀት የተነሳ ወደቤቱ መመለስ ካል ቻለ፣ በዚያው ለሥራ በሄደበት ቤት ማደሩ የተ ለመደ ነው::

**መልመጃ 3**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ስስራስ ስሞሽ የጻፈው ሰው ለጽሑፉ ማዳበሪያ መረጃ ከየት ያገኘ ይመስ ሳችኋል?
2. ጸሐፊው መረጃውን እንዴት ሲሰበስብ ቻለ?
3. ዕውቀትን ከምን ከምን መረጃዎች ማግኘት ይቻላል ትላላችሁ?

መረጃ በጽሑፍ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በመሳ ሰሉት ዘዴዎች ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የግንዛቤ ወይም የዕውቀት ምንጭ ነው፡፡ መረጃዎችን በማየት፣ በማዳመጥ፣ በማሽተት፣ በመዳሰስ ወይም በመቅመስ ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ መረጃዎችን ከአካባቢያችን ወይም ከአካባቢያችን ውጪ ልናገኝ እንችላለን፡፡

ከአካባቢያችን ከምናገኛቸው መረጃዎች መካከል የአካባቢ ሠላም፣ የመምህራን ጾታና ዕድሜ፣ ተዘ ውትረው የሚከበሩ በዓላት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ውጤት፣ የዓለም የነዳጅ ዋጋ ሁኔታ፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት የመሳሰሉት ደግሞ ከአካባቢያችን ወጣ ካሉ ምንጮች የምናገኛቸው ናቸው፡፡

ዕውቀታችንን ለማዳበር የሚረዱን የተለያዩ የመ ረጃ ምንጮች አሉ፡፡ በዋናነት የሚጠቀሱ ትም መደበኛ ትምህርት፣ ንባብ፣ መገናኛ ብዙኃን፣ ጉብኝት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ምልከታ የምንለው አንድን በአካባቢያችን የሚከሰት ክስተት ወይም የሰ ዎችን ተግባር በጥንቃቄ መመልከትን ነው፡፡ ለምሳሌ ከፍ ሲል ያነበብነውን «ራስ ስሞሽ» ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈልን ሰው አጨዳ ሥፍራ እየተገኘ በትኩረት ተመልክቶ፣ የሀገር ሽማግሌ ዎችንም አነጋግሮ መረጃ አግኝቷል፤ ያንን በም ልከታውና በጥየቃ የደረሰበትን ዕውቀቱን ነው ለእኛ ያካፈለን፡፡ ያንን ያነበቡ ሰዎች ደግሞ በየራሳቸው ቋንቋ ሐሳቡን ያሰራጩታል ማለት ነው፡፡

ትምህርት ቤት ደግሞ ከሁሉም የበለጠ የዕውቀት ማግኛ ቦታ ነው፡፡ በልዩ ልዩ ሙያዎች የሠለ ጠኑ ምሁራን በትምህርት ቤት ይገኛሉ፡፡ እነሱም እኛን ለመርዳት ቀን ከሌሊት ይደክማሉ፡፡ መጻሐ ፍትን፣ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንም በማንበብ ዕ ውቀት ልናገኝ እንችላለን፡፡

ሌሎቹ የዕውቀት ምንጮች እንደ ሬዲዮና ቴሌ ቪዥን ያሉት ናቸው፡፡ እነዚህ በዓለም ዙሪያ ያሉ ወቅታዊ ጉዳዮችን ተከታትለው በማቅረብ በኩል ተወዳዳሪ የላቸውም፡፡ በተለያዩ የሥራ አጋጣሚዎች ወይም በቱሪዝም ጉብኝት በተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወርም በርካታ ዕውቀት እናገ ኛለን፡፡ በጉብኝት ስለመሬት አቀማመጥ፣ ስለ አየር ሁኔታ፣ ስለሕዝቦች ባሕል ዕውቀት እንቀ ስማለን፡፡

ታዲያ እነዚህን ከተለያዩ ምንጮች ያገኘናቸውን መረጃዎች በሚገባ ለመረዳትና ከራሳችን ጋር ለማዋሐድ በተግባር ላይ ማዋል አለብን፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ጥቅምና ጉዳታቸውን እያስተዋልን፣ ደጋግመን ማጥናት ይኖርብናል፡፡ በዚህም ውጤ ታማ ለመሆን በማስታወሻዎች መመዝገብ ወይም በካሴት መቅረጽ ይጠበቅብናል፡፡

**መልመጃ 4**

***ከሚከተሉት ርእሶች መካከል የሚያመቻችሁን በመምረጥ፣***

?

ሀ. ርእሱን የሚያዳብሩ መረጃዎችን ከተ ለያዩ ምንጮች ሰብስቡ፡፡

ለ. ለይታችሁ ያወጣችኋቸውን መረጃዎች በተለያዩ መንገዶች አደራጁቸው፡፡

1. የትምህርት ቤታችሁ አመሠራረት ታሪክ፣
2. የጥገት ላምን ጤንነት እንዴት መንከባከብ ይቻላል?
3. ማር አዘውትሮ መመገብ ለጤንነት ምን ጥቅም አለው?

## 11.3 ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት

- አንዳንድ ሰዎች በማዳበሪያ የለማ እህል በ ረከት የለውም ሲሉ ይደመጣሉ፤ ይህ አስተ ሳሰብ ትክክል ይመስላችኋል? ለምን?
- በአካባቢያችሁ የሚነገሩ ኋላቀር አባባሎችን ዘርዝሩ።
- በአካባቢያችሁ ኋላቀር ብላችሁ የምት ገነዘቧቸውን አስተሳሰቦች እንዴት ማስወገድ ይቻላል? በማስወገዱ ሂደት የእናንተስ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?

ኋላቀር አመለካከት በጭፍን አስተሳሰብ ላይ የተ መሠረተ ልማድ ነው:: በኋላቀር አመለካከት ከተ መራን ለምናደርገውም ነገር ሆነ ለምናከናው ነው ተግባር አሳማኝ ምክንያት የለንም:: ልማዱ ለብዙ ጊዜ አብሮን የኖረ ሊሆን ይችላል:: በመሆ ኑም ሳይንሳዊና ዘመናዊ አስተሳሰብን እንዳንቀበል ያደርገናል::

በማይጨበጡ ግምቶችና እምነቶች እንድንገዛ ይገፋፋናል:: ለምሳሌ «የሸክላ ሥራ ለምን የተ ወሰኑ ቡድኖች ሙያ ብቻ ሊሆን ቻለ?» ብን ባል ተጨባጭ መልስ የለንም:: «ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ» የሚለው አባባል አብሮን ስለኖረ እኛም በጭፍን እንናገረው ይሆናል:: «ለምን?» ለሚል ጥያቄ ግን ሳይንሳዊ ምላሽ ሊቀርብ አይ ችልም::

ኋላቀር አመለካከቶች በልዩ ልዩ መልኮች ይከሰ ታሉ:: አንዳንዶቹ በምሳሌያዊ ንግግሮችና በቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ይገኛሉ:: ሌሎቹ በተግባር የሚገለጹና ጤንነትንም የሚጎዱ ናቸው:: ጤናን ከሚጎዱት መካከል የሴት ልጅ ግርዛትና ጉሮሮን ማስቧጠጥ ይጠቀሳሉ:: በእምነት መልክ የሚታ ዩም አሉ:: «የሰው ቡዳ አለ» ብሎ ማመን አንዱ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው:: በአንድ በኩል «ቡዳ» የተባለውን ሰው ማኅበራዊ ደኅንነት የሚጎዳ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ሰዎችን በመፍ ራት በጭንቀት እንዲሰቃዩ ያድርጋል::

ኋላቀር አመለካከት ያለው ሕዝብ ዕድገቱ አይፋ ጠንም:: ምክንያቱም ጠቀሜታ ያላቸው ነገሮች እንዲወገዱ ይደረጋል:: ጎጂ የሆኑት ግን ይበ ረታታሉ:: ይህ ደግሞ ዕውቀት እንዳይስፋፋ ያደርጋል:: ስለዚህ አዲሱ ትውልድ ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ሊያስወግዳቸው ይገባል::

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ኋላቀር አስተሳሰቦች በአካባቢያችሁ ነዋሪዎች ላይ ምን ጉዳት ሲያስከትሉ ይችላሉ?
2. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲዳብር ኋላ ቀር አስተሳሰቦች ይወገዳሉ ወይስ ይቀጥላሉ? ለምን?

## 11.4 የንባብ ባሕል



*ሥዕል 11.5 መጽሐፍን በማንበብ ሳይንስዊ አስተሳሰብን ማዳበር*

- በሥዕሉ ላይ የምትመለከቷቸው ልጆች ምን እያደረጉ ነው?
- እንደነዚህ ልጆች አንባቢ መሆን ምን ጥቅም ያስገኝ ይመስላችኋል?
- ንባብና ዕውቀት ምን ግንኙነት አላቸው ትላላችሁ?

ንባብ በወረቀት ወይም በሌላ ዝርግ አካል ላይ በሆሔያት ተጽፎ የቀረበን ሐሳብ መቅሰሚያ መንገድ ነው:: የሚቀሰመውም ነገር መረጃን የሚ ሰጠን፣ ዕውቀታችንን የሚያስፋልንና የሚያዝ ናናን ሊሆን ይችላል::

ገና ከልጅነታችን ጀምረን የንባብ ልምዳችንን ማሳደግ ይገባናል:: ከጨቅላ ዕድሜያችን ጀምረን እንድንጎበዝ መጻሕፍትን አዘውትረን ማንበብ ይኖርብናል:: በንባብ አማካኝነት ዕውቀታቸውን አዳብረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች አሉ:: ለምሳሌ በሀገራችን እንደነ ከበደ ሚካኤል፣ ይልማ ዴሬሳ፣ ጸጋዬ ገብረ መድኅንና ሌሎችም ግለሰቦች «ታላላቅ ሰዎች» መሆን የቻሉት ገና ከልጅነታቸው ጀምረው የንባብ ልምድ ስለነበራቸው ነው::

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ጠንክረው በማንበብና በመማር ከትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ በአካባቢያችሁ ወይም በሀገር ደረጃ የሚታወቁ ሰዎችን ስም ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቃችሁ ወይም ከጽሑፍ ሳይ አንብባችሁ መረጃ አሰባስቡ:: ከዚያም እነዚህ ሰዎች ስአካባቢያቸውና ለሀገራቸው ምን እንደሰሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::
2. ቀጣዩን ግጥም በሚገባ አንብቡና ከግርጌው የሚመጡትን ጥያቄዎች መልሱ::



*ሥዕል 11.6 የዕውቀት ምንጭ ከሆኑት ውስጥ መጽሐፍት አንዱ ናቸው*

**መጽሐፍ ወዳጄ**

ጥናት የወለዳት፣ ሳይንስ ያሳደጋት፣
ፈላስፎች ሸልመው፣ ምሁራን ያስጌጧት፣
ስለክብሯ ብዛት፣ ሰዎች የማሉላት፣
አለችኝ ፍቅረኛ፣ መጽሐፍ የሚሏት::
የምሁራን ዳኛ፣ የጥበብ መስካሪ፣
እንዳባት አለኝታ፣ እንደናት መካሪ፣
የድንቁርና መርዝ፣ የጨለማ ባትሪ፣
ገስግሰሽ ነይልኝ፣ መጽሐፌ ላንብብሽ፣
ውስጤ አንቺን በማጣት፣ እንዳይራብብሽ::
ልንገርሽ አድምጪኝ፣ ሆነሽ ካጠገቤ፣
መንፈሴ ተጠማ፣ ተራበልሽ ልቤ፣
ድረሽ መጽሐፌ፣ የአእምሮ ቀለቤ::
የጥናት መብራቴ፣ የሳይንስ ወዳጄ፣
ስሄድ በመንገዴ፣ ስቀመጥ በደጄ፣
አጋር መጽሐፌ፣ አትለይኝ ከጄ::
ውዷ መጻሐፌ፣ አንቺን ያነበበ፣
አእምሮው ዳበረ፣ ዕውቀት ተመገበ፣
ልቡ ተስፋ አገኘ፣ መንፈሱ ጠገበ::

ሀ. መጽሐፍ እንዴት እንደ ባትሪ ሊታይ ይችላል?
ለ. መጽሐፍ ድንቁርናን የሚገል መርዝ እንደሆነ መገለጹ ልክ ነው? ለምን?
ሐ. ባጠቃላይ ስትመለከቱት፣ መጽሐፍ ማንበብ ምን ምን ጥቅሞች አሉት?

## 11.5 የትምህርት አጠናን ዘዴ

- ትምህርታችሁን ማጥናት ከመጀመራችሁ በፊት ምን ዓይነት ዝግጅት እንደምታደርጉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
- ትምህርታችሁን ማጥናት ከጀመራችሁ በኋላስ የጥናት ተግባራችሁን እንዴት ታከናውናላችሁ? ጥናታችሁን ካጠናቀቃችሁ በኋላስ ምን ታደርጋላችሁ?

ትምህርትን በሚገባ ማጥናት ብዙ ጥቅሞች አሉት:: ጥሩ ውጤት በማምጣት ከክፍል ወደ ክፍል ማለፍ የምንችለው በጥልቀት ስናጠና ነው:: በሚገባ አጥንተን በትምህርታችን ከፍ ወዳለ ደረጃ ከደረስንም መምህር፣ መሐንዲስ፣

ግንበኛ፣ ሠዓሊ ወዘተ በመሆን ራሳችንን፣ ቤተሰ ባችንን፣ ማሕበረሰባችንና ሀገራችንን ልናገ ለግል እንችላለን::

ስናጠና ጥናታችንን በተዋጣ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉንን ዘዴዎች መከተል ይገባል:: አስ ቀድመን አመቺ የጥናት ጊዜና ጸጥታ ያለው ቦታ መምረጥ ያሻል:: ጥናታችንን ስንጀምር ደግሞ ጠቃሚ ሐሳቦችን በማስታወሻ ማስፈር ጥሩ ነው::

የምናጠናውን ትምህርትም ከራሳችንና ከአካባ ቢያችን ሁኔታ ጋር ማመሳከር አስፈላጊ ይሆ ናል:: የሐሳቡንም እውነትነት መመርምር ይገ ባል:: በመጨረሻም ንድፈ ሐሳቡን በቃል መሸም ደድ ሳይሆን፣ እንዴት አድርገን በሥራ ላይ ልናውለው እንደሚገባን ማሰብ አለብን::

ያኔ ያጠናነው ዕውቀት ተጨባጭነት ይኖረዋል፣ ጥናታችንም ግቡን መቷል ማለት ነው::

**መልመጃ 7**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ማብራሪያ በማቅረብ መልሱ::***

?

1. የጥናት ጥቅም ምንድነው?
2. አንድ ተማሪ በሚከተሉት የጥናት ደረጃ ዎች ሳይ ምን ማድረግ አለበት?
   ሀ. በቅድመ ጥናት ወቅት፣
   ለ. በዐውደ ጥናት ወቅት፣
   ሐ. በድኅረ ጥናት ወቅት::
3. በጥናት ወቅት ማስታወሻ መያዝ ጥቅሙ ምንድነው?
4. ማስታወሻ ስንይዝ ምን ዓይነት ዘዴ መከተል አለብን?
5. ጥናታችን በትክክል ግቡን መቷል የሚባለው መቼ ነው?

**የቡድን ሥራ**

ጥናት የራሱ የሆነ የሂደት ቅደም ተከተል ይኖ ረዋል:: ሂደቱም «ቅድመ ጥናት፣» «ዐውደ ጥናት» እና «ድኅረ ጥናት» የሚባሉ ደረጃዎች ያሉት ነው:: ቀጥሎ የቀረበው ሥዕላዊ መግ ለጫ ስለነዚህ የሂደት ደረጃዎች አጭር ማስገ ንዘቢያ ይሰጣችኋል:: መግለጫውን ልብ በሉና ጥናት እንዴት ሊከናወን እንደሚችል በቡድን ተወያዩበት::

ቅድመ ጥናት፤
አመቺ የጥናት ጊዜ፣ ቦታ፣
የጥናት ቁሳቁሶችን መምረጥ፣
የጥናት ዕቅድ መንደፍ::

ዐውደ ጥናት፤
በተመስጥዎ ማንበብ፣ ከራስ
ተሞክሮና በአካባቢ ካለ ዕውነታ ጋር
ማገናዘብ፣ ማስታወሻም መያዝ::

ድኅረ ጥናት፤
የያዙትን ማስታወሻ መከለስ፣ የተገ
ኘውን ዕውቀት በተግባር ላይ
ለማዋል የሚያስችል ሥራ
መሥራት::

በተለይ በትምህርት ጥናት ውስጥ ማስታወሻ መያዝ በጣም አስፈላጊ ነው:: ቀጥሎ ባሉት ሳጥኖች ውስጥ የምትመለከቷቸው ነጥቦች የጥ ናት ማስታወሻ በመያዝ ሂደት ውስጥ "ወርቃማ ሕጎች" የሚባሉ ናቸው:: እስቲ በቡድን እየሆናችሁ ምንነታቸውንና አስፈላጊነታቸውን ተወያዩባቸው::

አዘውትሮ ማስታወሻ መያዝ

ነጥቦችን መከለስ

በሐሳብ እየተሳተፉ ማንበብ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ዕውቀት ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝና ራሳችንን እንዲሁም አካባቢያችንን ለመለወጥ የሚያስችለን መሣሪያ መሆኑን ተገንዝባችኋል:: ይህም ዕውቀት ከትምህርት ቤት፣ ከንባብ፣ አካባቢን ከመመልከት ሲገኝ እንደሚችል ተመራችኋል። ጎጂ ልማዶችን በተመለከተም ያነሳነው ነጥብ በጣም ጠቃሚ ቁም ነገሮችን አስጨብጣችኋል። ሳይንሳዊና ተጨባጭ ባልሆኑ ጭፍን ግምቶችና ልማዶች መመራት ለኋላቀር አስተሳሰብ ተገዥ ያደርጋል። አስተሳሰባችን ኋላቀር በሆነ ቁጥር ደግሞ ራሳችንን ለመለወጥና አካባቢያችንን ለማልማት አንችልም። ከዚህም አልፎ ኋላቀር አስተሳሰብ በጤና ላይም ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

ጥናት የቅድመ ዝግጅት፣ የዐውደ ጥናትና የድኅረ ጥናት ደረጃዎች አሉት። ቅድመ ጥናት ለጥናት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማመቻቸትን የሚያካትት ነው። ዐውደ ጥናት በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተቀምጠን የምናጠናበት ጊዜ ሲሆን፣ እሱም ከፍ ያለ ጸጥታን ይሻል። የድኅረ ጥናት ደረጃም ያጠናነውን ትምህርት ፍሬ ሐሳቦች አሰባስበንና አደራጅተን መያዛችንን የምናረጋግጥበት ነው።

እንግዲህ በትምህርቱ ውስጥ ሁሉንም ፍሬ ነገሮች በጥንቃቄ እየተመለከታችሁ እንደመጣችሁና እነዚህን ዋና ዋና ነጥቦች እንደጨበጣችሁ እንዲሁም የተሻለ ዕውቀት እንደቀሰማችሁ ይታመናል። ነገር ግን ብዙ ዕውቀት ማግኘታችሁ በራሱ በቂ አይደለም። ይልቅስ የተማራችሁትን ፍሬ ነገር በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ማድረግም ይጠበቅባችኋል። ዕውቀትን በበለጠ ለመቅሰምና ጎጂ የሆኑ ልማዶችንና አስተሳሰቦችን ለመዋጋት ከባድ አደራ አለባችሁ።

## ቁልፍ ቃላት

**ዕውቀት፣** ነገሮችንና ሁኔታዎችን በብቃት ለመረዳት የሚስችል ብቃት።

**መረጃ፣** ስለጉዳዮች ለማወቅ የሚሰበሰብ ጥሬ ሐሳብ።

**ጥናት፣** ዕውቀትን በሚገባ ለመጨበጥ ጽሑፋዊ ወይም ሌሎች የመረጃ ፍንጮችን የመፈተሽ ዘዴ።

**ኋላቀር አስተሳሰብ፣** በትምህርት ያልተደገፈ፣ በጭፍን የሚታመን ወይም በልማድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ጎታች አመለካከት።

**ዐውደ ጥናት፣** በጥናት ሂደት ሳይ እያለን የሚስተዋል ወይም የሚከናወን ሁኔታ።

**ድኅረ ጥናት፣** ጥናታችንን ስናጠቃልል የምናከናውናቸው ተግባራት።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡***

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. ተጨማሪ ዕውቀት ለማግኘት ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ ጥሩ ነው፡፡
2. ጉብኝት የመዝናናት እንጂ የዕውቀት ማግኛ ዘዴ ሊሆን አይችልም፡፡
3. ውጤታማ ነጋዴ ለመሆን የተሻለ ዕውቀት ያስፈልጋል፡፡
4. ልዩ ልዩ ነገሮችን በትኩረት በመመልከት ዕውቀትን ማዳበር ይቻላል፡፡
5. የሰው ልጆች አስተማማኝ ዕውቀት የሚያገኙት መጻሕፍትን በማንበብ ብቻ ነው፡፡

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉትጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዐውደ ጥናት፣ | ሀ. ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ መጻሕፍት። |
| 2. ዋናው የዕውቀት ምንጭ፣ | ለ. የጥናት ቁሳቁሶችን መምረጥ። |
| 3. ኋላቀር አመለካከት፣ | ሐ. ታላላቆችን ማክበር። |
| 4. የመረጃ ምንጮች፣ | መ. የሴቶችን ሥራ ወንዶች መሥራት የለባቸውም። |
| 5. ቅድመ ጥናት፣ | ሠ. ትምህርት በትኩረት የሚነበብበት ሂደት። |
| | ረ. ትምህርት ቤት። |

**III. የሚከተሉት ፕያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ኋላቀር አስተሳሰቦች እየተዳከሙ ሊሄዱ የሚችሉት መቼ ነው?
   ሀ. በትምህርታችን እየጎለበትን ስንሄድ፣
   ለ. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲዳከም፣
   ሐ. ባሕላችንን ትተን የፈረንጆችን ባሕል ስንማር፣
   መ. ለ እና ሐ፡፡
2. አስተማማኝ የዘመናዊ ዕውቀት ምንጭ የቱ ነው?
   ሀ. ትምህርት ቤት፣
   ለ. መኖሪያ ቤት፣
   ሐ. በአካባቢያችን ያሉ የሀገር ሽማግሌዎች፣
   መ. ለ እናሐ፡፡
3. ከሚከተሉት መካከል መረጃ ሊያቀርብልን የሚችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ጋዜጣ፣
   ለ. ሬዲዮ፣
   ሐ. ቴሌቪዥን፣
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ፡፡

4. በጥናት ጊዜ ማስታወሻ የመያዝ ጥቅም ምንድነው?
   ሀ. ያነበብነው ሐሳብ ወዲያው እንዳይረሳን ለማድረግ፣
   ለ. ስናነብ ያልገባን ነገር ካለ ከሰዎች ጋር ለመወያየትና ለመረዳት፣
   ሐ. የእጅ ጽሑፋችንን ለማሻሻል፣
   መ. ሀ እና ለ፡፡

5. ከሚከተሉት መካከል ጎጂ አስተሳሰብ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ገላን አዘውትሮ መታጠብ ለቆዳ ድርቀት ይዳርጋል፣
   ለ. በቤት ውስጥ ሴት ልጆች የሚሠሩትን ሥራ ወንዶቹም ማገዝ አለባቸው፣
   ሐ. ባህላዊ ድርጊቶችን ሁሉ መደገፍ ተገቢ ነው፣
   መ. ወንዶች የሚሠሩትን ሥራ ሴቶች ሊሠሯቸው አይችሉም፡፡

## IV. ከታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች ጠቃሚ ከሆኑ «ገንቢ» ጎጂ ከሆኑ ደግሞ «ኋላቀር» እያላችሁ በባዶ ቦታው ላይ «✓» ምልክት አድርጉ::

| ዝርዝር ጉዳዮች፤ | ገንቢ | ኋላቀር |
|---|---|---|
| *ምሳሌዎች፣* | | |
| ሀ. ጉሮሮ ማስቧጠጥ፣ | | ✓ |
| ለ. በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም:: | ✓ | |

1. መተዳደሪያ ላጡ ሰዎች ምጽዋት ከመስጠት ይልቅ የሥራ ዕድል፣ መፍጠር፡፡
2. የሽክላ ሥራ ጠቃሚ ሙያ አይደለም፡፡
3. ሕጻናት ሲታመሙ ወደሐኪም ቤት መውሰድ፡፡
4. መማር፣ መማር አሁንም መማር  እናትና አባትን ማክበር፡፡
5. ሴት ልጅን ማስገረዝ፡፡
6. በሰው ርዳታ ከመተማመን ይልቅ ተፍጨርጭሮ ራስን መቻል።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ዕውቀት ለማግኘት የሚረዱን ምን ምን ዓይነት ምንጮች አሉ?
2. በጥናት ጊዜ አዘውትሮ ማስታወሻ መያዝ ለምን ይጠቅማል?
3. ስናጠና በተሳታፊነት ማንበባችንን እንዴት ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን?